# የኢትዮጵያ ታሪክ

# ኢጣሊያ በኢትዮጵያ

## ከወልወል እስከ ጐንደር

ግንቦት 1927 - ህዳር 1934 ዓ.ም

ከተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ ዕትም 2004 ዓ.ም

አሳታሚ፡- ማንኩሳ አሳታሚ ኃ.የተ.የግ.ማኅበር

# ማውጫ


| ምዕራፍ | አርዕስት | ገፅ |
|---|---|---|
| ምስጋና | ............................................................ | 5 |
| መቅድም | ............................................................ | 6 |
| መግቢያ | ............................................................ | 7 |
| ምዕራፍ 1፤ | ኢትዮጵያ ከአድዋ እስከ ማይጨው | 8 |
| ምዕራፍ 2፤ | ኢጣልያ ከውህደት እስከ ማይጨው ዋዜማ | 14 |
| ምዕራፍ 3፤ | የጎንደር ውዝግብና የወልወል ግጭት የአውሮፓ መንግስታት አመለካከት | 20 |
| ምዕራፍ 4፤ | ጦርነቱን ለማስቀረት የተደረገ የዲፕሎማቲክ ጥረት | 25 |
| ምዕራፍ 5፤ | የጦር ዝግጅት | 27 |
| ምዕራፍ 6፤ | የአድዋና የአክሱም መያዝ | 30 |
| ምዕራፍ 7፤ | የኢትዮጵያ ሠራዊት የክተት እንቅስቃሴ | 32 |
| ምዕራፍ 8፤ | የሽሬ ጦር ግንባር | 36 |
| ምዕራፍ 9፤ | የተንቤን ጦር ግንባር | 39 |
| ምዕራፍ10፤ | የአምባራደም ጦር ግንባር | 44 |
| ምዕራፍ11፤ | የኦጋዴን ጦር ግንባር | 46 |
| ምዕራፍ 12፤ | የቦረና ጦር ግንባር | 51 |
| ምዕራፍ 13፤ | የማይጨው ጦርነትና የኢትዮጵያ ድል መሆን | 57 |
| ምዕራፍ 14፤ | ከማይጨው መልስ | 61 |
| ምዕራፍ 15፤ | የንጉሠ ነገሥቱ ስደትና የኢትዮጵያ ሠራዊት መፍረስ | 65 |
| ምዕራፍ 16፤ | የኢጣልያን አዲስ አበባ መግባት | 68 |
| ምዕራፍ 17፤ | ኢትዮጵያ ለምን፤እንደምን ተሸነፈች? | 71 |
| ምዕራፍ 18፤ | የገጠሩ ሕዝብ ሁኔታና የአርበኝነትአጀማመር | 75 |
| ምዕራፍ 19፤ | የሲዳሞ ተጋድሎ | 79 |
| ምዕራፍ 20፤ | በሐረርጌ፣ በባሌና በአርሲ የተካሄደ ትግል | 87 |
| ምዕራፍ 21፤ | በጉራጌ አገር የተካሄደ አርበኝነት | 89 |
| ምዕራፍ 22፤ | በጋሞ ጎፋ የተካሄደ ትግል | 96 |
| ምዕራፍ 23፤ | በኢሊባቦርና በከፋ የተካሄደ ትግል | 98 |
| ምዕራፍ 24፤ | በወለጋ የተካሄደ የአርበኝነት ሥራ | 107 |
| ምዕራፍ 25፤ | ግንደ በረትና በሜጫ የተደረገ ትግል | 112 |
| ምዕራፍ 26፤ | በመርሃቤቴና በሰላሌ የተካሄደ ትግል | 122 |
| ምዕራፍ 27፤ | የመገናኛ መሥመርን መቆጣጠር | 139 |
| ምዕራፍ 28፤ | በቡልጋና ሸንኮራ የተካሄደ ትግል | 142 |
| ምዕራፍ 29፤ | የአንኮበርና ይፋት ትግል | 194 |
| ምዕራፍ 30፤ | የመንዝና ተጉለት ተጋድሎ | 205 |
| ምዕራፍ 31፤ | የጎጃም ጥዝጥዝ | 228 |
| ምዕራፍ 32፤ | የወሎ ትግል | 246 |
| ምዕራፍ 33፤ | የትግራይ ተጋድሎ | 254 |
| ምዕራፍ 34፤ | የጎንደር ተጋድሎ | 257 |
| ምዕራፍ 35፤ | የአዲስ አበባ የትግል አስተዋጽኦ | 294 |
| ምዕራፍ 36፤ | የሴቶችና የልጆች ሚና | 309 |
| ምዕራፍ 37፤ | የውስጥ አርበኞች ተጋድሎ | 313 |

| | | |
|---|---|---|
| ምዕራፍ 38፤ | የስደተኛው ትግል | 318 |
| ምዕራፍ 39፤ | የአርበኝነት ሥልት | 337 |
| ምዕራፍ 40፤ | የአርበኞቹ የእርስበርስ ግንኙነት | 347 |
| ምዕራፍ 41፤ | በአርበኞች ዘንድ የነበረ የፍርድ ሥራ | 353 |
| ምዕራፍ 42፤ | የጣልያን የግፍ ሥራዎች | 360 |
| ምዕራፍ 43፤ | የእሥረኞችና የእሥር ቤቶች ሁኔታ | 368 |
| ምዕራፍ 44፤ | የድርጅት ጥያቄ በአርበኞች ዘንድ | 373 |
| ምዕራፍ 45፤ | ጤናና ምግብ | 380 |
| ምዕራፍ 46፤ | ከሐዲዎችና የክህደት ሥራቸው | 384 |
| ምዕራፍ 47፤ | ግጥምና ቅኔ | 394 |
| ምዕራፍ 48፤ | የጣልያኖች ፖሊሲ | 399 |
| ምዕራፍ 49፤ | የኢጣልያን የምሥራቅ አፍሪቃ አስተዳደር | 409 |
| ምዕራፍ 50፤ | የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሚና | 419 |
| ምዕራፍ 51፤ | የአውሮፓ ሁኔታና የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሥልት | 423 |
| ምዕራፍ 52፤ | የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የድል ጉዞ | 432 |
| ምዕራፍ 53፤ | ኢትዮጵያን ነፃ ለማውጣት የተንቀሳቀሰው የእንግሊዝ ጦር | 446 |
| ምዕራፍ 54፤ | የኢትዮጵያና የጣልያን ጦርነት ፍፃሜ | 453 |
| ምዕራፍ 55፤ | በጦርነቱ ውስጥ የእምነት ድርጅቶች ሚና | 467 |
| ምዕራፍ 56፤ | ጦርነቱ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ያደረሰው ጉዳት | 481 |
| ምዕራፍ 57፤ | የጦርነቱ ጠቅላላ ግምገማ | 491 |
| ምዕራፍ 58፤ | የአድዋና የማይጨው ጦርነቶች ንጽጽር | 498 |
| ምዕራፍ 59፤ | የኢጣልያ ህልምና ውጤቱ | 502 |
| ምዕራፍ 60፤ | የኢትዮጵያ የጦር ፍርድ ቤት | 506 |
| ምዕራፍ 61፤ | ከድል በኋላ ትግል | 509 |
| ምዕራፍ 62፤ | የሰላም ንግግር ከኢጣልያ ጋር | 523 |
| ምዕራፍ 63፤ | ኢትዮጵያና ነፃነትዋ | 527 |
| አባሪ 1፤ | የንጉሠ ነገሥት መልእክ ፀሐይ አነጋገስ | 535 |
| አባሪ 2፤ | የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች ማህበር አመሰራረት | 536 |
| አባሪ 3፤ | የሙሶሊኒ አጭር የህይወት ታሪክ | 538 |
| አባሪ 4፤ | የፋሺስት ፓርቲ አነሳስና አወዳደቅ | 557 |
| አባሪ ስሌዳ፤ | የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት ያስከተለው የኢኮኖሚ ጉዳት | 565 |
| | የፀሐፊው አጭር የሕይወት ታሪክና ፎቷቸው | 567 |
| | ዋቢ የአማርኛ መጻሕፍት | 569 |
| | ዋቢ የእንግሊዝኛ መጻሕፍት | 572 |
| | ኢጣልያ በኢትዮጵያ ለሚለው መፀሐፍ የምስክርነት ቃል የሰጡ ሰዎች | 573 |


# ምስጋና


ከዚህ የደረስኩት በብዙዎች ዕርዳታና ድጋፍ ሲሆን ጥቂቶቹን ስም በመጥራት፣ ብዙዎችን በጠቅላላው ማመስገን እፈልጋለሁ::

1. በመጀመሪያ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረኝን ልዑል እግዚአብሔር፣ በችግሬ ሁሉ የረዳችኝን ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ ቸር ጠባቂዬን ቅዱስ ሚካኤልን አመሰግናለሁ::
2. የወለዱኝን፣ ያሳደጉኝን፣ ችግራቸውን ታግሰው የመማር ዕድል የሰጡኝንና ሳይንቁ ቃሌን የሰሙኝን አባቴን አለቃ ዘዮሐንስ ዘውዴ ሀብቱንና እናቴን ወይዘሮ ጸዳለ አባብለው ተክሌን አመሰግናለሁ::
3. ለአሳደጉኝ አያቴ ለይቶት በሀብትዋ ወልደሥላሴ ወንድሜነህ፣ በችግሬ ለረዱኝ አጐቴ ለፊታውራሪ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ፣ ፍሬ ሳይተካ በጦርነት ለወደቀው አጐቴ ለአቶ ኃይለሥላሴ ዓለሙ ባለውለተኛነቴን እገልፃለሁ::
4. በጦርነቱ ጊዜ በቤተሰብነት የደገፈችን ወይዘሪት/ወይዘሮ/ እምሪቱ አባብለውን፣ ወይዘሪት/ወይዘሮ/ ሥዕለ ዘዮሐንስን፣ አያ ማሩ አቶ ካሣ ዘዮሐንስን አስባቸዋለሁ::
5. አስተምረው የእውቀት ብርሃን የከፈቱልኝን አለቃ ዘዮሐንስን፣ መምህር ገድሌን፣ መምህር ጌታሁን/ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስን/፣ ኃይለማርያም ማሞ ትምህርት ቤት ያስገባኝንና በኑሮዬ የረዳኝን አቶ መኮንን ወልደሚካኤልን፤ በኑሮዬ የረዱኝን አቶ ግዛው ደስታን፣ በአዳሪነት እንድማር የፈቀዱልኝን ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን፤ ደብረ ብረሃን የኃይለማርያም ማሞ ትምህርት ቤትና የአዲስ አበባ መምሕራን ማሠልጠኛ ተቅዋም መምሕራንን፤ እንደዚሁም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ የማታውን ክፍል መምህራን አመሰግናቸዋለሁ::
6. ይህንን መጽሐፍ በምጽፍበት ጊዜ ማስረጃ የሰጡኝን፣ በጽሕፈት ሥራ የረዳችኝን ወይዘሪት የወርቅውሃ ጽጌ፣ በሕትመቱ ሥራ የተባበሩኝ የት.መ.ማ.ድርጅት ሹማምንትና ሠራተኞች ባለውለታዎቼ ናቸው::

# መቅድም

የዚህ መፅሐፍ ዓላማ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የተካሄደውን ጦርነት በአጠቃላይ ማመልከት ነው። ከወልወል ግጭት እስከ ጎንደር ነጻ መውጣት ለስድስት ዓመት ከስድስት ወር የተካሄደውን ረዥምና መራራ ትግል ይዘክራል። መፅሐፉን የሚያነቡ ሁሉ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች እንዲያጤኑ ያስፈልጋል።

1. በታሪኩ ሂደት በሀገር ውስጥና በውጭ አገር የተከናወነው ሥራ እንደየጊዜው ቅደም ተከተል ተገልፆአል።
2. እውነተኛውን ነገር ፈልፍሎ ለማውጣት ልዩ ጥረት ተደርጓአል።
3. የታሪኩ አጻጻፍ፤
   ሀ. ፍልሚያ በተካሄደባቸው ክፍላተ ሀገር እየተለየ፣
   ለ. የጊዜው ቅደም ተከተል እየተጠበቀ፣
   ሐ.የመሪዎችና የሠራዊት አገልግሎት እየተመዛዘነ ነው።
4. የታሪኩ ትንታኔ የተመዛዘነና አጠቃላይ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ እንዲሆን ጥንቃቄ ተደርጓአል።
5. ዘመንና ቀናት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ተመልክተዋል። አስፈላጊ በሆነበት የአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በቅንፍ ተገልጧል።
6. የማዕረግ ሥም የተጠቀሰው ሥራ በተሠራ ጊዜ የነበረው ነው። በኋላ የተገኘው በቅንፍ ውስጥ ተመልክቶአል።
7. የገንዘብ ጉዳይ የታሰበው በኢትዮጵያ ሲሆን አንድ የአሜሪካ ዶላር በሁለት ብር ተኩል፣ አንድ የእንግሊዝ ፓውንድ በአሥር ብር እየተሰላ ነው።
8. የሰውና የሰነድ ምንጮች በተገቢው ሥፍራ በቁጥር ከተመለከቱ በኋላ፤ ዝርዝራቸው ለማመሳከሪያነት በየምዕራፉ መጨረሻ ቀርቦአል። አጠቃላይ የማጣቀሻ መፅሐፍት ዝርዝርና የቃል ምስክርነት የሰጡ ግለሰቦች መግለጫ በመፅሐፉ መጨረሻ ላይ ሰፍሮአል።

# መግቢያ

ኢትዮጵያ ለም አፈር፣ ለስላሳ አየር ያለባት፤ ታታሪና አስተዋይ ህዝብ የሠፈረባት ሀገር ናት። ይህም ሆኖ ሕዝቧ በችግር ተቆራምዶ ያኖራል። ይህም ደግሞ ያለምክንያት አይደለም። ሀገሪቱ ዘላቂ ሰላም ባለማግኘቷ፤ ሕዝቧም ስለሁኔታዎች ትክክለኛ ግንዛቤ ካለማግኘቱ የተነሳ ነው። ትክክለኛ ግንዛቤ ማግኘት የሚቻለው ደግሞ ከእውነተኛ ታሪክ ነው።

ኢትዮጵያ ከ3016 ዓመተ ዓለም ጀምሮ፣ ማለትም ክርስቶስ ሲወለድ 2484 ዓመታት ሲቀረው፣ መንግሥት የተመሠረተባት ሀገር ናት። ከሰብታህ እስከ ንግሥት ሳባ፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከዛሬ 5000 ዓመት ያህል በመንግሥትነት ጸንታ በነፃነት ኖራለች። በዚህ ረጅም ዘመን ብዙ ውጣ ውረድ አጋጥሞአታል። ታላቅ የታሪክ ሀብትም አድልባለች። ነገር ግን በዚህ የታሪክ ሀብቷ በሚገባ አልተጠቀመችበትም። ለዚህም ብዙ ምክንያቶች አሉ። ብዙው ታሪኳ አልተፃፈም። ከተፃፈው ከጥቂቱም ብዙው ተዛብቶአል፣ ተበላሽቶአል፣ ጠፍቶአል። ይህ ሊሆን የቻለው ደግሞ የተነሳው መሪ ሁሉ ከእሱ በፊት የነበረውን እያስረከሰ፣ የራሱን እያስነገሰ ስለሚያፅፍ የሀገሪቱ ታሪክ የዝቅዝቂት በመሄዱ ነው።

አዲሱ ትውልድ ይህንን መጥፎ ልማድ መዋጋት አለበት። አንድ ታሪክ ጸሐፊ እውነተኛውን ታሪክ ለመፃፍ ካልቻለ ቢተወው ይሻላል። ሐሰት ሰውን እንደሚያጠፋ፣ እውነተኛ ያልሆነ ታሪክ ሀገርን ያጠፋልና!

እኔም በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ከህዳር 27 ቀን 1927 ዓ.ም እስከ ህዳር 19 ቀን 1934 ዓ.ም የተካሄደውን ጦርነት ለመፃፍ የተነሳሳሁበት በዚህ መንፈስ ተመርቼ እውነተኛውን ነገር ለኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ለመግለጽ ነው። ታሪክን መመርመር ይጠቅማል። ሲመረመርም አረረ መረረ ሳይሉ እውነተኛውን ነገር ማበጠር ያስፈልጋል። የሀገሩን ታሪክ ያላወቀ ዜጋ በጭለማ እንደሚጓዝ ሰው ነው። እርስዎም በታሪክ ብርሃን ለመጓዝ ይሞክሩ።

ይቅናዎ
ተድላ ዘዮሐንስ ዘውዴ
ታህሣሥ 1986 ዓ.ም
አዲስ አበባ።

# ምዕራፍ አንድ
## ኢትዮጵያ ከአድዋ እስከ ማይጨው

ተደጋግሞ በታሪክ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ ዓለምን ረስታ፣ ዓለምም እርስዋን ረስቶአት ወደ ሦስት መቶ ዓመት ኖረች፡፡ ከዚህ ረጅም የእንቅልፍ ዘመን በአፄ ቴዎድሮስ (ግ.1847-1860ዓ.ም) ተቀሰቀሰች፡፡ ስትነቃም ራስዋን ከአውሮፖ ሀገሮች በጣም ወደ ኋላ ቀርታ አገኘችው፡፡ ይህ ኋላ ቀርነት ለሕልውናዋ አስጊ መሆኑን ተገነዘበች፡፡

በዘመነ መሣፍንት ተከፋፍሎ የነበረውን የግዛት አንድነትዋን እንደገና መልሶ ለመያዝ ሞከረች፡፡ የአውሮፖ ሥልጣኔ በፍጥነት ወደ ሀገርዋ ለማስገባት ተጣጣረች፡፡ ጉዞዋ የሰመመን ሆነባት፡፡ ከዚህም የተነሣ ብዙ መደንቃቀፍ ደረሰባት፡፡ አፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያን አንድነት ለመመሥረት ሞከሩ፡፡ ቱርኮችን ከአካባቢያአቸው ለማስወጣት፣ ኢየሩሳሌምን ለማስለቀቅ ተመኙ፡፡ መድፍና ጀልባ ማሰራት ጀመሩ፡፡[1] በስተኋላም አመለካከታቸው ወደኃይል አዘነበለ፡፡ ይህ ደግሞ አውሮፖን አስገነገነ፡፡ የሃይማኖት ሰባኪያን እያስመሰሉ በላኩአቸው ሰዎች ምክንያት ከእንግሊዞች ጋር ግጭት ተፈጠረ፡፡ ለጥፋታቸውም መንስኤ ሆነ፡፡

ንጉሥ ተክለጊዮርጊስ (ግ.1861-1863 ዓ.ም ) ከደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ከተነሳባቸው ግጭት ፋታ ሳያገኙ ወደቁ፡፡ ደጃዝማች በዝብዝ ካሣ ደግሞ አራተኛ ዮሐንስ (ግ.1863-1880ዓ.ም) ተብለው ዘውድ ከተቀዳጁ በኋላ የሀገሪቱን አንድነት ለመገንባት ሞከሩ፡፡ ነገር ግን አመለካከታቸው ከሃይማኖት ልዩነት ላይ ስለአተኮረ የእስላሙን ኃይል ቀሰቀሰባቸው፡፡ እንግሊዞችም ለጥቃት አጋለጡአቸው፡፡ ምፅዋን ለኢጣልያ እጅ አዛውረው ሰጡባቸው፡፡ ክርስቲያኖች በመሆናቸው ይረዱኛል ብለው ሲታመኑ፣ የእስላሙን ኃይል አስነሱባቸው፡፡ መተማ ወድቀው ቀሩ፡፡[2]

የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት እ.ኤ.አ. በ1885 ዓ.ም በበርሊን ከተማ ተሰበሰቡ፡፡ የተሰበሰቡት ምክንያት አፍሪካን እንደምን እንደሚከፋፈሉ ለመቀየስ ነበር፡፡ ንግግሩ ያተኮረው "እንደምን" በሚለው ጥያቄ ላይ ብቻ ነበር፡፡ "ለምን" የሚለው ጥያቄ ጉዳያቸው አልነበረም፡፡ አህጉሪቱን በመላ በቅኝ ገዥነት መያዝ መፈፀም ያለበት እንጂ የሚያከራክር ጉዳይ አልነበረምና፡፡

በዚህ ውሣኔ መሠረት አውሮፓውያን አፍሪካን ተቀራመጡአት፡፡ ድርሻቸውም በ1906 ዓ.ም

- የፈረንሣይ ከመቶ 34 እጅ፤
- የእንግሊዝ ከመቶ 32 እጅ፤



- ጀርመን ከመቶ 7 እጅ፤
- ቤልጂግ ከመቶ 7 እጅ፤
- ፖርቹጋል ከመቶ 6 እጅ፤
- ኢጣልያ ከመቶ 5 እጅ፤
- ስፔይን ከመቶ 7 እጅ፤
- ነፃ መንግስታት ከመቶ 2 እጅ ሆነ፡፡

ይህ ሚዛን የኢጣልያን ክብር የሚቀንስ ሆነ፡፡ የሊቢያ፣ የሶማልያና ከኤርትራም ምድር አብዛኛው በረሃማ ሆነባት፡፡ ስለዚህ ዓይንዋን በኢትዮጵያ ላይ ጣለች፡፡

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ይህንን ሁኔታ ቀደም ብለው ደርሰውበት ነበር፡፡ መፍትሔ አድርገው የተከተሉት ዘዴ በግራኝ ወረራ ተከፋፍሎ ተይዞ የነበረውን ደቡባዊውን የአገሪቱን አካባቢዎች መልሰው መያዝ ሆነ፡፡ እንደዚሁም አደረጉ፡፡ አዲስ አበባንም ቆረቆሩ፡፡ ሰሜኑን ደግሞ በመለማመጥና እርስ በርሱ በማስማማት ያዙት፡፡ የአሁንዋን ኢትዮጵያ መሠረቱ፡፡ ጣልያንን አድዋ(በ1888 ዓ.ም) ላይ ድል በመምታት የሀገራቸውን ነፃነት አረጋገጡ፡፡ ነገር ግን ቀደም ብለው በቅኝ ገዥዎች እጅ የወደቁትን የባህር በሮች፤ ማለትም ኤርትራንና ደቡብ ሶማልያን ከኢጣሊያ፣ ሰሜን ሶማልያን ከእንግሊዝ፣ ጁቡቲን ከፈረንሣይ ማስለቀቅ የማይቻላቸው ሆነ፡፡ የሕዝቦቹም ስሜት ተከፋፈለባቸው፡፡ የቅኝ ገዥዎቹ ኃይል አየለባቸው፡፡ የተረፈውን፣ የቀረውን ሕዝቤን ባድን ይሻለኛል አሉ፡፡ መተናነቃቸውን ትተው ከአውሮፓ መንግሥታት ጋር ተስማሙ፡፡

በዓለም ፊት ኢትዮጵያ አሸናፊ፣ ኢጣልያ ተሸናፊ ሆነው እንደማይቀሩ ለብልሁ ለአፄ ምኒልክ ግልፅ ነበር፡፡ ሌላ ፍልሚያ መካሄድ እንደ አለበት ታውቆአቸዋል፡፡ ልዩ ልዩ መሣሪያ አስመጥተው ከረማሽ አስቀመጡ፤ የጥይት ፋብሪካ አቋቋሙ፡፡[3] በእንግሊዝና በፈረንሣይ ሴራ ቀረባቸው እንጂ፤ ጠመንጃ መስሪያ ፋብሪካ ለማቋቋምም ሞክረው ነበር፡፡[4]

ከእሳቸው በኋላ ጦርነቱ እስኪነሣ ድረስ በነበረው ጊዜ ግን ሀገርን በመከላከል ረገድ አንዳች የረባ ነገር አልተደረገም፡፡ ለጥቅምና ለሥልጣን በተደረገ ሽኩቻ ያ ሁሉ ዘመን በከንቱ አለፈ፡፡ በዚህ ጉዳይ ያን ጊዜ ባልሥልጣኖች የነበሩ ሁሉ በታሪክ ፊት ተወቃሽ ናቸው፡፡ ተወቃሽነታቸውም እንደ ደረጃቸውና እንደቅደም ተከተላቸው ይሆናል፡፡ ዋናው አቤቶ ኢያሱ ናቸው፡፡ ከአያታቸው ከአፄ ምኒልክ የተሰጣቸውን አልጋ በሥርዓት አለመያዛቸው በእሳቸው በራሳቸው ላይ ጥፋትን፣ በሀገሪቱ ላይ ውድቀትን፣ በሕዝቡ ላይ መንገላታትንና እልቂትን አስከተለ፡፡ ዋና ዋና ስህተቶቻቸው፡-

1. አፄ ምኒልክን ራሳቸው በሕይወት እያሉ ከአልጋ ለማውረድ መሞከር፣ የሞቱ ዕለት ጉግስ ማጫወት፤[5]
2. የሀገሪቱን ሥርዓት፣ የቤተክርስቲያኒቱን ደንብ አለማክበራቸውና በቅብዐ ቅዱስ ዘውድ አለመቀዳጀት፤
3. በክርስትና ፅንአት በማሳየት ፈንታ ወደ እስልምና ወገን ማዘንበል፤
4. የአፄ ምኒልክን አሽከሮች በሥርዓትና በአክብሮት አለመያዝ፤
5. ሴሰኝነትና ዘራቸውን በየትም መርጨት፤
6. የመንግሥቱን ሥራ በጥሞና በማካሄድ ፈንታ ዙረት ማብዛት፤
7. በአውሮፓ ተቀስቅሶ ከነበረ ጦርነት ጋር በተያያዘ፤ ከማያስፈልግ ንትርክ ውስጥ በመግባት ከቱርክ እና ከጀርመን ጐን መቆም ናቸው።[6]

ቀጥሎ ተጠያቂ የሚሆኑት እቴጌ ጣይቱ ብጡል ይሆናሉ። እቴጌ ጣይቱ ለኢትዮጵያ ታላላቅ ውለታዎች ሰርተዋል። ነገር ግን ሥልጣን በመፈለግ በቤተመንግሥቱ ነገር በመዝራት በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ሕመም ላይ ሀዘን መጨመራቸው፣ የአቤቶ ኢያሱን ባህርይ በመጥፎ ነገር በመበከል ማበላሸታቸው የውለታቸውን ያህል በድለዋል።

የዳግማዊ ምኒልክ አሽከሮችም ኃላፊነታቸውን በሚገባ አልተወጡም። ራስ ተሰማ ሥራቸውን በተገቢ መንገድ ባለመፈፀማቸው ከጥፋት ደረሱ። ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ በአነስተኛ ጉዳይ በአቤቶ ኢያሱ በመቀየም መሐላቸውን አፍርሰው የጌታቸውን የምኒልክን ሥርወ መንግሥት ከሚለውጡ ጋር ደባ ውስጥ መግባታቸው የሚነገርላቸውን ያህል አስተዋጽኦ ያደረጉ እንዳልነበሩ ያስረዳል።

በታሪክ ፊት ደጃዝማች ተፈሪ መኰንንም /ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ/ ከተጠያቂነት አይድኑም። የንጉሥ ሣህለሥላሴ ተወላጅ ይሁኑ፣ ያፍሩአቸው እንጂ አልጋውን በአግባቡ አልወረሱም። በእርግማንና በግዝት አልጋ የተሰጠው ከሣህለ ሥላሴ ለንጉሥ ኃይለ መለኮት፣ ከአፄ ምኒልክ ደግሞ ለአቤቶ ኢያሱ ነው። እሳቸው ራሳቸውም ቢሆኑ ከልጅ ኢያሱ ጋር የገቡትን ቃል ኪዳን አልጠበቁም። ለዚህም የሰጡት ምክንያት ልጅ ኢያሱ ቃል ኪዳናቸውን አፈረሱ የሚል ነው።[7] ማንኛቸው ቃል ኪዳን እንደ አፈረሱ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ሐቁ ግን ደጃዝማች ተፈሪ በልጅ ኢያሱ የተቀሰቀሰውን ነገር ለሥልጣን ሲሉ ማባባሳቸው ነው።

በዚህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንም ከተወቃሽነት አትድንም። በወቅቱ ዘውዱን የምትጠብቅ ብሔራዊ ቤተክርስቲያን ናት። የንጉሥ ሣህለሥላሴንም፣ የዳግማዊ ምኒልክንም ቃል በግዝት ያፀናች እርስዋ ናት። የዘውድ አወራረስ ተፋለስ የሚያስከትል ነገር ሲፈፀም ዝም ማለት አልነበረባትም። ነገር ግን ደጃዝማች ተፈሪ መኰንን



ራስ ተብለው አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ መሆናቸውን ደገፈች።[8] ምንም እንኳ የልጅ ኢያሱ ከሥልጣን መውረድ የማይቀርና ተገቢ ቢሆን፤ የአልጋ ወራሹ ምርጫ ቢቆይ ይሻል ነበር። ምክንያቱም የአልጋ ወራሽነት ሹመት ከንጉሡ ላልተወለደ የማይሠጥ ሲሆን፤ ከዚህም በስተቀር የባለሙሉ ሥልጣን ማዕረግ ተሰጥቶ አያውቅም ነበርና።

አፄ ምኒልክም ራሳቸው ተሳስተዋል። ስህተታቸውም በልጃቸው ልዕልት ዘውዲቱ ላይ የፆታ ልዩነት ማድረግ ነው። ያንን ያህል ደክመው አንድ ያደረጉአትን ሀገር፤ ለኃላፊነቱ አስተማማኝ ላልነበረ ወጣት ለአቤቶ ኢያሱ መጣል አልነበረባቸውም። በውጭ አገር እነ ንግሥት ቪክቶሪያንና ኤልሣቤጥን፣ በኢትዮጵያ እነ ንግሥት ሳባን፣ ማክዳን፣ ሰብለ ወንጌልን፣ አጠገባቸውም እቴጌ ጣይቱን አጢነው ዘውድን ለልጃቸው ለዘውዲቱ በሰጡአቸው በቀለለ ነበር።

ይህ ሁሉ አልሆነም። አልጋው ተነቃነቀ። የተሻለው አማራጭ ልዕልት ዘውዲቱን ማንገሥ፣ ደጃዝማች ተፈሪን ደግሞ ራስ ብሎ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ማድረግ ሆነ። ነገር ግን ይህ ቅንጅት ሥምረት አጣ። ውዝግብ ፈጠረ።[9] የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት ቀነሰ። ሀገሪቱን ለውጭ ጥቃት አጋለጣት። አፄ ምኒልክ "ነፋስ አይግባባችሁ" ያሉት ምክር አድማጭ አጥቶ የፈሩት ደረሰ።

የኢትዮጵያን ቅጥ ማጣት በትኩረት ይመለከቱ የነበሩት ጠላቶችና ዋና ተቃዋሚዎች ተንቀሳቀሱ። እንግሊዝና ኢጣልያ ሲያውጠነጥኑ የቆዩትን ሤራ አጠናከሩባት። ሮማ ላይ ተነጋግረው እንግሊዝ በጣና ባሕር ላይ ግድብ ስትገድብ፤ ኢጣልያ ከአሥመራ እስከ ሞቃድሾ በኢትዮጵያ ግዛት ላይ አቋርጣ የባቡር ሀዲድ ልትዘረጋ ተስማሙ። ውሉንም ከዓለም መንግሥታት ማህበር መዝገብ ቤት አገቡ።[10] ከኢትዮጵያ መንግሥት የቀረበውን ተቃውሞ ከቁም ነገር የቆጠረው የለም።

የኢትዮጵያ ሁኔታ በእንዲህ እንደአለ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተነሳ። ምንም ውጊያውን ያካሄዱት እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና መስኮብ አንድነት ሆነው በጀርመን ላይ ቢሆን፤ በወቅቱ ቱርክ ከጀርመን ጐን፣ የልጅ ኢያሱ ኢትዮጵያ ደግሞ ከቱርክ ጐን ቆመው ነበር። ኢጣልያ መጀመሪያ ከጀርመን ጐን እንደሆነች መስላ ከቆየች በኋላ፤ ሚዛን ሲያደላ አቋሟን ለውጣ ከእንግሊዝና ፈረንሣይ ጐን ቆመች። ጦርነቱ በእንግሊዝና በፈረንሣይ አሸናፊነት ሲደመደም፤ ቀደም ብሎ ተጀምሮ ፈር ሳይዝ የቆየው የዓለም መንግሥታት ጉባኤ በሰኔ ወር 1911 ዓ.ም (ጁን 1919) ተቋቋመ። በዚህ ወቅት በተቀናቃኞቻቸው ላይ የበላይነት የያዙት አልጋ ወራሽ ተፈሪ፤ ኢትዮጵያ የኃያላንን ጥቃት መመከት የምትችለው ከጋራ

ጸጥታ ከለላ ስታገኝ ነው ብለው አመኑ። ኢትዮጵያም የእንግሊዝን ተቃውሞ በኢጣልያ ድጋፍ አክሽፋ በሚያዝያ ወር 1915 ዓ.ም የማሕበሩ ሃያ ስምንተኛ አባል ሆነች።[11]

ከአሥር ዓመታት በኂላ ኢጣልያ የማህበሩን ውል ጥሳ በኢትዮጵያ ላይ የወረራ እንቅስቃሴ አነሣች። በኢትዮጵያ ወገን ስሞታ ከማቅረብ በስተቀር ራስን ለመከላከል እንዳች አልተደረገም። ይኸኛውም የሀገር ተከላካይነቱ ሥራ የነፍጠኛው ሆነ። የያዘው መሣሪያ በአድዋ ጊዜ የማረከው ነው። ከእሱም አብዛኛው ስናድር፣ ናስማር፣ ውጅግራ ነው። በአንድ ጊዜ ከአንድ ጥይት በላይ አይተኩስም፣ ይግላል፣ ቀለሁም ከውስጡ ይጎረዳል፤ ጭሱም ከባድ ነው። ለረጅም ጊዜ በተካሄደው የሥልጣን ሽሚያ ደግሞ ነፍጠኛው ተንገላትቶአል። በልጅ ኢያሱና በንግሥት ዘዉዲቱ ላይ በደረሰው ነገር ቆስሎአል። በአዲሶቹ መሪዎች አልተደሰተም። የማደሪያ መሬቱ እየተነቀለ ለአዳዲሶች ሹማምንት ባለሙዋሎች ተሰጥቶበታል።

በአንፃሩ ደግሞ የአዳዲሶች ባለሥልጣኖች ጦር የውጊያ ብቃት አልነበረውም። የልብ አንድነትም አላገኘም። በውልድ እና በዝምድና፣ በአምቻ በጋብቻ የተመለመለ እንጂ በመከራ የተፈተነና የጦር ልምድ ያካበተ አልነበረም። አዲሱን የሠልፍ ትምህርት ተምሮ፣ በአንድ አይነት አረማመድና በአንድ ዓይነት ልብስ አምሮ በተመልካች ዘንድ ደስ እንዲያሰኝ የሰለጠነ ነበር። ቁጥሩም እጅግ ጥቂት ነበር።[12] በዚህ ላይ ደግሞ የርስበርስ መናናቅና አንዱ ለአንዱ አልታዘዝም የማለት ሁኔታ ነበር። የኢትዮጵያዊ ዓይነት ቅርፅ አልነበረውም። የእነዚህ ሁኔታዎች ድምር የሀገሪቱን አቅም አሳነሰ። የሕዝቡን አንድነት ቀንሶ አገሪቱን ከጠላት ለተሠነዘረባት አደጋ አጋለጣት።




<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ አንድነት* ፤ገፅ 297።
2. ዝኒ ከማሁ።
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *አጤ ምኒልክ*፣ ገጽ 355።
4. ካፒቴን ሐሪስ
5. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት*፤ገጽ 55።
6. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ*፣ *1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 31።
7. ዝኒ ከማሁ፤ገጽ 27-29።
8. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 141።
9. ከበደ ተሰማ፣ የታሪክ ማስታወሻ፤ገጽ 44-73።
10. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 101-105።
11. ክፍለ ጽዮን ማሞ፣ ማለ መጽሔት አንደኛ አመት ቁጥር 2 ጥር 1985 ዓ.ም
12. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ገጽ 57-58።

## ምዕራፍ ሁለት

## ኢጣልያ ከውህደት እስከ ማይጨው ዋዜማ

የጣልያንን ሁኔታ ደግሞ በአጭር ማየት አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣል። እስከ አስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ድረስ፤ ኢጣልያ በልዩ ልዩ መሣፍንት የተከፋፈለች ሀገር ነበረች። ክፍፍሉሹ እስከ ሠላሣ ስምንት ይደርስ እንደነበረ ይነገራል። በዚህ ላይ ደግሞ በዚያን ጊዜ ገናና የነበረው የነምሣ(ኦስትሪያ) እንዲሁም የፈረንሳይ መንግስት ተፅዕኖ ነበረባት።

የሰርዲኒያው መሥፍን ካርሎ አልቤርቶ ይህንን ክፍፍሉሽ ለማስቀረትና ሀገሪቱን ወደ አንድነት ለመጠቅለል ሞከረ። እምብዛም ሳይቀናው ሞተ። ልጁ ዳግማዊ ንጉሥ ኢማኑኤል (ግ.1841-1870 ዓ.ም) ፈሩን ተከትሎ ከዳር አደረሰ። በጀርመንና በነምሣ፣ ቀጥሎም በጀርመንና በፈረንሣይ መንግሥታት መካከል የተካሄደውን ጦርነት በመጠቀም፤ በጳጳሱ ላይ ተፅዕኖ አድርጐ በ1862 ዓ.ም ሮማን መናገሻ ከተማው አደረገ።[1] ኢጣልያም የተዋሃደች ሀገር ሆነች።

ኢጣልያ የውስጥ ጉዳይዋን በዚህ አይነት ከቋጨች በኋላ አውሮፖን ስትመለከት በቅኝ አገዛዝ ረገድ ባዶ እጅዋን ቀርታ አገኘችው። ነገሩ አስደንጋጭ ሆነባት። እንግሊዝ ሰሜን አሜሪካን፣ ከአፍሪካ ደግሞ ከመቶ 32 እጅ፣ መካከለኛውን ምሥራቅ፣ ደቡብ እስያንና ደቡብ ምሥራቅ እስያን፣ አውስትራልያንና ኒውዚላንድን ትገዛለች። ፈረንሣይ ከካናዳ አንዱን ወገን ትቆጣጠራለች፤ ከአፍሪካም ከመቶ 34 እጅ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅም ደህና ድርሻ አግኝታለች። ሌሎችም እንደዚሁ የተቻላቸውን ያህል ቀንጥረዋል። በዚህ ሁኔታ ላይ የነበረችው ኢጣልያ ዓይንዋን በኢትዮጵያ ላይ ጣለች። የአውሮፖ መንግሥታትንም አግባባች። እንግሊዞች ለአፄ ዮሐንስ የገቡትን ቃል ኪዳን ጥሰው ከግብፅ የነጠቁአትን ምፅዋን 1877 ዓ.ም መጨረሻ ለገሡአት። አሰብን አስቀድማ በገንዘብ ገዛች። ሶማሊያን ከየባላባቱ በመስማማት ያዘች።

ነገር ግን ይህ ሁሉ በረሃ መሰብሰብ እንጂ የሚያረካት ሳይሆን ቀረ። ኢጣልያ ከየአቅጣጫው ጉዞዋን ወደ ማሕል ኢትዮጵያ አቀናች። የያዘቻቸውን ቦታዎች መረማመጃ አደረገች። ለዚህም በኤርትራ በኩል ያለው ይበልጥ ገር ሆነላት። ወታደሮቿ ከበረሃው ወጥተው ደጋውን ሐማሴንን፣ ሠራዬንና አካለ ጉዛይን ያዙ። ከዚያም ወደ ትግራይ ተሻገሩ። ከተደጋጋሚ ግጭት በኋላ አድዋ ላይ በ1888 ዓ.ም ኢጣልያ ተሸነፈች። የአድዋ ጦርነት ለኢጣልያ የሃፍረት ማቅ አልብሶ ለኢትዮጵያ ነፃነትዋን



አጐናጸፋት። አድዋ፣ በቅኝ ግዛት ለወደቁ ሕዝቦች ሁሉ መልካም ምሳሌ ሆነ።

ከአድዋ ጦርነት በኋላ የኢጣልያ ሁኔታ ችግር የበዛበት ሆነ። ውርደቱ በመግደርደር የሚሸፈን አልነበረም። የጦር ጉዳተኞችን መልሶ ማቋቋም፣ ኢትዮጵያን ተለማምጦ ምርኮኞችን ማስለቀቅ ግድ ነበር። የሊቢያ ጦርነት ፋታ አልሰጠም። የኤርትራና የሶማልያ ቅኝ ግዛቶችም የሚያረካ ጥቅም አላስገኙም።

ይህ በእንዲህ እንደአለ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ተቀሰቀሰ። ኪያዮች በተባለች አንዲት ትንሽ የቻይና መሬት ምክንያት የተነሳው ጠብ ጃፓንና ጀርመንን አፋጠጠ። ውሎም ሳያድር በጀርመንና በራሽያ መካከል ጦርነት ተነሳ። እንግሊዝና ፈረንሣይ ጥቅምት 25 ቀን 1907 ዓ.ም (ኖቬምበር 1914) ከጦርነቱ ገቡ።

ለኢጣልያ ይህ ሁኔታ አስቸጋሪ ሆነባት። ገለልተኛ መሆን አልቻለችም። መጀመሪያ ወደ ጀርመን አዘነበለች። የማያዋጣት ሲሆን ግንቦት 17 ቀን 1907 ዓ.ም (ሜይ 1915) ከጦርነቱ ገባች። ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጐን ለመቆም የወሰነችው ከኦስትሪያ ጥቂት ቦታ ተቦጭቆ እንደሚሰጣት፣ ከቱርክ ግዛትም ድርሻ እንደምታገኝ፣ በአፍሪካ ምድር ቅኝ ግዛት ለማስፋፋት እድል እንደሚኖራት ለንደን ላይ ቀደም ብሎ በተደረገ ንግግር ቃል ስለተገባላት ነበር።[2]

- በአውሮፓ ደግሞ የነበረውን አገዛዝ የሚሽር፣ አዳዲስ አስተዳደር የሚመሠርት ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ተጀመረ። ኮሚኒዝም በራሽያ፣ ናዚዝም በጀርመን፣ ፋሽዝም በኢጣልያ ሥልጣን ያዙ። እነዚህ ንቅናቄዎች ለሕዝቦቻቸው አርነት፣ ለሀገሮቻቸው አክብሮት፣ ለርእዮተ ዓለማቸው ጽንአት የሚያስገኙ ሥራዎች በመሥራት የሕዝብን እምነት ማግኘት ነበረባቸው። ሁሉም በየበኩላቸው እንደዚሁ አደረጉ።

በኢጣልያ የተካሄደው የፋሽስት አብዮት በቢኒቶ ሙሶሎኒ መሪነት በ1915 ዓ.ም (1922) ለሥልጣን በቃ። በ1915 ዓ.ም ገና ከሥልጣን ላይ እርካብ ለወጣው ለሙሶሊኒ ቀደም ብላ ኢጣልያ የገባችበት ስምምነት አላረካውም። በጦርነቱ ፍፃሜ ያገኘችውም ፀጋ በቂ መስሎ አልታየውም። በቬርሳይ ቤተ መንግሥት በተደረገው የሰላም ጉባኤ ላይ ኢጣልያ አክብሮት ሳታገኝ ቀረች። በጄኔቫ የዓለም መንግሥታት ማህበር ሲቋቋም አባል ሆነች። ነገር ግን በክብር አልነበረም፤ በቀዝቃዛ ስሜት እንጂ። የጣልያን ህዝብ ሮማውያን በአካባቢያቸው የነበሩ ሀገሮችን ይገዙበት በነበረ መንፈስ፤ ይህንን ዓይነቱን ስሜት ተቀብሎ በትዕግስት መኖር አቃተው።

በዚያውም ላይ የፋሽስት ደም ጠማሽ አመለካከት ሰፈነበት። ዕለት ዕለት የሚሰማው የሙሶሊኒ ቅዠት ዕረፍት ነሳው።

ማንኛውም ሕዝብ የራሱ የሆነ ባሕርይ፣ ወግና ሥርዐት እንደ አለው ሁሉ፤ የኢጣልያም ሕዝብ የበኩሉ አለው። ጠንካራ ሠራተኛ ነው። በተለይም በምህንድስና ሥራ ጉበዝ ነው። በመንገድና በሕንፃ ሥራ የሚተካከለው ያለ አይመስልም። በሕግ ማሰብና የመተዳደርን ሁኔታ ለዓለም ያበረከተ እሱ ነው። ነገር ግን አስተዳደርን እና ፖለቲካን በተመለከተ ገና ብዙ ይቀረዋል። አንዳንድ ባሕርያቱ የአስተዳደር እንዲሁም የፖለቲካ ሥምረት ሊያስገኙለት የሚችሉ አይደሉም። ለምሣሌ ችኩል፣ ቁጡ፣ ለፍላፊ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የመንፈስ እርካታ የለውም። የአስተዳደርና የፖለቲካ ሥራ ደግሞ ትዕግስት፣ ዕርጋታ፣ ጭምትነት ይጠይቃል። ባገኘው ለማይረካ፣ ማጣትና ማግኘት ልዩነት የላቸውም።

አዲሱ የፋሽስት መንግሥት ልዩ ልዩ ችግሮች ቀስፈው ያዙት። የፖለቲካ ቡድኖች ብዛት የማይቀንስ፣ የአስተያየታቸው ልዩነት የማይታረቅ ሆነበት። ሥራ አጥነት ጠነከረ። የሕዝቡ የዴሞክራቲክ አስተዳደር ፍላጎት የማያፈናፍነው ሆነ። የኢንዱስትሪ፣ የልማት ሥራዎች የመስፋፋታቸው ጉዳይ ዳተኛ ሆነበት። ብሔራዊ ስሜት እየጐለበተ ሄደ። የጳጳሱና የንጉሡ ተፅዕኖ ከበደው። የዓለም መንግሥታት ንቀት ጣሊያኖችን አናደዳቸው። [3]

በእነዚህ ሁኔታዎች ተቀስፎ የተያዘው ሞሶሎኒ ዓይነ ልቡናውን በኢትዮጵያ ላይ ጣለ። ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛትነት መያዝ ብዙ ጉዳይ የሚተኩስለት መስሎ ታየው። የአድዋን ቂም መበቀልና የጣልያንን ክብር ማደስ፣ ሰፊና ለም የቅኝ ግዛት ይዞ የወደቀውን ኢኮኖሚ መገንባት የሚቻለው ኢትዮጵያን በመያዝ መሰለው። በርእዮተ ዓለም ረገድ ለተቅበጠበጠው የኢጣልያ ሕዝብ አዲስ የሰፈራ ቦታና የሥራ እድል መስጠት፣ በዓለም ፊት ሞገስ ማግኘት፣ የሕዝቡን ብሔራዊ ስሜትና አንድነት ማፅናት፣ የእሱን የራሱን ክብር ከፍ ማድረግና የፋሽስት ፓርቲን ርዕዮተ ዓለም መገንባት የሚችለው ኢትዮጵያን በመያዝ መሰለው።

የኢጣልያ ሕዝብ በወቅቱ ነባራዊ ክስተቶች ስሜቶቹ ተቀሰቀሱበት። ወደ ቀድሞ ትልቅነቱ በታሪክ ተመለከተ። በጐ ስሜቱን የሚያጐለብት እና መጥፎ ስሜቱን የሚገታ መሪም፣ መካሪም አላገኘም። ከቤኒቶ ሙሶሊኒ ቅዠት ውስጥ ገባ። ንጉሡም፣ ጳጳሱም አብረውት ገቡ። መኳንንቱ ንጉሡን፣ ካህናቱ ጳጳሱን ከመከተል በስተቀር ሌላ መንገድ አልነበራቸውም። ሙሶሊኒ አዲስ ባቋቋመው የፋሽስት ርዕዮተ ዓለም



ወጣቱን አሰከረው። የእሱን ሐሳብ የሚከተሉትን እየመለመለ ካድሬ አደረጋቸው። በእናት ሀገር ውድቀት ያዘኑ ለማስመሰል ጥቁር ሸሚዝ አለበሳቸው። ነገር ግን ይህ ጥቁር ልብስ መጥፎ ግብሩን እንደሚያመለክት የተረዳ፣ ከዚያም ለመመለስ የሞከረ አልነበረም። በሐሳቡ ባልተስማሙት ላይ ተፅዕኖ አደረገ። የፖለቲካ መሪዎችንም አሰረ። ከጥቂቶች በስተቀር የኢጣልያ ሕዝብ ተከተለው።[4]

ሞሶሊኒ ይህንን ዓላማውን በሥራ ለመፈፀም የሚችልበትን መንገድ መቀየስ ጀመረ። አንዱ ተግባሩ የጦር መሣሪያ መሥራት፣ ሊሠራው ያልቻለውን መግዛት፣ ወታደር ማሠልጠንና ወደ ኤርትራና ሶማልያ ማጓጓዝ ሆነ። የጦር መሣሪያ የሚሠሩ ፋብሪካዎች በብዛት ተቋቋሙ። በአንድ ጊዜ ስድስት ጥይት የሚጐርሱና በየተራ የሚተኩሱ የምንሽርና የአልቤን ጠመንጃዎች ከነሳንጃና ከነጥይታቸው በብዛት ተሰሩ። ሃያ ጥይት ጐርሶ በአንድ ጊዜ የሚተኩስ መትረየስ፤ እንዲሁም ከምድርና ከአየር የሚተኮስ የውሃ መትረየስ ተሠራ። ከሁሉም በላይ አስተማማኝ የሆነው ታንክ ነበር። ሌላው ዝግጅት በቦምብ ረገድ ነበር። በእጅ የሚወረወር፣ ከጠመንጃ አፈሙዝ እየተገጠመ የሚተኮስ፣ ከሰማይ በአይሮፕላን የሚጣል የቦምብ ዓይነቶች ተዘጋጁ። ብዛት ያላቸው አይሮፕላኖች ተሠሩ። ይህም የማይበቃ ሆኖ ከአይሮፕላን የሚረጭ የጋዝና የኤፐሪት መርዝ በፈሳሽ መልክ ተዘጋጀ።

ወታደር ተመለመለ፣ ሰለጠነ። ከኢጣልያ፣ ከኤርትራና ከሶማልያ ብዙ ወታደር ተደራጀ። ብዛት ባይኖረውም ከሊቢያ ተመለመለ። በምድር ጦር፣ በአየር ኃይልና በባሕር ኃይል በኩል ሙሉ ዝግጅት ተደረገ። የዱቼ ሙሶሊኒ ልጅ ቪቶርዮ ሙሶሊኒ ራሱ በአየር ኃይል መኰንንነት ሰለጠነ። ነገር ግን ወደ ኢትዮጵያ የመምጣት ዕድል ሳያገኝ በስፔይን ጦርነት ከአይሮፕላን ጋር ወድቆ ሞተ።

ሞሶሊኒ የማጓጓዣ መኪናዎች አዘጋጀ። ካሚዮን በየአይነቱ አሠራ። ለጦር መኰንኖች እርዳታ አውቶሞቢል፣ ለኢጣልያውያን ሠራተኞች ሞተርሳይክሎች አዘጋጀ። በኢትዮጵያ በረሃማ፣ ደጋማና ተራራማ ቦታዎች ዕቃ የሚያጓጉዙ እስከ 50 ሺህ የሚገመቱ አህዮች፣ አጋሰሶችና ግመሎች አዘጋጀ። የኢትዮጵያን የመሬት አቀማመጥ፣ የወንዞችን አፈሳሰ፣ የአየር ንብረቱን ፊት ለጦርነት፣ ኋላ ደግሞ ለልማት ሥራ እንደሚበጀው እያስደረገ አስጠና። በዚህ ሁሉ ዓለም ተባበረው፤ የስዊዝ ካናል ክፍት ሆነለት።

ሌላው ትኩረቱ የኢትዮጵያን የውስጥ ሁኔታ በማጥናት መሪዎቹንና ህዝቡን መከፋፈል ሆነ። የመኳንንቱንና የመሣፍንቱን ልቡና

በጥቅምና በሥልጣን እየደለለ የኢትዮጵያን ምስጢር በዘበዘ። ልባቸውን ከፋፈለ። ህዝቡንም በኃይማኖት፣ በጎሣ ማቃቃር ያዘ። ኢትዮጵያ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሬዲዮ የምታስተላልፈውን መልእክት እየጠለፈ የሚያደምጥበት መሣሪያ አዘጋጀ። በዚህም ሚሲዮናዉያን፣ የዲፕሎማቲክ ሠራተኞችና ነጋዴዎች ተባበሩት።

ሞሶሎኒ የጦር ትጥቁን ከማዘጋጀት ጋር የኢጣልያን ሕዝብ ሥነ ልቡና ለጦርነቱ ማነሳሳት ያዘ። የጣልያንን ቁጭትና ጥቅም የሚያዳብሩ፣ የኢትዮጵያን ስም የሚያጉድፉ ወሬዎች በሕዝብ መገናኛዎች ነዛ። ዓላማውን ለሕዝብ አስረዳ። የጦርነቱን ግቦች በይፋ አስታወቀ። ከእነሱም ዋና ዋናዎቹ፡

1. ታላቅና ለም የቅኚ ግዛት በመያዝ የጣልያንን ኢኮኖሚ ማዳበር፤
2. ኢትዮጵያን ከኤርትራና ከሶማሊያ ቅኝ ግዛቶች ጋር በመቀላቀል ቦታ የጠበበውን የጣልያንን ሕዝብ አምጥቶ ማስፈር፤
3. ለኢጣልያ ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃና የሰው ኃይል፣ ለምርታቸው ገበያ ማስገኘት፤
4. በአድዋ ጦርነት የተዋረደውን የጣልያንን ክብር በአዲስ ድል ማደስ፤
5. ኢጣልያ በዓለም ኅብረተሰብ ዘንድ አክብሮት እንድታገኝ ማድረግ ነበር።

ከዚህም በተጓዳኝ የዓለምን አመለካከት ወደ እሱ ለመመለስ ልዩ ልዩ ጥረት አደረገ። ምነው ባይ እንዳይነሳና ዓላማውን እንዳያከሽፍበት፤ በተለይ የአውሮፓ መንግሥታት ተቃውሞ እንዳያነሱበት፤ እንደየጥቅምና ጉዳያቸው እየሸነገለ አስተባበረ። ጥረቱ ሁሉ ሠመረለት። ሙሶሊኒ አስቦ የሚሰራ እንጂ፣ በስመመን የሚንቀሳቀስ ሰው አልነበረም። የአድዋ ውርደት ተመልሶ እንዳይደገም ተገቢውን ጥንቃቄ አደረገ። ለጦርነቱም መሪዎች የሚሆኑት በጥንቃቄ ተመረጡ። ሰብዓዊ አመለካከት ይታይባቸው የነበሩትን አስወጣ። ለዘብተኛውን ጄነራል ደቦኖን ሽሮ፤ መጀመሪያ ላይ በጨካኝነቱ የተማመነበትን ጄነራል ባዶሊዮን ሾመ። ለጦርነቱም ስልት አወጣለት።

በጠቅላላው የኢጣልያ ዓይን በኢትዮጵያ ላይ፣ የኢትዮጵያ ተስፋ በዓለም መንግሥታት ማህበር ላይ ሆነ። ሙሶሊኒ በዓላማው ፀና። ጦርነቱን ለመክፈት ጠብ መጫር ያዘ። በጐንደር ቆንሲሉ አማካይነት ያስነሳው ጭቅጭቅ በኢትዮጵያ ጥረት ሲበርድ፣ የወልወልን ግጭት አስነሳ። ይህንንም በሚገባ አናፈሰው፤ ለዓለም ማህበርም ስሞታ አቀረበበት። ይህንን ሁሉ ከአዘጋጀ በኋላ ጦርነቱን በራሱ ሥልጣን ከፈተ።



ሠራዊቱም በአገኘው መሣሪያ ሁሉ፤ በጋዝና በመርዝ ጭምር እንዲዋጋ ትዕዛዝ ሰጠ።

ከሰሜንና ከደቡብ ምሥራቅ በአንድ ጊዜ በምድርና በአየር ተንቀሳቅሶ ኢትዮጵያን በመስቀለኛ ቅስት ወጠራት። የሰሜኑ ጦር ከአሥመራ ተነስቶ በሁለት መንታ መንገድ እንዲንቀሳቀስ አደረገ። አንዱ ቡድን በአዲግራት፣ በመቀሌ፣ በደሴ አድርጎ አዲስ አበባ እንዲገባ። ሁለተኛው ቡድን በአዲኲላ፣ በአክሱም አድርጎ ጐንደር፣ ጐጃምን ከዚያም ወለጋን፣ አፋርና ኢሉባቡርን እንዲይዝ አደረገ። ከሞቃድሾ የሚንቀሳቀሰው ደግሞ እንደዚሁ ከሁለት ተከፍሎ እንዲያጠቃ አሰለፈው። አንዱ ቡድን በፌርፌር፣ በቀብሪ ደሐር፣ በደገሐቡር፣ በጂጂጋ አድርጎ ሐረር እንዲገባና ድሬዳዋን በመያዝ የባቡሩን ሀዲድ እንዲቆጣጠር፣ ከዚያም አዲስ አበባን እንዲያጠቃ። ሌላው ቡድን በደሎ ፣ በነጌሌ፣ በይርጋ ዓለም አድርጎ ደቡቡን እንዲይዝ አደረገ። በአሰብ ለመንቀሳቀስ የሞከረ ቡድንም ነበር። ነገር ግን እምብዛም ውጤት አላስገኘም።


**<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>**

1. Carlton Hayes, *Contemporary Europe*, pp.123-311.
2. Ibid., pp.378-9 and 33-82.
3. Stanley Cooperman, *Benito Mussolini*, pp.147-160.
4. Ibid.,33-82.

## ምዕራፍ ሶስት
## የጐንደር ውዝግብና የወልወል ግጭት፤ የአውሮፖ መንግሥታት አመለካከት

ኢጣልያ ለጦርነቱ ሙሉ ዝግጅት ከአደረገች በኂላ ጠብ መጫር ጀመረች። ሃይማኖት የሚያስተምሩ መስለው ቀደም ብለው የገቡ ሚሲዮናውያን፣ ነጋዴዎች፣ የዲፕሎማቲክ ሰዎች በዚህ ጉዳይ አገለገሉ። ከተለመደና ቋሚ ከሆነው የስለላና የስብከት ግብራቸው ገቡ።

የኢጣልያ መንግሥት በዚያ አካባቢ የነበሩ ሚሲዮናውያንን ለመርዳት በሚል፤ ጐንደር አንድ ቆንሲል አስቀምጦ ነበር። ይህ ሰው ራፋኤል ዴ ላውሮ የሚባል ሲሆን፤ ወልደ ሩፋኤል ነኝ በሚል ራሱን ሰይሞ አማርኛ በማጥናት አገርና ሕዝቡን ያጠና ሰው ነበር። ከጳጳሱ ከአባ አብርሃም፣ ከካህናቱና ከመኳንንቱ ጋር ወዳጅነት ከመመሥረቱም በላይ፤ በጽህፈት ቤቱ አጠገብ ትምህርት ቤት አቋቁሞ ለተማሪዎች ልብስ እያለበሰ፤ የኢጣልያ ቋንቋና የፋሽስትን ሥርዓት ያስተምር ነበር። ምንም ቁጥጥር ስለማይደረግበት መለከት እያስነፋ መንደር ለመንደር እየዞረ፤ ከፈለገው ሰዉ ጋር ይነጋገርና የወደደውን ያደርግ ነበር። በየድግሱ ቤት እየገባ ይበላና ይጠጣ ነበር። በዚህ ዓይነት የሰበሰበውን ወሬ፣ የራሱን አስተያየት በመጨመር፣ ለኢጣልያ መንግሥት ሪፖርት በመስጠትና ምክር በማቅረብ በጦርነቱ አካሄድ ላይ የበኩሉን ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጐአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታደሰ ዓለሙ የሚባል የቆንሲሉ ዘበኛና የጐንደር ከተማ ፖሊስ የነበረው በላይ ገብረ እግዚአብሔር፤ አንዲት ብዙነሽ ነጋሽ በምትባል ሴት ምክንያት ጠብ አንስተው ሲታኮሱ፤ ቹኰል ታየ የሚባል ሌላ የቆንሲሉ ዘበኛ ሞተ። ራፋኤል ዴ ላውሮ ታላቅ ሪፖርት ስለአቀረበ አዲስ አበባ የነበረው የኢጣልያ ሌጋሲዮን በነገሩ በብርቱ ገባበት። በኢጣልያ መንግሥት ላይ በደል የተፈፀመበት ለማስመሰል ልዩ ጥረት አደረገ። ጠብን ለማብረድ ሲባል የጐንደር ከተማ ከንቲባ የከተማይቱን ዘበኞች አሰልፈው፤ እስከ ቆንሲሉ መሥሪያ ቤት ድረስ ሄደው ይቅርታ ጠየቁ። የደም ዋጋም ለሟቹ ወገኖች ከሚገባቸው በላይ ተከፈለ። በዚህ ዓይነት በጐንደር በኩል የተቀሰቀሰው ጠብ በረደ።[1]

ነገር ግን በጐንደር በኩል አንድ ጠብ ሲበርድ በወልወል በኩል ሌላ ግጭት ተነሳ። ጦርነቱ ከተነሣባቸው ምክንያቶች ዋነኛው እሱ ስለሆነ በዝርዝር መመልከት ይበጃል።

ኢጣልያ ኢትዮጵያን በያዘች ጊዜ ከወዳጅ ጋር የሚያቃቅር ነገር እንዳይኖር በቅድሚያ ተገቢውን ለማድረግ፤ እንግሊዝ በሰሜን ሶማልያና



በኢትዮጵያ መካከል ያለው ወሰን እንዲከለል ጠየቀች። ለወሰኑ ክለላ ሥራ ከእንግሊዝ ወገን ኰሎኔል ክሊፎርድ /ጉዳዩ ጦር ቀመስ ስለሆነ/፤ በኢትዮጵያ በኩል ፊታውራሪ ተሰማ ባንቲ /አፀፋውን ለመመለስ/ ዋና ተካፋዮች ሆኑ። የወሰን መካለሉ ሥራ የሚካሄደው በግንቦት 6 ቀን 1889 ዓ.ም (ሜይ 14 ቀን 1897) በአፄ ምኒልክ እንዲሁም በንግሥት ቪክቶሪያ ወኪል በሆኑት በሠር ጀምስ ረኔል ሮድ መካከል በተፈረመው ስምምነት[2] መሠረት ሆኖ፤ በወሰኑ ላይ ሕጋዊና ቅዋሚ ምልክቶች በማድረግ ነበር። የወሰን መካለሉ ሥራ ያለ ምንም ችግር ሲካሄድ ቆይቶ የአጋዴን፣ የሰሜን ሶማልያና የደቡብ ሶማልያ ግዛት እስከሚወሰንበት ቦታ ደረሰ። ስምምነቱም በኢትዮጵያ በኩል ከዓለም መንግሥታት ማህበር የገባ ነበር። ቡድኑ ከዚህ ቦታ ሲደርስ ግን ታላቅ ችግር አጋጠመ።

እንግሊዞች የወሰኑ መከለል ሥራ መሬቱ እየተረገጠ፣ ምልክትም እየተደረገበት እንዲሆን ጠየቁ። የኢትዮጵያ ፍላጐት ሕዝቡ በየጐሣው እየተጠየቀ በካርታው ላይ ምልክት እንዲደረግ ነበር። የኢትዮጵያውያኑን ሃሳብ እንግሊዞች ስለአልተቀበሉት፣ መሬት የመቁረት ሥራ ተጀመረ። እስከ ወልወል አካባቢም በሰላም ተካሄደ። የወሰን መከለሉ ሥራ ወደ ወልወል እየተቃረበ ሲሄድ፣ የጉዳዩ አሳሳቢነት እየከበደ ሄደ። መሬት የመቁረት ሥራ እንዲያበቃና በካርታ ላይ ምልክት እንዲደረግ የሚለው የኢትዮጵያ ሃሳብ ጠነከረ። ጉዳዩ አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት ጣልያኖች ጠብ ለመጫር ማቆብቆባቸው ስለታወቀ፤ በዚያ ላይ ደግሞ ከወልወል በስተደቡብ ያለው የግጦሽ ቦታ እምብዛም አከራካሪ ባለመሆኑ ነበር። ነገር ግን እንግሊዞች ደጋግመው ጠየቁ። ሀሳባቸው ከኢትዮጵያ ተቆርሶ ለኢጣልያ ይሰጥ የተባለውን ቦታ ለይቶ ለማወቅ ጭምር ነበር። ቡድኑ ሥራውን ለመቀጠል ህዳር 10 ቀን 1927 ዓ.ም ከጂጂጋ ተንቀሳቀሰ። አጃቢና ጠባቂ ኃይል ከኢትዮጵያ ወገን ታዘዘ።

ቡድኑ የወሰን መከለሉን ሥራ ለመቀጠል መንቀሳቀሱ ሲታወቅ ሙሶሊኒ ሙስታሄል እና በዋቢሸበሌ ወንዝ አካባቢ፣ እንደዚሁም የውሃ ጉድጓድ ያለባቸው ወልወል፣ ዋርዴር፣ ገርሎጐቤ፣ ቆራሄ፣ ቀብሪደሐርና የፋፈን ወንዝ አካባቢ ያለው ቦታ እንዲያዝ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ማንኛውም የኢጣልያ ወታደር የረገጠው መሬት ሁሉ የጣልያን ቅኝ ግዛት መሆን እንደአለበት ገለፀ። በዚህ መመሪያ መሠረት የኢጣልያ ወታደሮች፣ ወሰን ተካዮች ከመድረሳቸው በፊት ወልወልን ለመያዝ ሞከሩ። የኢትዮጵያ ወታደሮች ተከላከሉ። ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ተኩስ ተከፈተ። ኢጣልያ የፈለገችው ግጭት ተፈጠረ። ኢጣልያ አስቀድማ ተዘጋጅታ ስለነበር በታንክ የታገዘ እግረኛ ሠራዊት አሠማራች።

አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበች። በጀግንነት ሲከላከሉ 94 የኢትዮጵያ ወታደሮች ሞቱ፣ ሌሎች 45 ቆሰሉ። ከኢጣልያ ወገን ደግሞ 217 ባንዳዎች ተገደሉ።

ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን ጠብ አጫሪ አስመስሎ በዓለም መንግሥታት ማህበር አቤቱታ አቀረበ። ከዚያም አልፎ፣

1ኛ. የሐረርጌው ገዥ ወልወል ድረስ ሄዶ በዚያ ያሉትን የኢጣልያ የጦር አዛዦች ይቅርታ እንዲጠይቅ፤ ከዚህም በስተቀር አንድ የኢትዮጵያ የክብር ዘብ ተሰልፎ ለኢጣልያ ባንዲራ ሰላምታ እንዲሰጥ፣

2ኛ. የኢትዮጵያ መንግሥት ለፈረሱ ምሽጎች ማሠሪያና ለሞቱ የኢጣልያ ወታደሮች ካሣ 200,000 የማሪያ-ቴሬዛ ብር እንዲከፍል፣

3ኛ. ለግጭቱ መነሻ የሆኑ የኢትዮጵያ ሹማምንቶች ከሥልጣናቸው ወርደው እንዲቀጡ ጠየቀ።[3]

በኢትዮጵያ ወገን ከእነዚህ ጥያቄዎች አንዱን መፈፀም፤ የሀገሪቱን የግዛት አንድነትና ሉዐላዊነት ማስደፈር ሆነ። ኢትዮጵያም በመንግሥታቱ ጉባኤ ውል በአንቀጽ 15 ላይ ተመሥርታ አቤቱታዋን ለማህበሩ አቀረበች። ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ነገሩን የሚመረምሩ ዳኞች ተሰየሙ። ኢትዮጵያ አንድ ፈረንሣዊና አንድ አሜሪካዊ ስትመርጥ፣ ኢጣልያ ሁለት የራስዋን ዜጎች መደበች።

ነገሩን ለመመርመር ሁለት ቁልፍ ጥያቄዎች መታየት ነበረባቸው። ከእነዚህም አንዱ "ክልሉ የማነው?" የሚል ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ "ግጭቱን ያስነሳው ማን ነው?" የሚሉ ነበሩ። በጉዳዩ መመሪያ ለመቀበል ያለ ሀፍረት ወደ ሮም በመሄድ ሥራው ተጀመረ። ነገር ግን ኢጣልያ "ክልሉ የማነው?" የሚል ጥያቄ እንዳይነሣ፣ የወሰንና ቀደም ብለው የተደረጉ ስምምነቶች እንዳይወሱ ተከላከለች። ስለዚህ የማጣራቱ ሥራ "ጠቡን ማን አስነሣው?" በሚለው በሁለተኛው ጥያቄ ላይ ብቻ አተኮረ። ለኢትዮጵያ የተሻለ የሚሆነው "ክልሉ የማነው?" የሚለው ጥያቄ በመጀመሪያው ደረጃ ቢመረመር ነበር። የማህበሩ ጉባዔ ሐምሌ 27 ቀን 1927 ዓ.ም (ኦገስት 3 ቀን 1935) ባደረገው ስብሰባ ዳኞች የግዛቱን ጥያቄ እንዳያዩ አዘዘ።

ይኸ በእንዲህ እንዳለ ሂትለር በአንደኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ላይ ጀርመን የጦር ኃይል እንዳታቋቁም ተወስኖ የነበረውን ውሣኔ ጥሶ፤ የራይንላንድን ሠራዊት መልሶ ለማደራጀት የወሰደው እርምጃ በአውሮፓ ላይ አዲስ የድንጋጤ መንፈስ ፈጠረ። የማህበሩ አባላት አመለካከት እንደገና ተዘበራረቀ። የወልወል ግጭት ጉዳይ ብዙ ከአወዛገበ በኋላ ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ ቀረበ። ከሚያስገርሙት ሁኔታዎች አንዱ በዚህ ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያን ወክሎ የተናገረው ፈረንሣዊው የሕግ አማካሪ ሙሴ ዠዥ መሆኑ ነው። ጉባዔው የኢትዮጵያ ግዛትና ሉአላዊነት አልተነካም የሚለውን አቅዋም በግልፅ ተቀበለ።[4] የግጭቱን አነሳስ በተመለከተ ደግሞ ኢትዮጵያም፣ ኢጣልያም በወልወል በተደረገው አደጋ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም ተብሎ ተፈረደ።[5]

የወሰኑን ጉዳይ ባጭሩ መመልከት ደግሞ ሌላ ጠቅላላ ግንዛቤ ይሰጣል። በታህሳስ ወር 1900 ዓ.ም (1907) ከሞቃድሾ በስተ ሰሜን ምዕራብ 130 ማይል (208 ኪሎ ሜትር) ርቃ በምትገኘው ባይዳዋ በምትባል ቦታ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል ግጭት ደረሰ። በዚህ ግጭት ምክንያት በዳግማዊ ምኒልክና በሣልሣዊ ኢማኑኤል መልእክተኛ በሲኞር ኪሊ ዶ ፊሊዛኖ መካከል አንድ የወሰን ክልል ስምምነት ግንቦት 8 ቀን 1900 ዓ.ም (16 ቀን 1908) ተፈረመ። የስምምነቱ ዓላማ በኢጣልያ ይዞታና በኢትዮጵያ ግዛት መካከል ያለውን ወሰን በማያሻማ ሁኔታ ለመከለል ነበር። ለስምምነቱ መሠረት የሆነው ቀደም ብሎ በ1897 ዓ.ም በሁለቱ መንግሥታት መካከል ተፈርሞ የነበረው ውል ነበር። ምንም በስምምነቱ መሠረት መሬቱ ተረግጦ ወሰኑ ባይቆራም፤ ውሉ ፀንቶ የቆየና በኢትዮጵያ በኩል በ1915 ዓ.ም (1923) ለዓለም መንግሥታት ማህበር ገብቶ የተመዘገበ ነበር።

ወልወል በዚህ ውል ከተከለለው ወሰን 80 ማይል (ወደ 130 ኪሎ ሜትር) የምትርቅ የኢትዮጵያ ግዛት ነች።[6] የኢትዮጵያ ግዛት መሆንዋ አላከራከረም። ግዛቱ የማነው የሚለው ጥያቄ ፈጽሞ እንዳይነሣ ኢጣልያ አጥብቃ የተከላከላቸው በዚህ ምክንያት ነበር። ወልወልና አካባቢዋ በዚያን ጊዜ 359 ጥልቅ የውሃ ጉድጓዶች ነበሩባት። በግጭቱ የፈሰሰው ደም፣ የወደመው ንብረት ቀላል አልነበረም። ነገር ግን ከጥቅማቸው ውጪ ምንም ቁም ነገር ማየት ለማይችሉ ልዕለ-ኃያላን እነዚህ ጉዳዮች አንዳች አልነበሩም። ስለዚህ የቅኝ ግዛቶች ሁሉ ፍፃሜ፣ የሁለተኛው የዓለም ጦርነት መንሥዔ የሆነው የወልወል ግጭት ፍቺ ሳያገኝ ቀርቶ ጦርነቱ ቀጠለ።

የኢጣልያ ወረራ እየገፋ ሲሄድ ኢትዮጵያ ለዓለም ማህበር የምታቀርበው ነፍስ አድን የፍርድና የዕርዳታ ጥያቄ ጠነከረ። የአውሮፓ ታላላቅ መንግሥታት የጦርነት ደመና እያንዣበበባቸው ሲመጣ፤ ከማህበሩ ውጭ በሉካርኖ (እ.ኤ.አ 1925) እና እስትሬሣ(እ.ኤ.አ 1935) ላይ ሁለት ስምምነት ቀደም ብለው ተፈራርመው ነበር። ልዕለ-ኃያላኑ የዓለም ማህበርን ውል ወደ ጐን ትተው፤ የኢትዮጵያን ጥያቄ በእነዚህ ሁለት

ስምምነቶች መሠረት ለመፍታት ፈለጉ። ነገር ግን እነዚህ ሁለት ስምምነቶች በአንድ አባል መንግሥት ላይ ጥቃት በደረሰ ጊዜ ስለሚሰጠው ዕርዳታ የተለያየ ድንጋጌ ስለነበራቸው ችግር አጋጠመ። የሉካርኖው ውል እያንዳንዱ ተዋዋይ መንግሥት እንደ ፍላጐትና አቅሙ እንዲረዳ ሲፈቅድ፤ የእስትሬሣው ስምምነት ደግሞ ተዋዋዮቹ አገሮች በህብረት ዕርዳታ እንዲሰጡ ይደነግጋል።

የልዕለ-ኃያላኑ መንግሥታት ጭንቅ የእነሱ እንቅስቃሴ ሙሶሊኒን ወደ ሂትለር የሚገፋትር እንዳይሆን ነበር። ስለዚህ ያ ሁኔታ በየትኛውም ምክንያት እንዳይፈጠር መጠንቀቅ ያዙ። ስለ ኢትዮጵያ አቤቱታ ያላቸው አመለካከት ተሰበጣጠረ። ፈረንሣይ በሉካርኖ ውል መሠረት የግል እርዳታ ማቅረብን፤ እንግሊዝ ደግሞ በእስትሬሣው ስምምነት መሠረት የህብረት እርዳታ መስጠትን መረጡ። ኢትዮጵያ ግን አንዱንም አልተቀበለችም። ጉዳዩ ከማህበሩ ውጭ ይታይ የሚለው ሀሳብ ደግሞ ከነጭራሹ የክርክር ጭብጥዋን የሚያስለቅቃት ሆነ። አሜሪካን እስታንዳንደርድ ቫኪዩም የተባለው ኩባንያ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ ሊያወጣ ቀደም ብሎ ገብቶበት የነበረውን ውል እንዲሠርዝ አደረገች። ሶቪየት ራሺያ ይህንን ከመሰለ ውዝግብ የመግባት አቅምም ሆነ ፍላጐት አልነበራትም። ሙሶሊኒ ኦስትሪያን ለእሱ ትቶ በኢትዮጵያ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ለሂትለር ጥቅሙ ሆኖ ታየው። ጃፓን ኢትዮጵያን መደገፋን መረጠች። ነገር ግን ሙከራዋ የዘገየና ፍሬቢስ ሆነባት። ኢትዮጵያ በዚህ የተነሣ ለኢጣልያ ወረራ ተጋለጠች።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. *ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 187-190።
2. Pierre Petrides, *Boundary Questions between Ethiopia and Somalia,* pp.21-28
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 12-19።
4. ጆን ሐዛወይ ስፔንሰር፣ *ጥርስ የገባች ሀገር*፣ ትርጉም በመንግቱ ኃይለማርያም አርአያ መዝገቡ ተክሌ ቢልልኝ፣ ገጽ 62-69።
5. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ* ፣ገጽ 186።
6. Petrides, pp.44-52



# ምዕራፍ አራት
## ጦርነቱን ለማስቀረት የተደረገ የዲፕሎማቲክ ጥረት

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመንግሥታቸው ጠንካራ ጐን የውጭ ግንኙነት ነበር። ጥሩ የውጭ ግንኙነት ፈጠሩ። ኢትዮጵያንም ከዓለም አስተዋውቀው ከመንግስታቱ ማህበር አስገብዋት። እምነታቸውም በዲፕሎማሲ ጥበብ ኢትዮጵያን ከጦርነት ለማዳን ነበር። በመሆኑም በኢትዮጵያ ላይ ኢጣልያ የምትጭረውን ጠብ ለማብረድ ሞከሩ። እንደተገለፀው በጐንደር ከተማ የኢጣልያ ቆንሲል የነበረው ራፋኤል ዲ ላውሮ ያስነሳውን ጠብ አበረዱ።

እንደገና ከእንግሊዞች ጋር በሰሜን ሶማልያና በኢትዮጵያ ወሰን ላይ የመካለል ሥራ በሚካሄድበት ጊዜ፤ የኢጣልያ መንግሥት በ1900 ዓ.ም ከተደረገው የወሰን ክልል ወደ አንድ መቶ ኪሎ ሜትር ያህል ገብቶ በኢትዮጵያ መሬት ላይ ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ግጭት አነሳ።[1] ሞሶሎኒም ጉዳዩን ለዓለም መንግሥታት አቅርቦ፤ የተገላቢጦሽ ኢትዮጵያ ለኢጣልያ ካሳ እንድትከፍልና ኦፊሴላዊ ይቅርታ እንድትጠይቅ ጠየቀ። ከፍ ብሎ እንደተገለጸው
እነዚህን ጥያቄዎች ግን በተመሳሳይ ለመፍታት መሞከር፤ የኢትዮጵያን ክብርና የግዛት አንድነት የሚጐዳ ስለሆነ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።[2]

ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ ጉዳዩ ለመንግሥታቱ ጉባኤ ሰፊ ሪፖርት አቀረቡ። በኢትዮጵያ ላይ የተፈፀመባትን በደል አስረዱ። ቀደም ሲል እንደተገለፀውም ከብዙ ውዝግብ በኋላ ነገሩን . የሚመረምሩ ሽማግሌዎች እንዲመረጡ በዓለም ማህበር ተወስኖ ሽማግሌዎቹ "ኢትዮጵያም ኢጣልያም በወልወል ለተደረገው አደጋ ኃላፊ ሊሆኑ አይችሉም " ብለው ወሰኑ።[3] ምንም ፍርዱ የፍርሀት ቢሆን፣ ነገሩ በረደ።

ሌላው ችግር፣ እንግሊዞች አስታራቂ በመምሰልና ፈረንሣዮችን በማስከተል የሚያስነሱት ነገር ሆነ። ከዚህም አንደኛው ቀደም ባሉት ጊዚያት አፄ ምኒልክ በታመሙ ጊዜ፤ እንግሊዞች ፈረንሣይንና ኢጣልያንን አስተባብረው ታህሣሥ 13 ቀን 1899 ዓ.ም ለንደን ላይ ተፈራርመውት የነበረው አንድ አስገራሚ ውል ነበር። ውሉም፣

1. የእንግሊዝ መንግሥት በአባይ ውሃ ላይ ልዩ ጥቅም እንዲኖረው፣
2. የፈረንሣይ መንግሥት ለሐዲዱ መፈፀሚያና መመላለሻ መንገድ ሥፍራ እንዲኖረው፣

3. የኢጣልያ መንግሥት የኤርትራና የሞቃዲሾ ቅኝ ግዛቶቹን ለማገናኘት እንዲችል፤ በኢትዮጵያ ላይ አቋርጦ የሚሄድ የባቡር ሐዲድ እንዲዘረጋ የሚል ነበር። የዚህ ስምምነት መገረን እንደገና ከጉዳይ ተቀላቀለ።

ሁለተኛው እንግሊዝ የፈጠረችው ችግር ከፍ ብሎ የተጠቀሰው መዘዘኛ የወሰን ክለላ ጥያቄ ነበር። ይህ ጥያቄ፣ በዚያ ለኢትዮጵያ አስጨናቂ በሆነ ወቅት እንዲነሳ የሚያስገድድ ችግር አልነበረም። ሆኖም ኢትዮጵያ ተስማማችና የክለላው ሥራ ተጀመረ፤ በሰላምም ተካሄደ። ነገር ግን የእንግሊዝ መልእክተኞች ኢጣልያ ግጭት ለመፍጠር መዘጋጀትዋን እያወቁ፤ የግጦሹን ሥፍራ ለሁለቱም ወገን እየዞርን እንጉብኝ ማለት አመጡ። ከኢትዮጵያ ወገን ሥፍራው በየጉሣው እየተጠየቀ በካርታ ላይ እንዲሰፍርና ጉዳዩ በዚሁ እንዲያልቅ የቀረበውን ጥያቄ አንቀበልም፣ ጊዜም አንሰጥም አሉ። በዚህ ዓይነት አስገድደው ኢትዮጵያን ከወልወል ግጭት ውስጥ ጨመሩአት።

ሦስተኛው ችግር የተፈጠረው እንግሊዝ አስታራቂ መስላ ያቀረበችው ሐሳብ ነበር። ይህም በወልወል ግጭት ምክንያት ለተነሳው ጠብ ኢትዮጵያ በኦጋዴን በኩል ሀገር ቆርጣ ለኢጣልያ እንድትሰጥ፤ ኢትዮጵያም ከባሕር የምትገናኝበት የዘይላን በር ከእንግሊዝ እንድታገኝ የሚል ነበር። ነገር ግን ሙሶሊኒ ሳይቀበለው ቀረ።

አራተኛው ችግር ደግሞ ኢትዮጵያ በሰሜን በኩል የአክሱምን ቤተክርስቲያን ብቻ ወደ ራስዋ አስቀርታ እስከ ጊቤ ወንዝ ድረስ ያለውን ሀገርዋን ለኢጣልያ እንድትሰጥ፤ ከደቡብም እንደዚሁ ሰፊ ሥፍራ ለኢጣልያ መስፋፊያ እንድትሰጥ የሚል ሆኖ፤ የኢጣልያ መንግሥት የአሰብን የባሕር በርና በጂቡቲ መካከል ያለውን ሥፍራ ለኢትዮጵያ እንዲሰጥ የሚል ማጽናኛ ነበረበት። ይህ ሐሳብ በኢትዮጵያ በኩል ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ።[4] በእነኚህ ሁኔታዎች ምክንያት ችግሩን በዲፕሎማቲክ ዘዴ ለመፍታት የተደረገው ጥረት መክኖ ስለ ቀረ፣ ጦርነቱን የመመከትና የመከላከሉ ሥራ ቀጠለ።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገፆች 187-96።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 16።
3. ቀ.ኃ.ሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 186።
4. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 9-10። ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ ገጽ 223፡



# ምዕራፍ አምስት
# የጦር ዝግጅት

ኢጣልያ የአዘጋጀችው ጦር ከራሷ ተወላጆች፣ ከኤርትራውያን፣ ከሶማሊያና በጥቂቱም ከሊቢያ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልፃል።[1] የጦሩ አሰላለፍ ቅደም ተከተል ደግሞ እንደሚከተለው ነበር። ኢጣልያውያኑ ከኋላ ደጀን፣ በሁለተኛ ደረጃ በመካከል ኤርትራውያን /ሕዝብ ሐማሴን የሚሏቸውን/ እና ሶማሌዎች፣ በሦስተኛ ደረጃ በግንባር ደግሞ ከሀገር ውስጥ የተቀጠረው ባንዳ ነበር።

ኢጣልያኖቹ፣ በተለይም የፋሽስት ፓርቲ አባላት የነበሩት የፖለቲካ መሪዎች የጦር አለቆች ሲሆኑ፤ ማንኛውም ነገር የሚወሰነው በእነሱ ነው። የኤርትራና የሶማሊያ ተወላጆች /አስካሪዎች/ የተሰማሩት በተራ ወታደርነትና በአስተርጓሚነት ሥራ ነበር። ሆኖም ከጣልያኖች በታች ሙሉ ሥልጣን ነበራቸው። ባንዳ እግረኛ ተዋጊ ነው። በስለላ ሥራም ጠላትን ያግዛል። የታዘዘውን ከመሥራት በስተቀር ሌላ ሥልጣን የለውም።

ኢጣልያ በጦርነቱ ከልብ አስባበት ስለነበር በቂ መሣሪያ አዘጋጅታለች። ስለዝግጅቱ የተለያዩ ግምቶች ተሰጥተዋል። እውነት መስሎ የሚታየው ከዚህ የሚከተለው ነው።

| | |
|---|---|
| ጠመንጃ… | 782,390 |
| መትረየስ | 23,251 |
| መድፍ | 2,608 |
| ታንክና መኪና | 25,980 |
| ጥይት በያይነቱ | 1,281,816,100 |
| የጭነት እንስሳት | 162,790 |
| የመድፍ ጥይት | 7,600,000 |
| አይሮፕላን | 500 |
| መኪናና ሞተር ሳይክል | 6,500 |
| የሆስፒታል መርከቦች | 8 |

ትክክለኛ ቁጥሩ ገና ያልታወቀ ቢሆንም፣ በእጅ የሚወረወርና ከአይሮፕላን የሚጣል ቦምብ፤ እንዲሁም ግምቱ ያልታወቀ በአይሮፕላን የሚረጭ የጋዝና የኤፐሪት መርዝ አቅርባለች።

የሰው ኃይልን በተመለከተ የነበረውም ዝግጅት እንደዚሁ ከባድ ነበር።

| | |
|---|---|
| የጦር መኰንኖች | 25,000 |
| እግረኛ ወታደር | 509,700 |
| የመንገድ ሠራተኞች | 50,000 |

| | |
|---|---|
| መምህራን/ለኢጣልያን ልጆች/ . | 12,000 |
| ጋዜጠኞች | 3,000 |
| ሰላዮች | በብዛት አሠማራች።[2] |

በ15 እና በ55 ዓመት የዕድሜ ክልል ያሉ ጣልያናውያን ሁሉ በወታደርነት እንዲያገለግሉ አወጀች። ይህ ለዋናው ጦርነት ያቀረበችው ሲሆን ኢትዮጵያን ከያዘች በኋላ ደግሞ ከሀገር ተወላጅ ባንዳ እየመለመለች የአጫጭር ጊዜ ሥልጠና በመስጠት ጨምራበታለች።

የኢትዮጵያ ጦር ጀሌውንም ጨምሮ 700,000 ይገመታል። ከዚሁ ውስጥ የጦር ልብስ ለብሶ ደህና የጦር መሣሪያ የጨበጠው ከ25,000 አይበልጥም። 200 መድፍ 50 ኦርሊኮን/ፀረ አይሮፕላን/፣ 3500 መትረየስ፣ 15 ትንንሽ አይሮፕላኖች እንደነበሩ ይገመታል።[3]

የጦርነቱ አለመቅረት እየታወቀ ሲሄድ፣ የገነት የጦር ትምህርት ቤት ተቋቋመ። አንድ መቶ ሃምሣ ያህል ወጣቶች ትምህርት ጀመሩ፤ አስተማሪዎች ሲዊዲኖች ነበሩ። የስዊድን አልጋ ወራሽ ልዑል ጉስታፍ አዶልፍ ኢትዮጵያን በጎበኙ ጊዜ በተደረገ ንግግር መሠረት የመጡ ነበሩ። ሥልጠና ከጀመሩት ወጣቶች 105ቱ በጥር ወር 1928 ዓ.ም በመቶ አልቅነት ተመረቁ። በጦሩ ውስጥ ገብተው እንዲያዋጉ ቢታሰብ እንግሊዝ አዲስ አበባን ይጠብቁ የሚል ሀሳብ አቀረበች። ወጣቶቹ ከጦር ግንባር እንገባለን አሉ። ምክር ተደርጐ በሩን እንዲከላከሉ ተወሰነ።[4]

በኢትዮጵያ በኩል የጦር መሣሪያ ለመግዛት ሙከራ ተደረገ። ሃያ አምስት ሣጥኖች ከሐምበርግ ከተማ ተጭነው ለንጉሠ ነገሥቱ እንዲደርሱ ተላኩ። ሰባት ሚሊዮን ጥይት፣ 2,850 ከባድ መሣሪያዎች፣ 1,400 ጠመንጃዎች የያዙ ነበሩ። ዋጋቸውም የተከፈለባቸው ነበሩ። ሆኖም ለኢትዮጵያ መንግሥት የጦር መሣሪያ እንዳይገባ በፈረንሣይ መንግሥት ስለተከለከለ፤ ከጂቡቲ ወደብ ከደረሱ በኋላ ታገዱ። የወደቡ ሠራተኞች "ሣንዱ አልተሟላም" የማለት ሐሳብ ፈጠሩ። እዚህ ላይ "ጦርነት በተነሣ ጊዜ ኢትዮጵያ ወታደሮችዋንም ሆነ የጦር መሣሪያዋን ያለምንም ዋጋ የባቡሩ ድርጅቱ እንዲያመላልስ ተወስኖአል" የሚለው የአፄ ምኒልክ ስምምነት ከውል አልተቆጠረም።

ለታሪክ ማስታወሻነቱ ጭምር ሳይጠቀስ ሊታለፍ የማይገባው ጉዳይ፡- የጣልያን ግልጽ ወረራ ከመጀመሩ ወደ አንድ ዓመት አስቀድሞ በንጉሠ ነገሥቱ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ትዕዛዝ፤ ሀገሩ ሁሉ ለመከላከሉ ተግባር መዋጮ ታዝዞ ነበር። የተሰበሰበው ገንዘብ መጠን ባይታወቅም፤ በየባለቤቱ አንድ አንድ ጠገራ ማርትሬዛ ብር መዋጣቱ ግን እርግጥ ነው። ሁኔታው ግን «ሰርገኛ መጣ፣ በርበሬ ቀንጥሱ» ያስባለ ሆኗል።



ኢጣልያ ግን፣ የኢትዮጵያ አቤቱታ እንዳይሰማ የዓለምን ጆሮ ከደፈነች፣ መሣሪያም እንዳታገኝ የአውሮፖን መንግሥታት ከአስተባበረች በኋላ ጦርነቱን ከፈተች። ሙሶሊኒም "... ከኢትዮጵያ ጋር ያለኝን ያሁኑንም ሆነ ያለፈውን ቂሜን መበቀል አለብኝ" ብሎ በገሀድ ዛተ። ይህንንም ብሎ ሰላማዊቱን ኢትዮጵያ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም በይፋ ወረረ።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም በበኩላቸው በማግስቱ መስከረም 22 ቀን የክተት አዋጅ አስነገሩ። አሥራ አንድ ነጥብ ያለው የጦር መመሪያም ሰጡ።[5]

እዚህ ላይ ለአንባቢያን ላስገነዝብ የምወደው፣ እስከ ሚያዝያ 1937 ዓ.ም ድረስ ዓለምን የለበለበው ሁለተኛው የዓለም ጦርነት በዚሁ ሁኔታ መጀመሩን ነው። ዓለም ይኽንን ማመን አይወድም። ነገር ግን ሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ የኢትዮጵያ ድንበር ወልወል ላይ በክንቱ በተደፈረ ጊዜ መከፈቱ የማይታበል የታሪክ ሐቅ ነው።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. የማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ *የኢትዮጵያ የድል መታሰቢያ 23ኛ ዓመት*፣ ገጽ 11።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 34-6።
3. ማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ገጽ 62።
4. በኰሎኔል ገብራይ ገብረእግዚእ ለፀሐፊው ተነገረ።
5. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ* ፣1ኛ መጽሐፍ፣ ገጽ 189-97።

# ምዕራፍ ስድስት
# የአድዋና የአክሱም መያዝ

በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ለተካሄደው ጦርነት፣ አድዋ ታላቅ ሐውልት ነው። ሙሶሊኒ የጣልያኖችን ልቦና ወደ ጦርነቱ ለማስገባት የቻለው፤ ስለ 1888ቱ አድዋ የነበራቸውን ውስጣዊ ስሜት በነገር በመኰርኰር ነበር። ስለዚህ በ1928 ዓ.ም ጦርነት የአድዋ ተመልሶ መያዝ በጣልያኖች ዘንድ ልዩ የታሪክ ክብር ነበረው።[1]

ይህ ስሜት በኢትዮጵያ ዘንድ የታወቀ ስለነበረ፣ የመከላከያ ሥልት ተሠራ። በቀኛዝማች /ደጃዝማች/ ዓባይ ካሣ የሚመራው አንድ የጦር ክፍል ሰንሰለታማ ጉድጓድ /ትረንች/ በመቆፈርና ለጠላት እንዳይታይ ቅጠላ ቅጠል በማልበስ፤ በታንክና በተሽከርካሪ የሚደረገውን ወረራ ለመከላከል ተዘጋጀ። መስከረም 18 ቀን 1928 ዓ.ም ሌሊት ጠላት መንቀሳቀሱ እንደተሰማ ራማ ላይ መንገዱን በመዝጋት አገዱት። የጦሩ መሪ የነበረው ዶክተር ፍራንካ ተይዞ ወደ መጣበት እንዲመለስ ተደረገ። ቀኛዝማች ዓባይ ካሣ የፊታውራሪነት ማዕረግ ተሰጣቸው።

ጣልያኖች ከሽምበቆ እስከ ዛላአንበሳ ያለውን ግንባር በእግረኛ፣ በመድፍና በታንክ በማጥቃትና በአይሮፕላን በማስደብደብ መስከረም 21 ቀን 1928 ዓ.ም ወረራ ከፈቱ። በማግስቱ መስከረም 22 ቀን ኃይላቸውን አጠናክረው ወረራውን አፋፋሙ።[2] በመጀመሪያው እንቅስቃሴያቸው መስከረም 25 ቀን 1928 ዓ.ም አዲግራትን ይዘው፤ ወዲያው መንገድ እየሠሩ ወደ አድዋ አመሩ። ጦሩና ለዚሁ ሥራ የመጡት ባለሙያዎች መንገድ ሲሰሩ፤ የኢጣልያ አይሮፕላኖች አድዋ ከተማ ላይ እያንዣበቡ የስብከት ወረቀት በተኑ። ኢትዮጵያውያንም ፀረ አይሮፕላን ጥይትና መትረየስ በመተኮስ ተከላከሉ። ነገር ግን ውጤት አላገኙም። ሕዝቡ በፍርሃት ከተማዋን ለቅቆ ወጣ።[3]

የኢጣልያን ወታደር የአድዋን ከተማ ለመያዝ ተጠጋ። የኢትዮጵያም ወታደር ተከላከለ። ሠላሣ ጣልያናውያንን ገድሎ ሌሎች 70 አቆሰለ። ሌሎች 33 ጣልያናውያን የደረሱበት ጠፋ። ይሁን እንጂ የ84ኛው ሬጅሜንት 2ኛ ብርጌድ መስከረም 26 ቀን 1928 ዓ.ም የአድዋን ከተማ ያዘ። የዚህች ከተማ መያዝ እንደሌሎች ከተሞች አያያዝ ተራ ነገር አልነበረም። የሦስተኛ አየር ኃይል አዛዥ ጄነራል ራንዛ የአድዋን መያዝ ለደቦኖ በቴሌግራም አስታወቀ። ደቦኖም በተራው ለሙሶሊኒ "..ኢጣልያኖች በኩራት አድዋ ገቡ" ብሎ አስተላለፈ። በሮማ ከተማና በኢጣልያ ወታደሮች ዘንድ ታላቅ ደስታ ሆነ።



ይህ ብቻ አልነበረም። ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለመውጋት ሲያስቡ፣ ወታደር ተዘጋጅቶ ሲጓጓዝ ከሮማ ድረስ አብሮ የመጣ፤ በ1888 ዓ.ም በተደረገው የአድዋ ጦርነት ለወደቁት ኢጣልያውያን መታሰቢያ የዕብነ-በረድ ሐውልት፤ በሙሶሊኒ ልዩ ትዕዛዝ በከተማይቱ መካከል ተተከለ፤ በጀኔራል ደቦኖ በራሱ ተመረቀ።[4]

በጣልያኖች ዘንድ ሌላው አሳሳቢ ቦታ አክሱም ነበር። በእንግሊዝ አቀነባባሪነት ለንጉሠ ነገሥቱ የቀረበው የዕርቅ ሐሳብ ኢትዮጵያ የአክሱምን ቤተክርስቲያን ወደ ራስዋ እንድታደርግ የሚል ነበር። ልክ በውጫሌ ውል አፄ ምኒልክ ደብረ ቢዘንን ወደራሳቸው እንደአደረጉ። የዚህን ቅዱስ ቦታ የኢትዮጵያነት ብዙ መንግሥታት ለዓለም ማህበር ስለአስታወቁና የፈረንሣይ ጋዜጦችም ለሕዝብ በይፋ ስለገለጹ፤ ሙሶሊኒ ለባዶልዮ ማስጠንቀቂያ አስተላለፈ። በምስጢር የጻፈው ቴሌግራም "...ይህ /የአክሱም/ ገዳማዊ ቀበሌ በብርቱ ጥንቃቄ መጠበቅ እንዳለበት እንድታውቀው ነው" የሚል ነበር።

ነገር ግን ባዶልዮ ለዚህ ቴሌግራም በሰጠው መልስ "የአክሱም ገዳም... የኢትዮጵያዊነቱን ክፍል እንደያዘ መቆየት አለበት የተባለውን የውጭ መንግሥታት ሐሳብ ከምንም አልቆጥረውም..." አለ። ሙሶሊኒም "... የአክሱምን ካህናትና መነኮሳት ጠይቀህ ... በኢጣልያን ንጉሣዊ ዙፋን ሥር እንተዳደራለን የሚሉ እንደሆነም.. እያንዳንዳቸውን በጽሑፍ አስፍረህ ቃል የገቡበትን ወደ እኔ እንድትልክልኝ" የሚል ትዕዛዝ አስተላለፈለት።[5] ነገር ግን ምንም ምላሽ ሳያገኝ ቀረ። እዚህ ላይ ሙሶሊኒ የተመለከተው የራሱን ኃይል ብርታት እንጂ፤ የአክሱምን ካህናትና መነኮሳት ልቡና ጥንካሬ ከግምት አላስገባም ነበር።

በዚህ ዓይነት የጣልያን ጦር አክሱም ገባ። የኢትዮጵያም ጦር የቦታውን ቅድስና ለመጠበቅ ሲል አልተከላከለም። በመሆኑም የአክሱም ቤተመቅደስ ጉዳት ሳይደርስበት ቀረ።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ አፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 239።
2. ደጃዝማች ዓባይ ካሣ፣ የሕይወት ታሪክ፣ ከጀግኖች ማህበር ጽሕፈት ቤት አዲስ አበባ።
3. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 70።
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 71።
5. ሞገስ ክፍሌ፣ *የምሶሎኒ ምስጢር* ፣ገጽ 62-63።

## ምዕራፍ ሰባት
## የኢትዮጵያ ሠራዊት የክተት እንቅስቃሴ

የክተት አዋጅ መስከረም 22፣ 1928 ዓ.ም እንደተሰማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ሥጋት ወደቀበት። አብዛኛው የገጠር ሕዝብ መሪዎቹን አያውቅም። በሚያውቃቸው በጥቂቶቹም ላይ እምነት አላደረበትም። ነገር ግን የእናት ሀገር ጥሪ ነውና ተንቀሳቀሰ። አንካሴውን አሾለ፤ ጦሩን፣ ጐራዴውን፣ ሰይፉን ሣለ። የጋሻውን ጥቀርሻ አራገፈ። ጐራዴ፣ ጨቤ፣ ሴንጢ ፣ ዱላና ዘንግ በብዙዎቹ እጅ ይታይ ነበር። ጠመንጃ ያለው የታደለ ነው። ካሉት ጠመንጃዎች የሚበዛው ናስማስር፣ ሰናድር፣ መስኮብና ሹልኪት ሰናድር ነበር። መውዜርና ለበን ብርቅ ናቸው። ከተዘረዘሩት ጠመንጃዎች ደግሞ ከለበን በስተቀር ሌሎች ሁሉ ጭሳማ ናቸው። ይግላሉ ቀለሀቸው በውስጣቸው ይጐረዳል። አንዳንዶቹም ወደኋላቸው ባሩድ ስለሚሸኑና የተኳሹን ዓይን ስለሚያጠፉ አያስተማምኑም። አብዛኞች በቂ ጥይትም የላቸውም። ሃያና ሠላሣ ጥይት ያለው ጐበዝ ነው። ከዚህም ውስጥ መሣሪያውን ለመሞከር፣ ዓይኑን ለማጥራት፣ ለዘመቻው ከቤቱ ሲወጣ ቤተሰቡን ለመሰናበት ይተኩስለታል። "ግድ የለም መሣሪያ ከዚያው ይገኛል" ይላል። ከጠላቱ የሚነጥቅበትን መንገድ ያሰላስላል።

ሴቱ ስንቅ ያዘጋጃል። ለቅርብ ጊዜ የሚሆን ጭብጦ፣ ጢብኛ ይጋገራል። ለሩቅ ጊዜ የሚሆን ቆሎ ይቆላል፣ ዳቦቆሎ ይቆርጣል። ከተቻለው ቤት ደግሞ የማር ወይም የቅቤ ጭኮ ይዘጋጃል። ሰሊጥና ኑግ ይለጠለጣል። ለመያዣ ደግሞ ስልቻና ቅል አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

ሌላው ጉዳይ ለጉዞ የሚረዱ እንስሳት ማዘጋጀት ነው። ለዕቃ መጫኛ ከሁሉም አስተማማኙ ወደል አህያ ነው። ከጠፋ፣ እርጉዝ ከአልሆነች፣ ሴትዋም ትጫናለች። የተቻለው የበቅሎ፣ ካልተገኘም የፈረስ አጋሰስ ያዘጋጃል። የተቻለው የጭን በቅሎና ፈረስ ይኖረዋል። የበቅሎና የፈረስ ዕቃም ይዘጋጃል። ልጓምና እርካብ አስተማማኝነቱ ይረጋገጣል።

በዚህ ዓይነት የተዘጋጀው ሠራዊት ሚስቱን ልጆቹን እየተወ፣ ወላጆቹንና ዘመድ ወዳጆቹን እየተሰናበተ፣ ቤተሰብ የሌለው ጐጆውን እየዘጋ ተነሣ። መንገዱ ሁሉ ቀረርቶ ፉከራ ሆነ። አብዛኛው ወደ ሰሜን ሌላው ደግሞ ወደ ኦጋዴን ዘመተ። እጅግ የተፈራው የኦጋዴን ግንባር ነበር። ወደዚህ ግንባር ለሚዘምተው ሠራዊት የአዳል ጫማ አስፈላጊ ነበር።

ከዚህ ዓይነት ዝግጅት በኋላ ሠራዊቱ ዘመተ። አዲሱ የጦር ሥልት በገጠር ገና አልታወቀም ነበርና፤ የዘመተውም እንደየመሬቱ ደንብ



ነበር። ጥንት የመሬቱ ሥሪት ግንደበል፣ ፋና ወጊ፣ ውሃ ስንቁ፣ ደስታ ተካይ፣ ጠመንጃ ያዥ፣ የቅስና፣ የድቁና፣ የአወዳሽ፣ የገበዝና የመሪጌትነቱ ነበር። የሀገር ጉዳይ ነውና ሁሉም መዝመት አልቀረለትም። ዱግ፣ ጭቃሹም፣ ምስለኔ፣ መልከኛ አዝማች ሆነ። ከከተማ የሚንቀሳቀሰው ዘማች ከገጠሩ ዘማች የተሻለ አቅም ነበረው። ቢያምንበትም፣ ባያምንበትም አለቃውን ያውቃል። አብዛኛው የሆነ ዓይነት ጠመንጃና ጥይት አለው። ስለጦርነቱም አንዳንድ ሁኔታዎችን ይረዳል። ሁሉም በየታዘዘበት ጉዞውን ቀጠለ።[1] ዘማች ከሄደ በኋላ ሀገር ባዶ ሆነ። ሴት፣ ሽማግሌና ልጅ ብቻ ቀረ። በአብዛኛው የገጠር ቤተሰብ የሚበላው ጥሬ፣ የሚጠጣው ውሃ፣ የሚተኛው ከመሬት ሆነ። ሀዘኑ ከባድ ነበር። ለምሳሌ ቡልጋ እመየት ሀገር በተባለው ቦታ፤ አፀደ ወልደጊዮርጊስ የምትባል ሴት ነበረች። ባልዋ አቶ አበበ ከማይጨው ሲመለስ መቀነትዋ ከወገብዋ ተጣብቆ አልፈታም አላት። ልጦም አቆሰላት።

አዝማቾች በንጉሠ ነገሥቱ ተሾሙ። ለዋናው የሰሜን ጦር ግንባር ራስ ሙሉጌታ ይገዙ ተሾሙ። ራስ እምሩ ለጐጃም ለጐንደር፣ ራስ ካሣ ለወሎ፣ ራስ ስዩም ለትግራይ ጦር አዛዦች ሆኑ። ለደቡብ ምሥራቅ ራስ ደስታ ዳምጠው፣ በሐረርጌ በኩል ደግሞ ደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል ተመደቡ።

የንጉሠ ነገሥቱን አመኔታ ያላገኙ በጦርነቱ ውስጥ የመሳተፍ እድል አላገኙም። ራስ ብሩ ወልደገብርኤል ቦታ አልተሰጣቸውም። የወሎው ደጃዝማች በላይ ለመዝመት ቢጠይቁ አልተፈቀደላቸውም። ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ ታስረው እጃቸው ለደጃዝማች ብሩ ተሰጠ።

ሠራዊቱ ወደየጦሩ ግንባር ከመግባቱ በፊት በዋና ዋና ቦታዎች ተሰበሰበ። የትግሬ ጦር እዚያው እደጁ ገጠመ። የጐጃምና የጐንደር በዚያው በኩል ወደሰሜን ዘመተ። የከምባታ ጦር ጥቅምት 1 ቀን 1928 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። የወለጋ፣ የከፋ፣ የኮንታ፣ የጐሬ ጦር በየአለቃው ኮተተ። ታላቅ ሰልፍ አሳየ። እንደአሻው የሚራመድ እንጂ እንደአውሮፓ ጦር እግሩን አስተባብሮ በህብረት የሚረግጥ አልነበረም። ልብሱም፣ መሣሪያውም፣ አሰላለፉም የተዘበራረቀ ነበር። የጦሩ አዲስ አበባ መሰብሰብ ታላቅ መጨናነቅ ፈጠረ። ለጠላት ሰላዮችምሳያመቻቸው አልቀረም። ሰልፉ ቀርቶ በየአቅጣጫው ቢዘምት በቀለለ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ጦሩን ከአሰናበቱና የኦጋዴንን ጦር እስከ ጅጅጋ ድረስ በአይሮፕላን ሄደው ከጐበኙ በኋላ፤ ህዳር 18 ቀን 1928 ዓ.ም ጉዞአቸውን ወደ ሰሜን ጦር ግንባር ቀጠሉ። ከአዲስ አበባ በአውቶሞቢል ተጉዘው ህዳር 21 ቀን ደሴ ገቡ።[1] የተጓዙትም የልጅ ኢያሱን ዕረፍት

በአዲስ አበባ ከተማ ለነበሩት መኳንንትና ወይዛዝርት አርድተው በይፋ ከተለቀሰ በኋላ በመሆኑ ቀላል አልነበረም።

ወደ ደቡብ ምሥራቅ የዘመተው ጦር ከጋሞጐፋ በአርሲ፣ በሲዳሞ፣ በቦረናና በባሌ በኩል ወደ ደሎ ወረደ። ከሐረርጌ የዘመተው በጅጅጋና በደገሐቡር በኩል አስቀድሞ በመገስገስ፤ በኦጋዴን ለነበረው ጦር ድጋፍ ለመስጠት ተዘጋጀ። ይህ ጦር በሌሎች ጐራዎች ከተሰለፉት ጦሮች ሁሉ ጥራትና ብቃት ነበረው።

ንጉሠ ነገሥቱ በደሴ ከተማ እንደአሉ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ አዳዲስ ገጽታዎች መታዬት ጀመረ። የትግራዩ መሥፍን ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ ኢትዮጵያን ከድቶ ከጣልያን ጐን ቆመ። እሱም ከመቀሌ ተነስቶ 1200 የታጠቁ ወታደሮችና መትረየሶች ይዞ አዲግራት ገባ። ከዚያም አሥመራ ደረሰ። በኢትዮጵያ ወገን ለጦርነቱ የተደረገውን ዝግጅት ለጣልያን አስረዳ። ከአዲስ አበባ እስከ ደሴ የተሠራውን መንገድ ጠቆመ።[2] የጐጃም ጦር በደጃዝማች ገሠሠ በለው እና በፊታውራሪ ታምራት አስተባባሪነት ጦርነቱን ወደ ኋላው ትቶ ወደ ቤቱ ተመለሰ። የንጉሠ ነገሥቱ አዋጅ፣ የጳጳሱ ግዝት አላገደውም። በዚህ ላይ የኦጋዴኑ ግንባር መላላቱ ተሰማ።

ሁኔታው በዚህ እንዳለ ለመጨረሻ ፍልሚያ የተፋጠጡት ሁለቱ መሪዎች ሹም ሽር አደረጉ። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የጦር ሚኒስትራቸውን ራስ ሙሉጌታን ሽረው ራስ ካሣን ሾሙ።[3] ሙሶሊኒም በበኩሉ ጄነራል ደቦኖን ሽሮ ጄነራል ባዶሊዮን ሾመ። ይህ የሹመት አሰጣጥ በኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ ተጨማሪ ድንግርግርን ሲፈጥር፤ በኢጣልያ ወገን ግን ይበልጥ ቁርጠኛ አልፎ ተርፎም ጨካኝ መሆንን አስገኘ።

የዓለም ቀይ መስቀል የጦሩን አሰላለፍ ተከትሎ ዕርዳታ ለመስጠት በኢትዮጵያ ወገን ገባ። ሥራውን ለማስተባበርና ለመርዳት የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ሐምሌ 1 ቀን 1927 ዓ.ም ተቋቋመ። በሰሜን የጦር ግንባር የእንግሊዝ፣ የነምሣ /ማለትም የኦስትሪያ/፣ የሆላንድ፣ የፈረንሣይ ቀይ መስቀሎች ገቡ። ከዚህም በስተቀር የግብፅ በጅጅጋ፣ የስዊድን ደግሞ በቦረና ተሰማሩ።[4]

የኢትዮጵያን ሠራዊት ሥርዓት ለማስያዝና የውጊያ ሥርዓት ለማስለመድ ተሞከረ። የጦር ዕቅድ አውጭዎች የውጭ ሀገር ሰዎች ነበሩ። ንጉሠ ነገሥቱ የሌላ ሰው ምክር አልተቀበሉም። ኢትዮጵያውያኑ አዛገሮችም ለሚያሰለጥኑት ሠራዊት የሚናገሩት ቃል በፈረንጅ ሥርዓት ነበር። ተሠለፍ፣ እርገጥ፣ ከመሬት ላይ ተንደባለል፣ ልብስህን ከል ንከር ይሉታል። ነገር ግን ስለስንቁ፣ ስለጤንነቱ የሚያስብለት የለም። ለእራሱ



አስፈላጊውን ማድረግ አለበት። ነገሩ አልጣመውም። ቢሆንም ጉዞውን ቀጠለ።[5]



የኢትዮጵያ ህዝብ በየአካባቢው ለአይቀሬው ጦርነት ክተት ጀመረ።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ.*፣ ገጽ 215-221።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 52-4።
3. Leonard Mosley, *Haile Selassie*, PP.200-8
4. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፤ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፤ ገጽ 175።
6. ከአለቃ ወንድም አገኘሁ ለጸሐፊው የተነገረ፡



የኢትዮጵያ ህዝብ በየአካባቢው ለአይቀሬው ጦርነት ክተት ጀመረ::

## ምዕራፍ ስምንት
## የሽሬ ጦር ግንባር

ሌላው የሰሜን ጦር ግንባር ሽሬ ነበር። በዚህ ግንባር ጦርነቱ ህዳር 1 ቀን 1928 ዓ.ም ተከፈተ። በየቦታው ልዩ ልዩ ጦርነቶች ተካሄዱ።

የኢትዮጵያ ጦር የተሰለፈው በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ አዝማችነት ነበር። ጦሩም የጐጃምና የጐንደር ሠራዊት ሲሆን፤ ብዛቱ እስከ ሃያ አምስት ሺህ ተገምቶአል። ከሌላው የኢትዮጵያ ጦር የሚለየው ከቦታው ቅርበት የተነሳ በመንገድ ላይ ብዙ ቅጥቃጤ ያልደረሰበት መሆኑ ነው። እንደተገለፀው በእነ ደጃዝማች ገሠሠ የሚመራው የጐጃም ጦር ቀደም ብሎ ሳይዋጋ ወደ ሀገሩ ተመልሷል፤ ይህ ጦር ግን ልቡ ሳይላላ የሀገር መከላከል ሥራውን እስከ መጨረሻው አካሄደ።

እያንዳንዱ ሽንተረር፣ ተራራ፣ ወንዝና ሸለቆ የጦር አውድማ ሆነ። ሁሉን መዘርዘር ስለሚያስቸግር ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን። ደምበጉና በተባለው ቦታ የነበረውን የጠላት ጦር፤ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከበቦ ደጋግሞ በመውጋት አስጨነቀው። ባዶሊዮ በታንክ የተደገፈ አዳዲስ ጦር ቢልክም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም። ታህሣሥ 7 ቀን 1928 ዓ.ም በተደረገው ውጊያ ከኢጣልያ ወገን ዘጠኝ መኰንኖች፣ 22 ነጭና 370 ጥቁር ወታደሮች ሞቱ። ከዚህም በስተቀር ብዙ ጣልያኖች ከአሥር ታንክና ከሁለት መድፍ ጋር ተማረኩ። ከእልቂትና ከምርኮ፣ ከመቁሰል የተረፈው የጠላት ጦር በአንድ ወገን ከበባውን ሰብሮ አመለጠ። የኢትዮጵያ ጦር እስከ አቢይ አዲ፣ እስከ ሰለክላካ ድረስ እያባረረ ወጋው ::[1]

እንደገና አምባ ደስሬ በተባለው ቦታ በታህሣሥ 13 ቀን 1928 ዓ.ም ውጊያ ተካሄደ። ጠላት የኢትዮጵያን ጦር መቋቋም ስለአቃተው ቦታውን ለቅቆ ወደ አፍጋጋ ሸሸ። በፊት እንዳባጉና፣ በኋላ ደግሞ ደስሬ ላይ የደረሰባቸው ሽንፈት ጣልያኖችን አስደነገጣቸው። አድዋ እንዳይደገም ሠጉ። ባዶሊዮ ተሸሮ ግራዚያኒ እንዲተካ ለሙሶሊኒ ሐሳብ ቀረበ። በጦር ሚኒስትሩ ብርታት ባዶሊዮ ከመሻር ዳነ። ባዶሊዮ ይህንን እንደሰማ ይበልጥ ጨከነ። አካባቢውን መርዝ አስረጨበት። እንደ እሳት በሚያቃጥለው መርዝ ብዙ ሰው አለቀ፤ ብዙ ሰው ቆሰለ።

ራስ እምሩ ከሞት የተረፈው ሠራዊት ማይላህላ ተዛውሮ እንዲከት አደረጉ። እሳቸውም ጦሩ እስኪሰበሰብ በደፈጣ ቆዩ። ጦሩ ተሰበሰበ፣ ገና ለውጊያ ያልደረሰው ጦር ገባ። ራስ ካሣ ድል ሆነው ወደ ኋላ



መመለሳቸው ተሰማ። ምክር ተደረገ። "ከሚያቃጥልና ከሚገድል ዝናም ጋር ሰው እንደምን ይዋጋል" የሚል ጥያቄ ተነሣ። ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል ሥልት ተቀየሰ። ሰማማ፣ ማይላህላ እና ሰለክላካ የመሸገው ሃያ ሺህ ደጀን ጦር እንደገና ተከዜ ላይ እንዲቆይ ተወሰነ። በኢጣልያም በኩል ዝግጅት ተደረገ። በጄነራል ማራሻኛ የሚመራው ሁለተኛው ክፍለ ጦርና በጄነራል ማቢኒ የሚታዘዘው አራተኛው ክፍለ ጦር በተጠንቀቅ ቆሙ።

የካቲት 21 ቀን በጄነራል ማራሻኛ የሚመራው ሃያ ሺህ የጠላት ጦር ከአክሱም ወደ ሰለክላካ ጉዞ ጀመረ። ሰለክላካ ሸለቆ ውስጥ አድፍጦ ይጠባበቅ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር የካቲት 21 ቀን፣ ቀትር ላይ ገጠመው። ውጊያው እስከ ሌሊት ድረስ ቆየ። የኢትዮጵያ ጀግና እየተወረወረ በመትረየሱ ላይ ተጠመጠመበት። መሣሪያ የተጫኑትን ካሚዮኖች ለመማረክ ሞከረ። ጣልያኖች ደግሞ ለማዳን በአይሮፕላን ጭምር ተከላከሉ። ታላቅ ጦርነት ተካሄደ። በአካባቢው ያለውን ኮረብታ ለመያዝ ያደረጉትን ሙከራ ኢትዮጵያውያኑ ተሽቀዳድመው በመያዝ አከሸፉባቸው። ጦርነቱ እስከ የካቲት 26 ቀን ድረስ ቀጠለ። ባዶሊዮ ስምንት ቶን የሚመዝን ቦምብ በአይሮፕላን ቢያወርድበትም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም።[2]

የኢጣልያ ጦር ብዛት ነበረው። ተተኪ ኃይልም ተላከለት። በአይሮፕላን ድጋፍ ተሰጠው። እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አገላለጽ ከጣልያን ጐን ቆመው በርትተው የሚዋጉት የኤርትራ ወታደሮች ነበሩ እንጂ፤ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች ጣልያኖች ጥቂቶች ነበሩ። ኢጣልያኖች የሚሰለፉት በጣም ርቀው በስተኋላ ስለነበር እነሱን ለማግኘት ብዙ ችግር ነበር።

በሹም አውሬ የተደረገውም ጦርነት በታሪክ ሊጠቀስ ይገባል። የእኛ ወታደሮች በተለመደ ፈጣንነታቸው እንደ ነብር እየተወረወሩ በጦርነቱ መካከል ስለገቡ፤ የኢጣልያ ወታደሮች መትረየሳቸውንና ጠመንጃቸውን ከነጥይቱ፤ እንደዚሁም ቴሌፎናቸውንና የሬዲዮ ማስተላለፊያ መኪናቸውን እየተው እስከ መሸሽ ደረሱ። የተማረከውን መሣሪያና ዕቃ ከኢትዮጵያውን የጦር ሠፈር ለማስገባት አራት ሙሉ ቀን ፈጀ።[3]

የኢትዮጵያ ጦር ቦታውን ሳይለቅ ጠንክሮ በመዋጋቱ፤ ባዶሊዮ መላው የተከዜ አካባቢ በቦምብ እንዲደበደብና መርዝ እንዲረጭበት አደረገ። የተከዜ አካባቢ በሙሉ በሬሣ ተሸፈነ። በዛ ቦታ ትግሉ ሊቀጥል አልቻለም። ራስ እምሩም የተረፉአቸውን 300 ያህል ወታደሮች ይዘው ወደ ጐንደር ተመለሱ።

የኢትዮጵያውያኑ ቁርጠኝነት አስገራሚ ነበር። ጣልያኖችን ራሳቸውን አስደንቆአቸዋል። ለማስረጃ ያህል አንድ ሁኔታ መጥቀስ ይበቃል። በሰሜን ጦር ግንባር በየካቲት 21 እና 26 መካከል በተደረገው ጦርነት ጥቂት የኢትዮጵያ ወታደሮች ተማረኩ። የጦራቸውን ወሬ ቢጠየቁ አንናገርም አሉ። ምክንያቱን ቢጠየቁ ኢትዮጵያውያን እስከ መጨረሻው ሰው ድረስ እንደሚዋጉ፤ እነሱም ቢለቀቁ ክንዳቸውን እስከሚንተራሱ ጊዜ ድረስ እንደሚፋለሙ አረጋገጡ። ይህም የመላው ኢትዮጵያዊ ሐሳብ መሆኑን ገለጹ።[4]

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ተክለ ፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ.*፣ ገጽ 245-246።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 108-111።
3. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 223-224።
4. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 110።



# ምዕራፍ ዘጠኝ
# የተንቤን ጦር ግንባር

በኢጣልያ በኩል ዋናው ግንባር የሰሜኑ ነበር። እሱም በመቶ አለቃ ሞርጋንቲኒ የተመራው የኢጣልያ ጦር ዳውሮ ተክሌ በተባለው ቦታ በኢትዮጵያ ጦር ላይ አደጋ በጣለ ጊዜ በይፋ ተከፈተ። ኢጣልያ ከመስከረም 21 ቀን ጀምሮ በአይሮፕላን የአድዋን ከተማና አካባቢውን ስትደበድብ ሰንብታ ስለነበር ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴም መስከረም 22 ቀን አዋጅ ስለ አስነገሩ ሁኔታው ግልጽ ሆኖ ነበር።

ተጠንቅቆ ይጠባበቅ የነበረው የኢጣልያ ጦር በየግንባሩ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ። መስከረም 25 ቀን አዲግራትን ይዞ ወደ እንቲጮና አድዋ የሚያደርሰውን የመኪና መንገድ መሥራት ጀመረ። በደጃዝማች ገብሬ የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር በርትቶ ተከላከለ። ሠላሣ የጠላት ወታደሮች ገድሎ ሌሎች ሰባ አቆሰለ፤ ሌሎች ሠላሣ የደረሱበት ጠፋ። በዚህ ጦርነት ላይ የመጀመሪያውን ወራሪ ኢጣልያዊ መኮንን ገደሉ። ስሙም መቶ አለቃ ሞርጋዜር ነይ ይባል ነበር። ጠላትም በቦምብ መደብደብ ጀመረ። በዚያ የነበሩ የጣልያን ወታደሮች ቦታውን ለቅቀው ስለሸሹ፣ አዛዦች አዲስ ጦር መተካት ነበረባቸው። ከሁለት ሰዓት ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ ጦር ትዕዛዝ ስለተላለፈለት ዳዕሮ ተክሌን ለቅቆ ወደ ጋሻ ወርቁ አፈገፈገ።

የጣልያን ጦር በአይሮፕላን ወረቀት በመላክ እየተለማመጠና እያስፈራራ፣ አካባቢውንም በቦምብ እየደበደበ ከ40 ዓመት በፊት የሀገሩ ክብር የተዋረደበትን የአድዋን ከተማ መስከረም 26 ቀን 1928 ዓ.ም ከጠዋቱ በአራት ሰዓት ያዘ። ሮም ተዘጋጅቶ የተላከው የዕብነበረድ ሃውልትም በፍጥነት ተተከለ።[1] ከኢትዮጵያውያን ዘንድ ሀዘን፣ በኢጣልያውያን ዘንድ ደስታ ሆነ።

በፀዲያ፣ በሐውዜን፣ በገርዓልታ፣ በኃይሌ የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ደግሞ በአቶ /ደጃዝማች/ ገብረሕይወት መሸሻ መሪነት፤ በጥቅምት 1928 ዓ.ም በቅድሚያ በእንዳ ማርያምና በአሸዊት፣ ቀጥሎም በሐመድና በአውገር፣ ከዚያም አፍካሮ በተባሉት ቦታዎች ላይ የሚያስደንቅ ውጊያ አካሄደ። ትግላቸውን በመቀጠል በህዳር ጉንዲ፣ በታህሣሥ ወር በዳዕሮና በደንገሌ፣ በመከፈል፣ በጥር ወር በሐውዜን ቆላ ተላላቅ ውጊያዎች አካሄዱ።

ወረራው ተፋፋመ። ከፍ ሲል እንደ ተገለፀው ቅዱስ ቦታ መሆኑ በሁለቱም ወገን የታመነበት አክሱም እምብዛም ጦርነት ሳይካሄድበት

ጥቅምት 3 ቀን 1928 ዓ.ም ተያዘ። ቀጣዩ የጣልያን ጦር ዓላማ የመቀሌን ከተማ መያዝ ሆነ። በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣና በግብረ አበሮቹ ምክርና ጠቋሚነት የጦርነቱ ሥልት ተቀነባበረ። የኢጣልያ ወጣት መሣፍንትና ምሑራን በልዩ ልዩ ሥራ እየተመደቡ ከሮም መንቀሳቀስ ጀመሩ። በአንፃሩ ደግሞ ብዙ ኤርትራውያን ወታደሮች ከጣልያን እየከዱ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው መቀላቀል ስለአመጡ፣ በኢጣልያ ዘንድ ሥጋት ተፈጠረ። ከሁኔታው አስደንጋጭነት የተነሣ ጥቁርና ነጭ ተቀላቅሎ እንዲዘምት የሚል አዲስ ትዕዛዝ መጣ።

በዚህ ዓይነት ከተዘጋጀ በኋላ የጣልያን ጦር መቀሌን ለመያዝ ጥቅምት 23 ቀን 1928 ዓ.ም ተንቀሳቀሰ። ጦሩ በሦስት ረድፍ የተከፈለ ነበር። ዕቅዱም ዋናው ጦር ከአዲግራት በመነሣት መሐል ለመሐል በመንዝ ምሽግ እንዲያዘጋጅ፣ ሁለተኛው በስተደቡብ እንዲጓዙ፣ ሦስተኛው ደግሞ ከአድዋ ተነስቶ በሐውዜን በኩል አልፎ ሦስቱም ጦሮች መቀሌ እንዲገናኙ ነበር። ቢያስፈልግ ዕርዳታ ለመስጠት እንዲችል ደግሞ ሌላ አራተኛ ጦር ከምፅዋ ተነስቶ በረሃውን በፍጥነት እንዲያቋርጥ ታዘዘ።[2]

የኢትዮጵያ ሠራዊት በሁሉም በር ተከላከለ። ከምፅዋ ተነስቶ በደንከል በረሃ የሚጓዘውን የጠላት ጦር በየቦታው ወግቶ ስምንት ደንጉላ ፈረስና 13 በቅሎዎች ማረከበት። ሦስት መቶ ያህል የኤርትራ ተወላጆች ተገደሉ። ብዙ ኢጣልያውያንም ሞቱ። ጠላትም የአይሮፕላን ድጋፍ በመስጠት ወረራውን ቀጥሎ በደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ እየተመራ ህዳር 1 ቀን 1928 ዓ.ም የመቀሌን ከተማ ያዘ።

የጦርነቱ ሂደት ከዚህ ላይ ሲደርስ ጄነራል ባዶሊዮ ማርሻል ተብሎ የአዛዥነቱን ሥልጣን ያዘ። ባዶሊዮ ሹመቱ እንደ ተሰጠው ከሮም ገስግሶ አሥመራ ገባ። የጦርነቱ ሥልት ተለወጠ። የቀድሞው አዛዥ ጄነራል ደቦኖ ጦርነቱን በእግር ጦር ተዋግቶ ማሸነፍ እንደሚቻል ያምን ነበር። በአይሮፕላን በሚጣል ቦምብ መደብደብ አስፈላጊ መስሎ አልታየውም ነበር። የኢጣልያን ስም የሚያጠፋ ሥራ እንዳይሠራ ምክር ይሰጥ ነበር። ከዚህም በስተቀር የኢትዮጵያ ጦር ፈጥኖ የሚያፈገፍገው፣ ከወጥመድ አስገብቶ ለማጥቃት ብሎ ሊሆን እንደሚችል ጠርጥሮ ወደፊት እንዲገፋ የሚደረግለትን ጉትጎታ አልተቀበለም ነበር። የተሻረውም በዚሁ ምክንያት ነበር።[3]

የማርሻል ባዶሊዮ አስተሳሰብ ከዚህ የተለየ ሆነ። ኢጣልያ ዳግማዊ አድዋ ቢደርስባት ሊጠገን የማይችል ውርደት እንደሚሆን ገባው። የጦርነቱ ጊዜ መውሰድ ኢጣልያን በዓለም ማህበር አደባባይ ቁጣ እያበራከተባት መሆኑ ታየው። ስለዚህ ባለው መሣሪያ መዋጋትና ቶሎ



ከፍፃሜ ማድረስ ይሻላል ከሚል ድምዳሜ ላይ ደረሰ። ሞሶሎኒ በጦርነቱ ብዙ የደከመውን ደቦኖን ሽሮ እሱን የማርሻልነት ማዕረግ ሰጥቶ የሾመው በጨካኝነቱ ተማምኖ ስለነበረ አስተያየቱን ደገፈለት። በእጁ ባለው መሣሪያ ሁሉ እንዲጠቀም፤ ማለትም በቦምብ እንዲደበድብ፣ የጋዝ መርዝና ኢፕሪት በአይሮፕላን እንዲረጭ፤ ሙሉ ሥልጣን ተሰጠው።[4]

ጣልያኖች በተንቤን የጦር ግንባር በኩል ህዳር 27 ቀን 1928 ዓ.ም ውጊያ ከፈቱ። ጦራቸውም ከመቀሌ ተነስቶ ዋሪዮ በር የተባለውን ቦታ ያዘ። ከዚያም በራስ ሙሉጌታ ይመራ የነበረውን የኢትዮጵያን ጦር ለማጥቃት ወደ አምባላጌ ተጠጋ። በስተግራ በኩልም ወደ በለሳ ገፋ። በተንቤን ምድር ከባድ ጦርነት ተካሄደ። ከአራት ቀን ውጊያ በኋላ የኢትዮጵያ ሠራዊት አሸነፈ። የጠላት ጦር አፈገፈገ። በጣልያኖች በራሳቸው አመለካከት ጉራው ዳግማዊ አድዋን መሰለ። በራስ ካሣም፣ በራስ ስዩምም የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ታላቅ ጀብዱ ሠራ። ጠላት ከአይሮፕላን በሚጣል ቦምብ ቢደበድበውም፣ የመርዝ ጋዝ ቢረጭበትም አልተበገረም። ጦርነቱ እስከ ጥር ወር ዘለቀ። ከኢጣልያ ወገን 60 የጦር መኰንኖች፣ 605 ነጭ ወታደሮች፣ 417 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ተገደሉ። ከኢትዮጵያም ጦር እስከ 8000 የሚገመት ወታደር ሞተ።[5]

ጠላት ባወጣው ዕቅድ መሠረት አንዱ የኢትዮጵያ ጦር ሌላውን እንዳይረዳ መንገዶችና በሮችን አስቀድሞ ዘጋ። ራስ ካሣና ራስ ሥዩም ተንቤን ሲከላከሉ፣ የራስ ሙሉጌታ ጦር እንዳይረዳቸው ደብር ነጋይዳን የተባለውን በር አስያዘ። ራስ እምሩ ከሽሬ እንዳይደርሱላቸው ደግሞ የአዲ ደናግልን መተላለፊያ ያዘ።

በሮችና መተላለፊያዎቹን በዚህ ዓይነት በጦር ካስያዘ በኋላ ጥር 14 ቀን 1928 ዓ.ም ዋሪዮ መልፋ ከተባለው ምሽግ ከጥዋቱ በ3 ሰዓት ወጥቶ ተንቀሳቀሰ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ማይ መርታ የሚባለውን ወንዝ ይጠባበቅ ስለነበር፣ ዘባን ቀርክሀታ ከተባለው ቦታ ላይ ከባድ ውጊያ ተካሄደ። ጦርነቱ ከተኩስ ወደ ጨበጣ ዞረ።ኢትዮጵያውያን በሚያውቁበት ዘዴ በሰይፍና በጐራዴ ጠላታቸውን ጨፈጨፉት። ጦርነቱ ከወሳኝነት ደረጃ ላይ ሲደርስ የጣልያን አይሮፕላኖች ደርሰው ከጨበጣው ለመግባት የሚገደረደረውንና ደጀን ሆኖ የሚጠብቀውን የኢትዮጵያ ጦር በቦምብ ደበደቡት።ይህም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑ አልተበገሩም። ጦርነቱ 3 መዓልትና 1 ሌሊት ፈጀ።ዓላማቸው ኢትዮጵያውያንን ከመቀሌና ከዙሪያው አስለቅቆ ለመግባት እንዲሁም ከግባ ወንዝ ወዲያ ለማባረር ነበር። አንዳቸውም ሳያሸንፉ ቀሩ። ከኢትዮጵያ ሠራዊት 1000 ሞተ፤

ሌላ 2000 ቆሰለ፡፡ ከኢጣልያ ወገን 1500 ሞተ፡፡ ሁለቱም ሰልችተው ወደየሠፈራቸው ተመለሱ፡፡

ከሀዲው ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ የመቀሌን ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ የአምባረዶም መያዝ አስፈላጊ መሆኑን ለባዶሊዮ አበክሮ ምክር አቅርቦ ነበርና፤ በጣልያኖች ወገን ዝግጅት ከተደረገ በኋላ የካቲት 30 ቀን ቀለሚኖ እና ገባ ከሚባሉት ቦታዎች ተንቀሳቀሰ፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ስለመከተ የካቲት 1 ቀን ታላቅ ጦርነት ተከፈተ፡፡ ሳያቋርጥ እስከ የካቲት 7 ቀን ድረስ ቀጠለ፡፡ በተለይ የካቲት 4 ቀን 1928 ዓ.ም ሌሊት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከጠላት ሠፈር ገብተው የተቃና ሥራ ሠሩ፡፡ በዚህ ማታ የጣልያን ጦር አምባራዶም ግርጌ ደርሶ በእግርና በአየር ወረደበት፡፡ 40 ቶን ቦምብ በመጣል ደብድቦ ስለነበርና ብዙ ሠራዊት ስለአለቀ፣ ራስ ሙሉጌታ ወደ ኋላ ለማፈግፈግ ወሰኑ፡፡ ከአየሩ ድብደባ ለመሠወር ወደ አዘቦ በረሃ ወረዱ፡፡ ለአራት ቀን የኢጣልያ አይሮፕላኖች ሳያገኙአቸው ሰነበቱ፡፡ ባገኙአቸውም ጊዜ ድብደባቸውን ቀጠሉ፡፡

በዚህ ጊዜ ከጉዞው ላይ የራስ ሙሉጌታ ልጅ ታጣ፡፡ እሳቸውም ልጃቸውን ለማፈላለግ ወደ ኋላ መልእክተኛ ላኩ፡፡ መሞቱን ሲሰሙ ደግሞ ደሙን እበቀላለሁ ብለው ወደ ኋላ ተመለሱ፡፡ ራስ ሙሉጌታ በጦር ሰልፍ እንደ አሉ ከጦር ሚኒስትርነት በመሻራቸው ልቦናቸው ሳይቆስል አልቀረም፡፡ የጦር ሚኒስትርነቱ ሥልጣን ከእሳቸው ተወስዶ ለራስ ካሣ የመሰጠቱ ምክንያት፣ ከዘር በስተቀር የችሎታ ሚዛን የተከተለ አለመሆኑ በሁሉም ዘንድ የታወቀ ስለነበረ፤ ቁስለቱ የመላው ሠራዊት እንጂ የእሳቸው ብቻ እንደአልነበረ መገመት አይዳግትም፡፡ ሽረታቸውም ለጠላት ጭምር አስደሳች ነበር፡፡ በአዲሱ ሹምሽር የተከዙት ራስ ሙሉጌታ በዚህ ዓይነት ከሠራዊታቸው ሲለዩ ለጠላት ጥቃት ስለተጋለጡ በጥይት ተመትተው ሞቱ፡፡ ጣልያኖች በአይሮፕላን ገደልን ይላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ወገን የሚታመነው ግን በአዘቦ ከሀድያን እጅ እንደተገደሉ ነው፡፡

እዚህ ላይ መጤን የሚገባው ጉዳይ በአንድ ከፍተኛ የጦር አዛዥነት የነበረባቸውን ከባድ ኃላፊነት ዘንግተው የአንድ ሰው ደም ለመበቀል ያደረጉት ሙከራ ስሕተት እንደነበረ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ልጆች ግን የአዛዡን ወደኋላ መመለስ ከምንም ሳይቆጥሩ የአምባራዶምን ተራራ መከላከሉን ቀጠሉ፡፡ በጦርነቱም ላይ የመጨረሻዎቹ ቆራጥ ጀግኖች ሲያልቁ፣ የካቲት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ተፈፀመ፡፡ በዚህ ጦርነት ከኢጣልያ ወገን 36 መኰንኖች፣ 621 ነጭና 145 ጥቁር ወታደሮች ሞተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የጥቁሮች ተሳትፎ



መጠነኛ እንደነበረ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ ወገን የወደቁት እስከ 6000 እንደሚደርስ ተገምቶአል፡፡

በሌላ በኩል ራስ ካሣና ራስ ሥዩም የጋራ ግንባር ፈጥረው በቀጨማ መልፋ የመከላከል ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡ ጦርነቱም የካቲት 11 ቀን ተጀመረ፡፡ አንድ ጊዜ አንዱ፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላው እያሸነፈ የ5 ቀን ውጊያ ተካሄደ፡፡ የኢጣልያ አይሮፕላኖች የቦምብ ነጐድጓድ አወረዱ፤ የጋዝ መርዝ አዘነሙ፡፡ እልቂቱ ከፍተኛ ሆነ፡፡ ጦርነቱ ሰው ከማስጨረስ በስተቀር ለኢትዮጵያ አንዳች ፋይዳ መስጠቱ ቀረ፡፡ ሁለቱ የጦር መሪዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ጦር ጋር ሆነው መዋጋትን በመምረጥ ወደ ኋላ ተመለሱ፡፡ ደጃዝማች በየነና መሰሎቻቸው ጠላታችንን ከፊታችን አስቀምጠን ፊታችንን ወደ ኋላ አንመልስም በማለት ጉራዲያቸውን እየመዘዙ ከጠላት መካከል በመግባት ጠላታቸውን እየጨፈጨፉ በጀግንነት ወደቁ፡፡[6] የተንቤን ጦርነት የካቲት 15 ቀን 1928 ዓ.ም እንዲህ ተፈፀመ፡፡

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 10፡፡
2. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 74፡፡
3. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 213፡፡
4. ሞገስ ክፍሌ፣ *የሞሶሎኒ ምስጢር*፣ ገጽ 79፡፡
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 88-89፡፡
6. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 242፡፡

# ምዕራፍ አስር
# የአምባራዶም ጦር ግንባር

የአምባራዶም ጉራ ጠላትን አስፈራርቶት ነበር፡፡ ከዚህም የተነሣ ሞሶሎኒ ለባዶሊዮ ከባድ ማስጠንቀቂያ ሠጠው፡፡ ማስጠንቀቂያውም ራስ ሙሉጌታ ከሌሎች የኢትዮጵያ የጦር አዛገች ሁሉ አስፈሪ መሆናቸውን ገልጾ ጦሩ ምንም ሳይፈራ መዋጋት እንደሚገባው ያስረዳ ነበር፡፡[1] ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ደግሞ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣ አምባራዶም እስከ አልተያዘ ድረስ በመቀሌ ላይ የኢጣልያኖች ይዞታ አስተማማኝ አለመሆኑን እየገለፀ፣ አምባራዶም በቶሎ እንዲያዝ ይወተውት ነበር፡፡[2]

የጠላት ጦር ራስ ሙሉጌታን ለማጥቃት እና አምባራዶምን ከኢትዮጵያ ሠራዊት አስለቅቆ ለመያዝ የሚችልበትን መንገድ ቀየሰ፡፡ ለመጀመሪያው ቀን 1ኛው ክፍለ ጦር ከነበረበት ተንቀሳቅሶ የተቻለውን ያህል እንዲገፋ፤ በሚቀጥለው ቀን ደግሞ 2ኛውና 3ኛው ክፍለ ጦሮች ተንቀሳቅሰው ከአምባራዶም በስተደቡብ እንዲሠፍሩ ባዶሊዮ ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ ጦርነቱንም እሱ ራሱ እንደሚመራ ቃል ገባ፡፡ የጠላትን ጦር መጠጋት በመመልከት የኢትዮጵያ ጦር በበኩሉ ዝግጅት አደረገ፡፡ አዲ አማራግ፣ ተግታጋ በተባሉት ቦታዎች ላይ ከየካቲት 1 ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት 5 ቀን ድረስ ውጊያ ሲካሄድ ሰነበተ፡፡ በተለይ የካቲት 4 ቀን ሌሊት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከኢጣልያን ምሽግ ውስጥ ገብተው የተቃና ሥራ ሠሩ፡፡[3]

የአምባራዶም ዋናው ጦርነት የካቲት 5 ቀን 1928 ዓ.ም ጠዋት በ3 ሰዓት ተከፈተ፡፡ ጦርነቱ የተጀመረው እንዳግብር በተባለው ቦታ ላይ ሲሆን የኢጣልያን የጦር አዛገች ጦርነቱን በዕቅድ ለመምራት እስኪቸገሩ ድረስ የኢትዮጵያ ጦር ግራ አጋባቸው፡፡ ጥማቸውን የሚያረካ ጠመንጃ አልነበራቸውምና፣ ኢትዮጵያውያኑ በጠመንጃ ከመታኮስ ይልቅ ሰይፍና ጉራዴአቸውን እየመዘዙ በሩጫ ከጠላት መካከል እየገቡ መጨፍጨፍ ቀናቸው፡፡

ጦርነቱ ሙሉ ቀን ዋለ፤ በማግስቱ የካቲት 7 ቀንም ቀጠለ፡፡ ራስ ሙሉጌታ በጥሩ ዘዴ ውጊያውን መሩ፡፡ ባዶሊዮ ወታደሩን አንድ አቅጣጫ ሲያሲዝ፣ እሳቸው አቅጣቸውን ወዲያው ለውጠው ሌላ አቅጣጫ ፈጥረው ጠላት ያተኮረበትን ቦታ ባዶ ያደርጉበታል፤ ካላሰበና ካልተዘጋጀበት አቅጣጫ ይወጉታል፡፡ በዚህ ዓይነት ዘዴ ራስ ሙሉጌታ ባዶሊዮ ራሱን ጭምር ግራ አጋቡት፡፡

የካቲት 7 ቀን የኢጣልያ ጦር አምባራዶምን አስለቅቆ ለመያዝ ከባዶሊዮ ትዕዛዝ ተሰጠ፡፡ አይሮፕላኖችም የራስ ሙሉጌታን ሠፈር እንዲደበድቡ ተደረገ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር በየፊታውራሪዎች እየተመራ በርትቶ



ተዋጋ፡፡ ጦርነቱ ሙሉ ቀን ዋለ፡፡ እልቂቱ ከመጠን በላይ ስለሆነ ራስ ሙሉጌታ ወደኋላ አፈገፈጉ፡፡ ጠላትም የካቲት 7 ቀን ማታ አምባራዶምን ያዘ፡፡ ራስ ሙሉጌታ ወደ ኋላ ቢመለሱም ጦርነቱ በቢትወደድ መኰንን ደምሰው መሪነት ቀጠለ፡፡ የኢትዮጵያ ጀግኖች እስከ የካቲት 12 ቀን ድረስ ሽንጣቸውን ገትረው እስከ መጨረሻ ተዋጉ፡፡

በጦርነቱ ፍፃሜ ላይ የታየው ሁኔታ አስገራሚ ነበር፡፡ ሠላሳ ስድስት ነጭ መኮንኖችና 621 ነጭ ወታደሮች ከ154 ጥቁር ወታደሮች ጋር ሞቱ፡፡ የጭፍሮች ማነስ በዚህ ጦርነት ላይ በሙሉ ልብ አለመዋጋታቸውን ያመለክታል፡፡ በኢትዮጵያ በኩል የሞቱት ከ6000 አላነሱም፡፡ በምድር ከተደረገው ውጊያ ሌላ 170 አይሮፕላኖች የቻሉትን ያህል እየተመላለሱ 396 ቶን ከባድ ፈንጂ ጥለዋል፡፡ አንድ አይሮፕላን በኢጣልያን የሕክምና ቡድን ላይ በስሕተት አምስት ቦምብ ጣለች፡፡ ከሕክምናው ቡድን በሕይወት የተረፈ አልተገኘም፡፡ አንድ መቶ ያህል ሰዎች ሞቱ፡፡ በኢትዮጵያውያን በደረሰው ጥቃት ለደረሰው ጉዳት፣ ይህንን ማስረጃ ማድረግ ይቻላል፡፡

የጣልያን አይሮፕላኖች የራስ ሙሉጌታ ጦር የደረሰበትን ማወቅ አቃታቸው፡፡ አካባቢውን ሁሉ እየተዘዋወሩ ዝቅ እያሉ በመብረር መረመሩ፡፡ ምልክት እንኳን አላገኙም፡፡ ራስ ሙሉጌታ ያፈገፈጉት ቀጥተኛውን መንገድ ይዘው አልነበረም፡፡ ወደ አዘቦ ነበር የወረዱት፡፡ ራስ ሙሉጌታ በደህና ጉዞ ላይ እንዳሉ ነበር የልጃቸውን ሞት ሰምተው የተመለሱት፡፡

ከሰሜን እየተነሣ ኢትዮጵያን ለሚወጋ ጦር መከላከያ ሆነው ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የተዘረጉ ብዙ ተራሮችና ሸንተረሮች አሉ፡፡ ከእነዚሁ ተራሮች ዋነኛው አምባላጌ የሚባለው ነው፡፡ ይህ ተራራ ከሰሜን ለሚያጠቃና ከደቡብ ለሚከላከል ወሳኝነት ያለው የጦር ቦታ ነው፡፡ ይህንን የመሰለው የጦር ጉራ አንዳችም ጥንቃቄ ሳይደረግለት ቀርቶ ያለምንም ችግር የኢጣልያን ጦር ወጣበት፡፡ ለኢትዮጵያም ጦር ታላቅ ሽንፈት ሆነ፡፡ የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ከዚህ ላይ ተሳስተዋል፡፡

ይህ ጦርነት እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አገላለጽ የመጨረሻው የታላቁ ጠላታችን ጦርነት ነበር፡፡[4] ከኢትዮጵያ ወገን የወደቀው ከ5000 አላነሰም፡፡ ከጠላት ወገን 68 መኰንኖች 332 ነጭ ወታደሮች፣ 873 የቅኝ ግዛት ወታደሮች ሞተዋል፡፡ ሰባ አይሮፕላኖች ድብደባ አካሂደው 34 ቶን በምብና የጋዝ መርዝ የጣሉ ሲሆን፣ ከእነዚሁ ውስጥ 36 ተመትተው ወድቀዋል፡፡

**<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>**

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 99፡፡
2. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ*፣ ገጽ 242፡፡
3. ዝኒ ከማሁ፡፡
4. ዝኒ ከማሁ፣ገጽ 257፡፡

# ምዕራፍ አሥራ አንድ
## የኦጋዴን ጦር ግንባር

እንደተገለፀው ዋናው የጦር ግንባር ሰሜን ነው ቢባልም፤ ጦርነቱ የተቀሰቀሰው በኦጋዴን ግዛት ወልወል በተባለው ቦታ ነበር። የታሪኩ ሂደት በአጭሩ ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ወልወል ከኢትዮጵያና ከደቡብ ሶማልያ ወሰን ወደ 100 ኪሎ ሜትር የምትርቅ የኢትዮጵያ መሬት ናት። የምትቀርበው ለሰሜን ሶማልያ ነው። በኢጣልያ ጠብ አጫሪነት ግጭት እስከ ተቀሰቀሰበት ጊዜ የይገባኛል የግዛት ጥያቄ ማንም አንስቶባት አያውቅም። በዚያን ጊዜ የእያንዳንዳቸው ጥልቀት እስከ 60 ሜትር የሚደርሱ 359 የውሃ ጉድጓዶች በዛ ነበሩ።

በኢትዮጵያና በሰሜን ሶማልያ መካከል ያለው የግጦሽ መሬት ይከለል የሚል ጥያቄ ከእንግሊዝ ወገን እንደ ተነሳና ጥያቄው ምን ሴራ ጎርሶ እንደተቀሰቀሰ በሌላ ምዕራፍ ተገልፆአል። ከዚህ የምንመለከተው ሂደቱን ብቻ ይሆናል።

የኢትዮጵያና የእንግሊዝ ወሰን ተካይ ቡድን ህዳር 14 ቀን 1927 ዓ.ም ወልወል ሲደርስ ጣልያን በምሥጢር ወታደሮች አስገብታ ከጥቂት ጊዜ በፊት ባንዲራዋን አሰቅላ ኖሮአል። ሁለት መቶ ሃምሣ ባንዶች ከዚህ አትለፉ ብለው ወሰን ተካዩን ቡድን አስከለከሉ። በኢትዮጵያ ወታደሮችና በኢጣልያ ባንዶች መካከል ፍጥጫ ተጀመረ። ፍጥጫውን ለማርገብ እንግሊዞች ተጠቂዎቹን፣ ኢትዮጵያኑን ተለማመጡ። አጥቂውን ለማስታገስ በኢትዮጵያዊው ተከላካይ በደጃዝማች ተሰማ ባንቲ፣ በእንግሊዝ ዳኛ በኮሎኔል ክሊፎርድና በአጥቂ የኢጣልያ ጦር አዛዥ በሻምበል ሮበርቶ ችማሩታ መካከል ህዳር 15 ቀን የመልእክት ልውውጥ ቢደረግም፤ ችማሩታ ከነበረበት ቦታ ንቅንቅ የማይል ሆነ። የእንግሊዝ ወሰን ተካዮች ኢጣልያ የዓለምን ሕግ ጥሳ፣ ወሰን አልፋ የኢትዮጵያን ግዛት በኃይል መያዝዋን አስታውቀውና ለኢትዮጵያ መንግሥት በግልባጭ አሰምተው ከአደጋ ለመዳን ሀውድ ወደተባለው ቦታ አፈገፈጉ። ከዛም የኢጣልያ አይሮፕላኖች የኢትዮጵያ ጦር ከሠፈረበት በግርስገቡ አካባቢ ማንዣበብና ለማስፈራራት መትረየስ መተኮስ አበዙ።

ነገሩ በዚህ ሁኔታ በመፋዘዝ ሰነበተ። ህዳር 25 ቀን 1927 ዓ.ም ችማሩታ ለደጃዝማች ተሰማ ባንቲ አንድ ደብዳቤ ላከ። ደብዳቤውም የኢትዮጵያ ወታደሮች ለመንቀሳቀስ በመዘጋጀት ላይ ለመሆኑ መረጃ እንደደረሰው ጠቅሶ "ለመወያየት" መቀረጡን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ነበር። ግጭቱን እንዲፈጥር ከኢጣልያ ባለሥልጣኖች ከተፈቀደለት በኋላ የፃፈው የጠብ መጫሪያ መሆኑ ነው።



ምንም ችግር ሳያጋጥም እንዲሁም የኢትዮጵያ ጦር አንዳች እንቅስቃሴ ሳያደርግ ህዳር 26 ቀን 1927 ዓ.ም ረቡዕ፣ ከቀኑ በ9:00 ሰዓት ባንዳዎች በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይ በድንገት ተኩስ ከፈቱ። በምድር ታንኮች፣ በሰማይ አይሮፕላኖች ሥራ ቀጠሉ። ኢትዮጵያውያኑ በጀግንነት ተከላከሉ። ፊታውራሪ ዓለማየሁ ጉሹና ሌሎች 93 ኢትዮጵያውያን በጀግንነት ወደቁ። 127 ባንዳዎች ተገደሉ። ባላምባራስ አሊ ኑር የሠሩትን የጀግነት ሥራ ሠሩ።[1] የወልወል ግጭት ከኢጣልያ ወራሪ ጋር፤ እንደዚሁም የባላምባራስ አሊ ኑር ጀግንነት ከወልወል ግጭት ጋር በታሪክ ሲወሳ ይኖራል።

ወሰኑን የመከለሉ ሥራ ቀረና ሌላ ዓይነት የዲፕሎማቲክ ንትርክ ተጀመረ። ኢጣልያም ወልወልን የማትለቅ ሆነ። የጦርነቱ እሳት በመቀዝቀዝ ፈንታ እየተጋጋመ ሄደ።

በዚህ ጊዜ ወሉል ጂሌ የተባለው ቀንደኛ የሶማሌ ባላባት ተወራሪዋን ኢትዮጵያን ክዶ ከኢጣልያኑ ወራሪ ጐን ቆመ። ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት በግርስገቡ ከጠላት ጋር ፍጥጫቸውን ቀጠሉ። የኢጣልያን ጦር በባዶሊዮ አዛዥነት በትግራይ ማጥቃት ሲጀምር፣ በጀኔራል ግራዚያኒ መሪነት በኦጋዴን ላይ ወረራ ተጀመረ። ጦርነቱም በልዩ ልዩ መኪናዎች የተደገፈ፣ በታንክና በአይሮፕላን የሚዋጋ ነበር።

የኢትዮጵያ ሠራዊት በደጃዝማች ነሲቡ ዘአማኑኤል የጦር አበጋዝነት ተሠለፈ። የሐረር፣ የአርሲ፣ የኢሉባቡር፣ የባሌ ጦር በኦጋዴን፣ የሲዳሞ ጦር በቦረና በኩል ለመከላከል ተዘጋጀ። የከፋ ጦር በቦረና ከተሰለፈው የሲዳሞ ጦር ጋር ተቀላቀለ።[2]

በዚህ ግንባር የተሰለፈው ጦር የአደረጃጀት፣ የስትራቴጅና የአመራር ችግር ነበረበት። በስትራቴጂው በኩል ሲታይ ቆላው በረሃማ ነው። ጦሩ ለመከላከል ከዚያ ሲገባ ውሃና ምግብ አያገኝም። መገናኛ ስለሌለው ከቀለበት ውስጥ ከገባ ፈልቅቆ በመውጣት መዳን አይችልም። ከበረሃው ወርዶ ካልተዋጋ ደግሞ ሀገሩን ኢጣልያኖች ይይዙታል። ይህም ለኢትዮጵያ ጥቃትና ጉዳት ነው። በአደረጃጀት ሲታይ ደግሞ ርስበርሳቸው ግንኙነት በሌላቸው ብዙ አዛዦች የሚመራ ነው። በአመራር ረገድ የደጃዝማች ነሲቡ የአበጋዝነት እንጂ የአዛዥነት ሥልጣን የላቸውም። አዛዡ ንጉሡ ነገሥቱ ናቸው። እሳቸውም ከሰሜኑ የጦር ግንባር የሚተርፍ የአመራር ኃይል አልነበራቸውም። የኦጋዴን ጦር ግንባር የሚንቀሳቀሰው በእነዚህ ችግሮች ውስጥ ተተብትቦ እንደታሠረ ነበር። ያም ሆኖ የኢትዮጵያ ጦር ሀገር ከመልቀቅ፣ ከበረሃ ገብቶ ጠላቱን መዋጋትን መረጠ። በቦረና እስከ ዶሎ፣ በባሌ እስከ ኢሚ፣ በጅጅጋ እስከ

ቆራሄ ወረደ። ከንጉሠ ነገሥቱ የተሰጠው ትዕዛዝ የራሱን ግዛት ይዞ ጠላት እስኪጠጋ እንዲጠብቅ ነበር።[3]

የኢጣልያ ጦር በጥቅምት ወር 1928 ዓ.ም ከሞቃድሾ ተነስቶ በሰፊው፣ በሙሉ ኃይሉ ተንቀሳቀሰ። በሦስት ታላላቅ ረድፍ የተከፈለ ነበር። ዋናው ረድፍ በፈርፌር፣ በዛላቦ፣ በቀብሪደሐር፣ በደገሐቡር፣ በጅጅጋ ሐረር ገብቶ ድሬዳዋን የሚይዝ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ በኢሚ ወደ ደጋው የባሌ ግዛት የሚወጣ ነበር። ሦስተኛው ደግሞ በደሎ፣ በነገሌ አድርጐ ይርጋ ዓለም ገብቶ ደቡቡን ሀገር የሚይዝ ነበር። ጦሩ በዚህ በተሰጠው ዕቅድ መሠረት ወረራውን ቀጠለ።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ወራሪውን ለመመከት የሚቻለውን ሁሉ አድርጐ፤ በፈርፌር በኩል የመጣውን ጦር ቆራሄ ላይ ሲደርስ ጦርነት ገጠመው። ቆራሄ ከሱማሌና ከደቡብ ሁለቱ ወንዞች ያሉበት ለጥ ያለ ሜዳ በመሆኑ ለጠላት ታንክና አይሮፕላን አመች ቢሆንም የኢትዮጵያ ሠራዊት በጀግንነት ተዋጋ። ቀኝአዝማች አፈወርቅ መሬቱን ቆፍረው ነበርና በኃይል ተዋጉት። ጣልያን ሁለት ጊዜም ቢመጣ፣ ሁለት ጊዜም ተሸንፎ ተመለሰ። ጐሬውን በእግር ጦርነት ለመስበር እንደአልቻለ በተረዳ ጊዜም የጦሩን ቦታና አካባቢውን በአይሮፕላን ደበደበ። ጥቅምት 23 ቀን ባካሄደው ድብደባ ጀግናው ግራዝማች አፈወርቅ በቦምብ ፍንጣሪ ቆሰሉ። እሳቸውም አዛዥ ጠይቀው እስኪደርስላቸው ከቦታቸው ቆይተው ወታደሩን አዋጉ። ፊታውራሪ በሌላ ሲተኩላቸው ወደ ደገሐቡር ተመልሰው ከዚያ አረፉ። ስለፈፀሙት አገልግሎት ከዕረፍታቸው በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ከንጉሠ ነገሥቱ ተሰጥቷቸዋል። የቆራሄ ጀግና አፈወርቅ ደጃዝማች እየተባሉ ስማቸው በታሪክ በክብር ሲጠራ ይኖራል።

ይህንን ግንባር ንጉሠ ነገሥቱ ከህዳር 9 እስከ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ጐበኙ። ጉብኝቱ ለአጭር ጊዜ ቢሆንም ጦሩን ሳያጠናክረው አልቀረም። ነገር ግን የባሌና የቦረናው ግንባሮች ይህንን አላገኙም።

ቀደም ሲል ለዘመቻ በተጠራ ጊዜ የኢሉባቡር ጦር አዲስ አበባ ድረስ መጥቶ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት በሰልፍ ከአለፈ በኋላ በባቡር ተጓጉዞ ድሬዳዋ ገባ። ከዚያም ቀርሣ ከተባለው ቦታ ጥቂት ቆይታ ከአደረገ በኋላ ወደ አበከር ሄዶ ከዚያም ለሐረር ከተማ ሰልፉን እያሳየ ውሃ፣ ውሃ በሚል ነጋሪት እየተመራ፣ ተጉዞ ካራማራ ሠፈረ። ቁጥሩ ከ3000 የሚበልጥ ነበር። በዚህ ቦታ ከሁለት ወር በላይ ስለተቀመጠና በውሃ ጥም፣ በረሃብ፣ በበሽታ ስለተዳከመ ወደ ጦር ግንባር ለመግባት በራሱ አነሳሽነት ወሰነ። አለቆችም የጦሩን ጥያቄ መቀበል ግድ ስለሆነባቸው ተስማምተው እንዲዘምት አደረጉ። ደገሐቡር ላይ የጉሩ፣ የጋሙ ጐፋ፣



የአርሲና የኩሎ ጦር ሹማምንት የጋራ ስብሰባ አድርገው የጦር እቅድ አወጡ። ዕቅዱም የኢሉባቡር ጦር በደጋሐመዶ፣ የኩሎ ጦር ወደ ጅጅጋ ተመልሶ ደጀን እንዲሆን፣ የሐረርጌ ጦር ቀብሪደሐር ሄዶ ወደጥናን ለተላከው ጦር ደጀን እንዲሆን፣ የአርሲ ጦር ደገሐቡር ቆይቶ ለሐረርጌ ጦር ደጀን /የደጀን ደጀን/ እንዲሆን ነበር። ጦሩ ጀነጋብ እንደደረሰ በአሰላለፍ ረገድ ቀኙን እኔ ልያዝ፣ ለእኔ ይሁን በመባባል ለጠብ ተቃረበ። ይህም በውይይት ተፈትቶ ለጦር ተሰለፈ።

የኢጣልያ ጦር በአምስት ጀነራሎች የሚመራ ነበር። ሚያዝያ 7 ቀን፣ በ11 ሰዓት ጥዋት ጦርነት ተከፈተ። ጦርነቱ ጀነጋብ ወንዝ ላይ ነበር። ጠላት በታንክ ቢንቀሳቀስና በአይሮፕላን ቢደበድብም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም። ከረቡዕ አንስቶ እስከ እሑድ ድረስ አምስት መአልትና አምስት ሌሊት ተዋጋ።[4] አብዛኛው ወታደር በዚሁ ጉራ ላይ ብቻ አለቀ። አለቆቹ ግን በደህና ተመለሱ።

ፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴ በደጃዝማች አፈወርቅ እግር ከተተኩ በኋላ ጦርነቱ ቀጠለ። ፊታውራሪ ጓንጉል የደረሱት 500 የሠለጠነና በጥሩ ሁኔታ የታጠቀ ጦር ይዘው ነበር። የመጀመሪያውን ግጥሚያ ህዳር 1 ቀን ነሐሴ በተባለው ቦታ አደረጉ። ይህ ቦታ የፋፈን እና የጀረር ወንዞች የሚገናኙበት ነው። ጠላት በአባባቢው መኖሩ እንደታወቀ፣ ዋናው ጦር ወደ ኋላ እንዲያፈገፍግ አድርገው 40 ወታደር ብቻ ይዘው ነበር ጦርነቱን የጀመሩት። አራት ታንኮች በየተራ ቢመጡባቸው ከአሸዋ ውስጥ እስኪዘፈቁ እየጠበቁ እንዳይነቃነቁ በመትረየስ ጥይት ጠዘጠዙአቸው። ጣልያኖች መትረየስ ቢተኩሱ፣ የእጅ ቦምብ ቢወረውሩ፣ አካበቢውን በቤንዚን ቢረጩ አንዳች ማድረግ የማይቻላቸው ሆነ። ከሙሉ ቀን ውጊያ በኋላ ጣልያኖች ሸሹ። ኢትዮጵያውያኑ 66 ጠላት ገደሉ። ሰባቱ ኢጣልያውያን ነበሩ። አራቱ ታንኮች ተማረኩ። በኢትዮጵያውያኑ በራሳቸው ላይ የደረሰው ጉዳት ትንሽ ነበር።

ነገር ግን ሌላ ያልታሰበ አደጋ ደረሰ። በአንዱ ታንክ ወስጥ ሰጠኝ የተባለ ወታደር አንድ ዕቃ አግኝቶ አመጣ። ምን እንደሆነ አልታወቀም እንጂ የእጅ ቦምብ ነበር። ምን እንደሆነ ባልታወቀ ዕቃ የተደናገሩት አዛገሮች ወዲያው እንዲጥል አዘዙት። ያ ወታደር እዚያው እመካከላቸው ስለጣለው ቦምቡ ፈነዳ። ሰጠኝና ሌሎች ሰባት ወታደሮች ወዲያው ሲሞቱ፣ ፊታውራሪ ጓንጉል ኮላሴና ወንድማቸው አቶ ኃይለ ማርያም ኮላሴ ቆሰሉ። አቶ ኃይለማርያም ደገሐቡር ሕክምና ጣቢያ ሲሞቱ፤ ጓንጉል ወደ አዲስ አበባ ለሕክምና ተወሰዱ። ጦርነታቸውም የአንድ ቀን ብቻ ሆኖ ቀረ። ወታደሩም ተበተነ።[5]

በዚህ ዓይነት በሩ ለጠላት ከተከፈተ በኋላ፤ ያለቀው አልቆ፣ የተረፈው የኢትዮጵያ ጦር የተቻለውን ያህል እርስበርሱ በመተባበር፣ እየተከላከለ ወደ ኋላ ተመለሰ። ጠላት መጀመሪያ ቀብሪደሐርን ከዚያም ደገሐቡርን ያዘ። የኢትዮጵያ የጦር አለቆች የንጉሠ ነገሥቱን መሄድ እንደሰሙ በየፊናቸው በበርበራና በጅቡቲ በኩል ከሀገር ወጥተው ነበርና፤ ጠላት ወደ ጅጅጋ በሚያደርገው ግሥጋሴ እምብዛም ችግር አላጋጠመውም።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 12-16
2. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀ.ኃ.ሥ.* ፣ገጽ 233።
3. *ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 198-203።
4. መኰንን እንዳልካቸው፣ *አልምትኩም ብዬ አልዋሽም*፣ ገጽ 294-302
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 142-44።



# ምዕራፍ አሥራ ሁለት
# የቦረና ጦር ግንባር

በቦረና ግንባር የተሰለፈው አብዛኛው ሠራዊት በራስ ደስታ ዳምጠው የሚመራው የሲዳሞ ጦር ነበር። በደጃዝማች ወልደ ሚካኤል የሚመራውም አብሮት ነበር። በዘመናዊ የጦር ስልት የሠለጠኑ ወጣቶችም ነበሩ። ጦሩ ጥቅምት 5 ቀን 1928 ዓ.ም ከይርጋለም ተንቀሳቀሰ። በጥቅምት 7 ቀን ሀገረ ሰላም ደረሰ። ከዚያም መንገድ እየተመነጠረና ለእግረኛ እንደሚስማማ እየተደለደለ ጉዞ ቀጥሎ መልካ ዳዱ ከተባለው የገናሌ ወንዝ ላይ ጦሩ ሠፈረ። ይህ ቦታ ባሌን እና ሲዳሞን የሚያዋስን ከመሆኑም በላይ ውሃ ያለበት፣ አየሩም ለስላሳ ሆኖ ለጦሩ ምቹ ነበር። ዋሻ ተዘጋጅቶ መሣሪያና ስንቅ ከዚያ ተከተተ።

ጥቅምት 21 ቀን 1928 ዓ.ም ዓርብ መልካ ዳዱ ላይ የነበረው የስዊድን ቀይ መስቀል ሠፈር በቦምብ ተደበደበ። ሌላ የአይሮፕላን ድብደባ ታህሣሥ 7 ቀን አሚኖ በተባለው ቦታ ተካሄደ። በድንገት የደረሰ ድብደባ ስለነበር በሰውና በከብት ላይ ጉዳት አስከተለ። ጦሩም ሀሳቡ ተንጀዋለለበት። እንዋጋ በሚለው የአባቱ ልጅና፣ እናፈግፍግ በሚለው የእናቱ ልጅ መካከል ከባድ ክርክር ተካሄደ። ከክርክሩ መጠን የተነሳ የጦር ዕቅድ ሳይተካከልለት ቀረ። ቢሆንም ትግሉ ቀጠለ። ግራዝማች ገብሩ /ኰሎኔል/ ሰባት ራሳቸውን ከጣልያን ከድተው ከኢትዮጵያ ጦር ተቀላቀሉ። ይህም ለኢትዮጵያ ጦር አዲስ የውጊያ ስልት አስገኘ።

ታህሣሥ 21 ቀን 1928 ዓ.ም አሚና በተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ጦርነት ተከፈተ። ለመጀመሪያ ጊዜ ድል የኢትዮጵያውን ሆነ። ጠላትም ሸሸ። ታህሣሥ 23 ቀን አንድ ሰላይ አይሮፕላን በመላክ ጠላት አካባቢውን ሰለለና፣ የኢትዮጵያ ጦር በተደናገረበት ጊዜ ጦር በማቅረብ አዲስ ውጊያ ከፈተ። ጠላት ብዙ የሱማሊያ ወታደርና ታንክ አቀረበ፤ ኢትዮጵያውያን ጠንክረው ተዋጉ። አንድ ታንክ ቆርጠው አስቀሩ። ነገር ግን ጠላት ረዳት ታንክ በመላክ አስጐትቶ ወሰደው። የኢትዮጵያ ጦር ሁኔታውን ከገመገመ በኋላ ከአሚና ወደ መልካ ዳዱ ተመለሰ። ይህም ለጠላት መግቢያ አንድ በር ከፈተ።

ሌላው የጦሩ ሜዳ መልካ ዳዱ ሆነ። የጠላት ጦር እየገፋ ስለመጣ የኢትዮጵያ ጦር ለመመከት ወሰነ። ጦሩ በሦስት ሻምበሎች ተደለደለ። ለሻምበሎችም ረዳቶች ተመደቡላቸው። ሻምበሎቹ ራሳቸው ነገሌ ላይ እንዲጠባበቁ ተደረገ። ጦር ለውጊያ ተዘጋጀ። ጀነራል /ማርሻል/ ግራዚያኒ ጦሩን እየመራ መጣ። እዚህ ላይ የእኛ ሻምበሎች

በአዋጊነት ወደ ኋላ ሲቀሩ ግራዚያኒ ራሱ ከጦርነቱ መግባቱን ማጤን ይገባል፡፡

በጠላት በኩል የተሰለፈው የኢጣልያ ተወላጅ፣ ሶማሊያዊ እና ከሊቢያ የመጡ ነበሩ፡፡ ታንኩን በመሬት፣ አይሮፕላኑን በሰማይ ግንባር ቀደም አድርጐ መጣ፡፡ በሦስት ሻምበል የተመደበው የኢትዮጵያ ሠራዊት እርስበርሱ ተቀላቅሎ መከተ፡፡ ከባድ ውጊያ ተካሄደ፡፡ የጦርነቱ ሚዛን አጠራጣሪ ሲሆን፤ ግራዚያኒ መልካ ዳዲን በእግረኛ ጦር ለመክበብ ሞከረ፡፡ ነገር ግን ራስ ደስታ ቁልማዩ የተባለውን ገዥ ቦታ ገስግሰው ያዙበት፡፡ የኢትዮጵያ ልጆች "እኛ በዚህ ሥፍራ እንደ ቅጠል ረግፈን፣ እንደ ሻሽ ተነጥፈን ነው እንጂ፤ እንዲያው ጠላት አይገባም፡፡" ብለው ምድር ሰቅስቀው ተዋጉ፡፡ ከዋሻው ውስጥ የተቀመጠውን መሣሪያና ስንቅ እያወጡ ተጠቀሙበት፤ በተቻላቸው ሁሉ ተከላከሉ፡፡ ጠላትን በሩቅ በጥይት፣ በቅርብ በጨበጣ፣ በሰይፍና በጉራዴ ጨፈጨፉት፡፡ መቶ አለቃ በለጠ አንድ ራሱን አንድ መትረየስና ሦስት ሣጥን ጥይት ማረከ፡፡ ሌላውም ጀግና የየራሱን አገኘ፡፡ ግራዚያኒ የኢትዮጵያ ጦር እንደአልተበገረለት ባየ ጊዜ፤ በከሀዲዎች አማካኝነት እና በግብረ አበሮቹ ጠቋሚነት በመንገሾ ያለውን፣ መሣሪያ የተቀመጠበትን ዋሻ ማወቅ ስለቻለ፤ በባሌ በኩል አዙሮ በመድፍ መደብደብ ያዘ፡፡ ዋሻውም ፈርሶ ተደፈነ፡፡ በውስጡ የነበረው መሣሪያና ስንቅ ተቀበረ፡፡

ከጥር 4 ቀን ጀምሮ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት ያለአንዳች ዕረፍት የተካሄደው ውጊያ በጠላት አሸናፊነት ተደመደመ፡፡ ድል ወደጠላት የዞረው 1ኛ/ ዋሻው በመናዱና በውስጡ የቀረው ስንቅና ትጥቅ በመቀበሩ፤ 2ኛ/ ብዙዎች ጀግኖችና የጦር መሪዎች በመውደቃቸው፤ 3ኛ/ የጠላት ጦር ከምድር በታንክ፣ በሰማይ በአይሮፕላን በሚጥለው መሣሪያ ብልጫ በማግኘቱ ነበር፡፡ እዚህ ላይ ልናስተውለው የሚገባው ጉዳይ ግራዚያኒ ራሱ በጦርነት ውስጥ ባይኖር ኖሮ የኢትዮጵያ ግምጃ ቤት የነበረውን ዋሻ ለማግኘትና ለማስደብደብ አይችልም ነበር፡፡ ዋሻውን ባያስደበድብ ኖሮ ለድል አይበቃም ነበር፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ሠራዊት ከባድ መሣሪያውን ከገናሌ ወንዝ ውስጥ ጥሎ ተመለሰ፡፡[1]

እዚህ ላይ ጠላት ይህንን ጦርነት እንደምን እንደ አቀነባበረው መመልከት ይገባል፡፡ ሞሶሎኒና የጦር አዛዦቹ አስበው የሚሠሩ እንጂ በመላ የሚንቀሳቀሱ አልነበሩም፡፡ በተለይም ግራዚያኒ፡፡ ግራዚያኒ ቀደም ብሎ ዶሎ በመግባት ጦሩን ማጠናከርና የውጊያ ሥልት መቀየስ ያዘ፡፡ ከዛም ጦሩን ከሦስት ከፈለው፡፡ በአንድ ጄነራል የሚመራ ጦር በገናሌ የፍያ ሸለቆ እስከ ሣንዶር እንዲገፋ፤ ሁለተኛው ጦር በፊልቱ አድርጎ ወደ



በነገሌና ማኞ እንዲያልፍ፤ ሶስተኛው ደግሞ ባደዋ ፓርማ በኩል ወደ መልካ ሙሪ እንዲገባ ደለደለ፡፡ ጦሩን እንዲህ ከአሰለፈ በኋላ አዛዦችን ሰብስቦ "…ኢትዮጵያውያን ለኢጣልያውያን አስደግድጉአቸው" በማለት አዘዛቸው፡፡

ቀጣዩ ጦር ሜዳ፣ ቁልማዩ ሆነ፡፡ ይህ ቦታ በአካባቢው ከነበሩት ቦታዎች ሁሉ ለጦርነት ተስማሚ ነበር፡፡ ራስ ደስታና ረዳቶቻቸው ጦሩን በረድፍ፣ በረድፍ ደለደሉት፡፡ አዛዦችም ከሠራዊታቸው ጋር ቆሙ፡፡ ጣልያን ከ60,000 የማያንስ ወታደር፣ ከ100 የማያንሱ ታንኮች፣ ከ60 የሚበልጡ መድፎች፣ ከ200 የማያንሱ መትረየሶች አቀረበ፡፡ በሃምሣ ሁለት አይሮፕላኖች እየተረዳ መጣ፡፡ ጦርነቱ መልካ ዳዲ ላይ ጥር 4 ቀን ጠዋት ሲከፈት፣ የቁልማዩው ውጊያ ከቀኑ ልክ 6 ሰዓት ተጀመረ፡፡



በዘመናዊ ስልት የሰለጠኑ ወጣቶችን ያካተተው የደቡቡ ግንባር ለጣልያን ታላቅ ፈተና ነበር፡፡

ከሁለቱም ወገን በሚተኮሰው መሣሪያ ምድር የተገለባበጠች መሰለ፡፡ በሁለቱም ወገን የጦርነቱ እቅድ ውጥንቅጡ ወጣ፡፡ ራስ ደስታ ዳምጠውና ደጃዝማች በዛብህ ስለሺ ከጦር ውስጥ ገብተው ተዋጉ፡፡ የኢትዮጵያ ወታደሮች ከታንኩ ላይ እየወጡ ጠላታቸውን ወደ ውስጥ ሽቀሸቁት፡፡ ጦርነቱ እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ቆይቶ ጠላት ተሸንፎ ወደ ኋላው ተመለሰ፡፡ እነ ጄነራል በርጉዝሊ የቆሰሉትና ሌሎችም ብዙ ኢጣልያውያን የሞቱት ከዚህ ጦርነት ላይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ደስ አለው፡፡ ምርኮው፣ የጦር ጀብዱው ሲሰማ እኩለ ሌሊት ሆነ፡፡



በዘመናዊ ስልት የሰለጠኑ ወጣቶችን ያካተተው የደቡቡ ግንባር ለጣልያን ታላቅ ፈተና ነበር።

ለጥር 5 ቀን አጥቢያ፣ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት እንደገና ተኩስ ተከፈተ። ግራዚያኒ ካባሊየር የተባሉ አዲስ የነጭ ወታደሮች አቀረበ። ጦርነቱ ከትናንቱ የበለጠ ሆነ። የልብ ልብ የተሰማው የኢትዮጵያ ጦር ጠላቱን ያለ እንዳች ዕረፍት ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት መውጋቱን ቀጠለ። የቁልማዩ ሜዳ ሬሣ ለበሰ። ጠላት የመልካ ዳዲን ጦርነት ስለአሸነፈ በዚያ የነበረውን ጦር ወደ ቁልማዩ አዞረው። በዛም የኢትዮጵያም ሠራዊት እንደ ቅጠል ረገፈ። ራስ ደስታ በነፍስ አባታቸው በአባ ወልደ ፃድቅ ግዝት ጥቂት የተረፉ ወታደሮቻቸውን ይዘው ወደ ኋላ ተመለሱ። ሦስት መኪናዎች ስለተገኙ የቅርብ የሥራ ጓደኞቻቸውን፣ ታቦቶቹንና ቁስለኞቹን፣ ምርኮኞችና መድፎቻቸውን፣ መትረየሶቻቸውን አስጭነው ወደ ቦረና ነገሌ ተመለሱ።[2]

የቦረና ግንባር አጠቃላይ ሁኔታ ደሴ ለነበሩት ለንጉሠ ነገሥቱ ደረሰ። እሳቸውም የሀገር አስተዳደር ሚኒስትሩ ደጃዝማች ገብረማርያም ወደ ሲዳሞ፣ የገንዘብ ሚኒስትሩ በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ ከተማ በባሌ በኩል በተጨማሪ ዘምተው ድጋፍ እንዲሰጡ አዘዙ። እንደዚሁም ለሲዳሞና ለባሌ ጦር ሁለት ማጠናከሪያ አዋጆች አወጡ። አዋጆቹም ያፈገፈጉት ጦሮች ተመልሰው ጠላትን እንዲከላከሉ ትዕዛዝ የሚያስተላልፉ ነበሩ። ጥር 19 ቀ ን የተላለፉት እነዚህ ሁለት አዋጆች "እንዴት ሲዳሞን፣ ባሌን ወንድ እንደሌለበት አድርጕ ይግባበት?" የሚል ኃይል ቃል የያዙ ነበሩ።[3]

የመልካ ዳዲን እና የቁልማዩን ጕራ ከሰበረ በኋላ፣ ጠላት ወደ ነጌሌ ገሰገሰ። በኢትዮጵያም በኩል አዲስ ዝግጅት ተደረገ። ይርጋ ዓለም የነበረው ደጅን ተንቀሳቅሶ በአዲስ ገባ። በራስ ደስታ በሚመራው ጦርም ላይ ጠላት የአይሮፕላን ድብደባ አጠነከረበት። በመሆኑም ከነገሌ አፈግፍጐ ዋደራ ላይ ለመመከት ተዘጋጀ። ጥይትና መሣሪያውንም በሰዋራ ጫካና ገደል ውስጥ አኖረ። የማይጠቅመውን ዕቃ ሕዝብ እንዲወስደው አደረገ። ሊያነሳው ያልቻለውን የውጅግራ ጥይትና ሌላም አሮጌ መሣሪያ አንድነት ሰብስቦ ለቃጠሎ አዘጋጀው።

በዚህ ወቅት ከኢጣልያ ከድተው ለመርዳት በዳሞ በኩል ጥሰው የመጡ 600 ኤርትራውያን፤ በቀኛዝማች ፀጋዬ መሪነት ጥር 12 ቀን 1928 ዓ.ም ከኢትዮጵያ ጦር ጋር ተቀላቀሉ። ድካም ጸንቶባቸው ነበርና ለዕረፍታቸው ወደ ይርጋ ዓለም ተላኩ። አንዳች ሳይጕድልባቸው በይርጋ ዓለም የ9 ወር ዕረፍት አደረጉ።

ወደ ጦርነቱ ሁኔታ እንመለስ። በዛ ማንኛውም ዝግጅት ከተደረገ በኂላ የጦር ሠፈሩ ከአዶላ ወደ ዋደራ ተዛወረ። ሁለት ጣልያኖች



አካባቢውን ለመሰለል በታንክ ከነገሌ ወደ ዋደራ ሲንቀሳቀሱ በመንገድ ላይ በደፈጣ ተገደሉ። አንደኛው የጦር መኰንን ነበር። እንደዚሁም በሌላ ቀን የኢትዮጵያ ወታደሮች ጠላት የነበረበት ቦታ በድንገት ደርሰው 37 ኢጣልያኖች በመግደልና 7 መትረየስ፣ 115 ጠመንጃ በመማረክ ጀብዱ ሠሩ። ይህ ዓይነት የደፈጣና የአደጋ መጣል ዘዴ ጥሩ ውጤት ስለአስገኘ ቢታታ ከተባለው ቦታ ምሽግ ተሠራ። እርድ ተምሶ ምሽጉ ከተሠራ በኂላ 80 ወታደሮች ከዚያ ውስጥ ገብተው ይጠባበቁ ጀመር።

በየካቲት ወር 1928 ዓ.ም የጠላት ጦር በሰባት መኪና ተሳፍሮ ከነገሌ ወደ ቢታታ መጣ። አመጣጡን ባዩ ጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቦታውን ለቅቀው ከፊትና ከኂላው ተደበቁ። ጠላትም ከቦታው ላይ ምንም ባጣ ጊዜ ከመኪና ወርዶ ምሣ በልቶ መዝናናት ያዘ። ከዋደራ ወገን የተደበቁት 40 የኢትዮጵያ ወታደሮች በድንገት ደርሰው ጨፈጨፉት። ወደ ነገሌ ሲሸሹ ደግሞ ሌሎች 40 ደገሙት። በጠላት ወገን የነበሩት ኢጣልያኖች ብቻ ነበሩ። አንድ መኪና ብቻ ጥቂት ሰዎች ይዞ ሲያመልጥ ሌሎች 63 ኢጣልያኖች ተማረኩ። ወታደሮቹም ተገደሉ። ጦርነቱም ለኢትዮጵያ ጦር በሰላ ቢላዋ ጮማ እንደመቁረጥ ሆነለት። ይህ ጀግንነት የተሠራው ግራዝማች ኃይለ ማርያም ገብረ ሥላሴ በተባሉት የሰላሌ ሰው ነበር።

የደሎ ጕራ ሲፈታ በዚያ ተቀርጦ የቀረው ጦር ታላቅ አበሳ አጋጠመው። በረሃብና በውሃ ጥም አለቀ። የአለቀው አልቆ ከተረፉት ጥቂት ሃያ፣ ሠላሣ ሰዎች ቀን ተጉዘው ሦስት፣ አራት መሣሪያ እየተሸከሙ ዋደራ ገቡ። በተለይ አንድ ቡድን በግራዝማች ሥዩም የሺጥላ መሪነት 45 ቀን ተጉዞ 12 መትረየስና ጥይት ጭኖ ደረሰ። ይህም ለጦርነቱ ድጋፍ ሰጠ። እነዚህ በደሎ በረሃ ተቀርጠው የቀሩ ሰዎች ዋደራ ለመድረስ የበቁት ቀጋና አጋም የተባሉ ዛፎች ፍሬ እየበሉ፣ እንደዚሁም ቀጭኔና ጕሽ እያደኑ፣ የእነሱን ሥጋ እየበሉ ሕይወታቸውን አትርፈው ነው።

ጦርነቱ በዚህ ሁኔታ እንደአለ ከንጉሠ ነገሥቱ ታዝዘው በሰሜን የጦር ግንባር የመጡት የደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ ከቆቦ እስከ ደሴ በመኪና፣ ከአዲስ አበባ በአይሮፕላን፣ ከዛም በእግር በአገምጃና በሶዶ አድርገው በመጓጓዝ በመጋቢት ወር 1928 ዓ.ም ከዋደራ ጦር ሠፈር ደረሱ። በጦር ምክር ቤት ተጠንቶ ድኑን የውጊያ ቦታ እንዲሆን ተመረጠ። በደጃዝማች መኰንን ወሰኔ መሪነት የወላይታና ከአዲስ አበባ የዘመተው ጦር ድኑን ላይ እንዲመክት በድምፅ ብልጫ ተወሰነ። ነገር ግን የደጃዝማች ገብረማርያም ከቆቦ ድረሱ መጥቼ እንዴት ዕድል

አይሰጠኝም ስለአሉ ውሣኔው ፈረሰ። ሁለቱ ደጃዝማቾች አብረው እንዲዘምቱ ማድረግ የማይቻል ሆነ። ራስ ደስታ ዳምጠው ራሳቸው እንዳይሄዱ ሠራዊታቸው በደሎ በረሃ ከደረሰበት ጉዳት ገና ስላአላገገመ የማይመች ሆነ። ከብዙ ንትርክ በኋላ የድኑን ጉራ በዕጣ ለደጃዝማች ገብረማርያም ደረሳቸው።

ሻለቃ በቀለ ወያ ደግሞ በሰሜን ጦር ግንባር በአስረከቡት መሣሪያ ልክ ከአዲስ አበባ አራት መድፍ፣ አንድ ሺህ አንድ መቶ ቤልጅግ መውዜር ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋር ይዘው ሚያዝያ 23 ቀን 1928 ዓ.ም ዋደራ ደረሱ። ይህም ለኢትዮጵያ ጦር የልብ ልብ ሰጠው።[4]

የቦረናው ጦር ግንባር በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ንጉሠ ነገሥቱ ሀገር ጥለው ሄዱ። ወሬውም ወዲያው በሬዲዮ ተሰማ። የጦርነቱም ሥልት መሪ ስለአጣ፣ ወደ አርበኝነት ተለወጠ።

ከማይጨው ጦር ግንባር የተመለሰ አንድ ቡድን ገስግሶ ቦረና ገባ። ቀደም ብለው በአካባቢው የነበሩ እንደ አደረጉት፣ ወደ ኬንያ ሳይሰደድ በጋርዱላ አውራጃና በደቡብ ቦረና ትግሉን ቀጠለ። ቡድኑ ትግሉን የቀጠለው ጉማይዴ ላይ በአደረገው ስብሰባ የሃያ አንድ ዓመቱን ወጣት አቶ /ደጃዝማች/ ተስፋዬ ወልዴን መሪ አድርጉ በመምረጥ ነበር። በቡርጂ፣ በአማሮ፣ በገለና፣ በሀገረ ማርያም፣ በባርጉዳ፣ በተልተሌ፣ በያቤሎ፣ በስኮሪ፣ በመርቃ፣ በገለባና በጮራም የጦር ሜዳዎች ጠላትን ግንባር ለግንባር እየገጠመ አኩሪ ውጤት አግኝቶአል።[5]

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ሰይፉ አባወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 46-66። ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 128።
2. ሰይፉ አባወሎ፣ገጽ 66-79።
3. ገብረ ወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 81-82።
4. ሰይፉ አባ ወሎ፣ ገጽ 82-91።
5. የጀግኖች አደራ፣ የጀግኖች ማህበር መጽሔት፣ መጋቢት 28 ቀን 1983 ዓ.ም ገጽ 37-39።



# ምዕራፍ አሥራ ሶስት
# የማይጨው ጦርነትና የኢትዮጵያ ድል መሆን

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ላይ እንደተገለፀው፣ ጦርነቱ ለብዙ ጊዜ በብዙ ቦታ ተካሄዶአል። ከረጅም ትንቅንቅ በኋላ ኢጣልያ የአሸናፊነትን እድል ተቀዳጅታለች። ከታሪክ አኳያ ከሚነሱት ጥያቄዎች አንዱ "ኢትዮጵያ ድል የሆነችው የትና መቼ ነው?" የሚል መሆን ይገባዋል።

በአበጋዝ የተሰለፈ ጦር ድል መሆን የሀገሪቱን መሸነፍ አያመለክትም። ሀገሪቱ ድል እንደተመታች መቆጠር ያለበት ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው በቆሙበት ጦርነት ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የተሸነፈችው ነው። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ራሳቸው ለመጀመሪያም፣ ለመጨረሻም ጊዜ በዚህ ጦር ሜዳ የቆሙት መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ማክሰኞ ነው። ኢትዮጵያ ድል የሆነችው በዚህ የጦር ሜዳ ነው። ወደ አምስት ሺህ ዘመን በሚጠጋ ታሪኳ ሰንደቅ ዓላማዋ ወድቆ፣ ንጉሠ ነገሥትዋ ጥሉአት ሄዶ፣ ከወራሪ እጅ የወደቀችው በዚህ ቀን፣ በዚህ ቦታ ነው። የጦርነቱ ሂደት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

በሰሜንም በደቡብም የተሰለፈው የኢትዮጵያ ጦር የተመራው በንጉሠ ነገሥቱ ነበር። የሰሜኑ ጦር ግንባር ዋነኛው እንደ ነበር ተገልፃል። በእሱም የጦር ሚኒስትሩን ጨምሮ አምስት ራሶች፣ ማለትም ራስ እምሩ፣ ራስ ካሣ፣ ራስ ሥዩም፣ ራስ ሙሉጌታ፣ ራስ ጌታቸው እንደነበሩበትና እነሱም ምን ምን እንደሠሩ አይተናል። ሰበደቡብ ግንባር አንድ ራስ ብቻ፣ ማለትም ራስ ደስታ ዳምጠው ብቻ እንደተሰለፉ አይተናል። በምሥራቅ አንድም ራስ እንደአልነበረ ተረድተናል።

በአመራር ረገድ ለሁሉም አዛዡ ንጉሠ ነገሥቱ ነበሩ። የጦር አበጋዞች የመታዘዝ እንጂ ምክር የመስጠት መብት አልነበራቸውም። ለስም የተቋቋመውም የአዲስ አበባው ምክር ቤት ስለጦርነቱ አገባጠም አንድም ጊዜ አልመከረም። ምንም አዋቂና ትጉህ ቢሆኑ፣ በአንድ ሰው አእምሮ፣ በርቀት የተዘረጉ ጦርነቶችን በብቃት መምራት አይቻለም። ከዚህም በተጨማሪ መገናኛ አልነበረም። ጥቂትም ቢኖር፣ ምሥጢር ወደ ጠላት ከማሸጋገር በስተቀር ለኢትዮጵያ የሰጠው ጥቅም እምብዛም ነው።

ሁኔታው እንዲህ ሳለ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ከደሴ በመኪናና በበቅሎ ተጉዘው መጋቢት 12 ቀን 1928 ዓ.ም ሃያ ከተባለው ቦታ ደረሱ። ራስ ካሣና ራስ ስዩም ከተንቤን ጦርነት የተረፈውን ሠራዊታቸውን ይዘው ቀደም ብለው መጋቢት 10 ቀን ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኝተው ስለነበር ስለ ጦርነቱ ልዩ ልዩ ምክር ተደረገ። ዋና ዋናዎቹ የጦር አማካሪዎች ነጮች

ነበሩ፡፡ የንጉሠ ነገሥቱም አመለካከት የሚያዘነብለው ወደ እነሱ ነበር፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ምክሩን በትዕግስት ያዙት፡፡ እንደምን እንዋጋ ለሚለው ጥያቄ ልዩ ልዩ ሐሳብ ከታለመ በኋላ ውሣኔ ተደረገ፡፡ ክብር ዘበኛ በንጉሠ ነገሥቱ ግንባር እንዲሰለፍ ተመደበ፡፡ በግራ ራስ ጌታቸው፣ በመሐል ራስ ካሣ፣ በቀኝ ራስ ሥዩም እንዲሰለፉ ተወሰነ፡፡ አቡነ ጴጥሮስና እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ የደብረ ጽጌ ጊዮርጊስን፣ የደብረ መንግሥት ገብርኤልን፣ የደንባሮ /ግንባርዋ/ ማርያምን ይዘው ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት እንደሚቆሙ ተወሰነ፡፡

በዚህ መልኩ ጦሩ ከተደለደለ በኋላ መች እንግጠም የሚለው ጥያቄ አስቸገረ፡፡ የጦር አለቆች ሠራዊታቸው አልተከተለንም እያሉ ምክንያት አበዙ፡፡ የጦርነቱ ቀን ተጓተተ፡፡ ከግንባር የደረሰው ጦር ትዕግሥት አጣ፣ ተቅበጠበጠ፡፡ መጋቢት 19 ቀን ባአታዩ ላይ በተደረገ ምክር ጦርነቱ መጋቢት 21 ቀን እንዲሆን ተወስኖ ከንጉሠ ነገሥቱ መመሪያ ተሰጠ፡፡ ጦሩ መጋቢት 21 ቀን ከማታው በ2 ሰዓት እንዲንቀሳቀስ የሚያዝ ነበር፡፡ እንዲሁም መመሪያው እርስ በርሱ እንዳይጠራራ፣ እንዳይጮህ፣ እንዳያቅራራ፣ ጠላት የሸሸ መስሎት በማባረር ቀለበት እንዳይገባ ጥንቃቄ እንዲያደርግ፣ ጠላት ድል መሆኑ ሳይረጋገጥ ግዳይ ለመጣል ወደ ኋላ እንዳይመለስ፣ ለዘረፋ እንዳይጣደፍ፣ ረዳት እስኪደርስለት ጠንክሮ እንዲዋጋ፣ ተኩስ ጀምሩ ለማለት አመሻሽ ላይ የርቺት ምልክት እንደሚተኮስ፣ ባለማዕረግ የጠላት ወታደር ምሥጢር ስለሚገኝበት እንዲማረክ እንጂ እንዳይገደል የሚደነግግ ነበር፡፡[1]

ነገር ግን ይህ ውሣኔ ለኢትዮጵያ ሠራዊት ከመድረሱ አስቀድሞ ባዶሊዮ ሁኔታውን አወቀው፡፡ ሊያውቀው የቻለው ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ "ቅዳሜ ወይም ሰኞ እንገጥማለን" ብለው ለእቴጌ መነን መጋቢት 19 ቀን ማታ ያስተላለፉትን ቴሌግራም ጠልፎ በማዳመጥ ነበር፡፡ ባዶሊዮ ይህንን ምሥጢር እንደ አወቀ ጦሩን ለቅዳሜ ውጊያ አዘጋጅቶ በጥንቃቄ ይጠባበቅ ጀመር፡፡

የኢትዮጵያ ሠራዊት በመመሪያው መሠረት ለእሑድ፣ ለመጋቢት 21 ቀን ሲዘጋጅ ዋለ፡፡ ሌሊቱን ከጠላት ተጠግቶ ለውጊያ ቦታ ያዘ፡፡ ነገር ግን ከንጉሠ ነገሥቱ ሌላ ትዕዛዝ መጣ፡፡ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት ጦሩ በየአለበት እንዲውል ተለፈፈ፡፡ ጦሩ እንደታዘዘው አደረገ፡፡ እሳቸውም በነበሩበት መሐን በተባለው ዋሻ ዋሉ፡፡ ጠላት ጦርነቱ ለመጋቢት 21 ቀን መቀጠሩ ቀደም ብሎ ሰምቶ የበኩሉን ዕቅድ አውጥቶ ይጠባበቅ ስለ ነበር፣ ጦርነቱ በአንድ ቀን መዘግየቱ ለጠላት ፋሲካ ሆነለት፡፡ ብዛታቸው እስከ አንድ መቶ ሃምሣ የሚደርሱ አይሮፕላኖች ከጉር አይሮፕላን ጣብያው



እያስነሳ ሙሉ ቀን በቦምብ ደበደበው፣ መርዝ ረጨበት፡፡ የመጋቢት 21 ቀን ውጊያ መተላለፍ ጠላትን በብዙ ጠቀመ፡፡ በኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ታላቅ ጉዳት ያደረሰ ስህተት ነበር፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ገና አልታወቀም፡፡

ጦርነቱ መጋቢት 23 ቀን 1928 ዓ.ም ማክሰኞ ከሌሊቱ በ10 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ተከፈተ፡፡ የተከፈተውም በድንገት እንጂ፣ አመራር ተሰጥቶበት አልነበረም፡፡ አንድ ያልታወቀ የሐማሴን ተወላጅ ሰው ቀደም ብሎ ከጠላት ከድቶ ከኢትዮጵያ ሠራዊት ጋር ተቀላቅሎ ነበር፡፡ የግጥሚያው መዘግየት ስለአበሳጨው ሌሊቱን በድብቅ ተመልሶ ወደ ኢጣልያኖች ሠፈር ገባ፡፡ ገብቶም በዚያች ሌሊት ኢትዮጵያውያን ጣልያኖችን ሊወሩ መዘጋጀታቸውን ለጀነራል አግሪ ነገረ፡፡ የመጨረሻውን መልእክት ርችት በመተኮስ እንደሚያስታውቅ ነግሮ ወደ ኢትዮጵያውያን ሠፈር ተመለሰ፡፡ ለእነሱ ደግሞ ጣልያኖች ዛሬ ሌሊት ሳይታሰብ በድንገት ሊገጥሙ ተዘጋጅተዋል በማለት ነግሮ ከአስጠነቀቀ በኋላ ለሁለቱም ወገን ከሚሰማ አማካይ ቦታ ሆኖ ሁለት የሽጉጥ ጥይት ተኮሰ፡፡ ጣልያኖች ድምፅ ሲሰሙ፣ መስማታቸውን ለማረጋገጥ በስምምነታቸው መሠረት ቀይ ርችት ተኮሱ፡፡ የዚህ ቀይ ርችት ምስጢር ለኢትዮጵያውያኑ አስቀድሞ ተነግሮአቸው ነበርና ተኩሱ ተከፈተ፡፡[2] በዚህ ዓይነት ዋናው ጦርነት ተጀምሮ ቀጠለ፡፡



ንጉሠ ነገሥቱ በጦር አውድ ላይ፡፡

ጦርነቱ በከፍተኛ ደረጃ ተካሄደ፡፡ ጠላት ከማይጨው በስተሰሜን ከአለው ተራራ ላይ ስለነበር የኢትዮጵያ ጦር ጠላቱን ለማጥቃት አልተመቸውም፡፡ እንዲያውም የኢትዮጵያ ጦር የነበረበት ሥፍራ ወደ



ንጉሠ ነገሥቱ በጦር አውድ ላይ።

ሰሜን ማለትም ጣልያን ወደ ነበረበት ተዳፋትነት ስለነበረው ለጥቃት የተጋለጠ ነበር። የኢትዮጵያ ጦር ጠላቱን ለማጥቃት የተቻለውን አደረገ። እስከ ምሽጉ ድረስ እየተጠጋ 5 ያህል ምሽጎች እስከ ማስለቀቅ ደረሰ። ጠላት ከምድር በመድፍ፣ ከሰማይ በአይሮፕላን ድብደባውን አጠናከረ። ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው የቆሙበት የጦር ሜዳ በመሆኑ ወሣኝነቱ ለሁለቱም ወገን ግልፅ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ ከጦርነቱ ሜዳ ገብተው እንደ አንድ ወታደር ተዋጉ። እኩለ ቀን ሲሆን የኢትዮጵያ ጦር መሸሽ ጀመረ። ንጉሠ ነገሥቱም ሰንደቅ ዓላማ አስቀመጡ። ነጋሪት እያስመቱ ድል አድርገናል ብላችሁ እልል በሉ ብለው አዘዙ። እንዲሁም ተደረገ። የሸሸው ወታደር እንደገና እየተመለሰ ተዋጋ። መኳንንቱንም ከአዳራሹ ላይ ምን እያልክ ፎክረህልኝ ነበር እያሉ አነቃቁት። ጦርነቱ ከማታው እስከ 5 ሰዓት አልቆመም ነበር። ንጉሠ ነገሥቱ ሲመሽ መጋቢት 21 ቀን አድረውበት ወደ ነበረው መሐን ወደ ተባለው ዋሻ ተመለሱ። ንጉሠ ነገሥቱንም በዚህ ቀን ውሎአቸው ያላመሰገነ አልነበረም። ንጉሠ ነገሥቱ የቆሙበት ሌላ ጦርነት ስለአልተደረገ ይህ የመጨረሻው ሆነ። ኢትዮጵያ ድል የተመታችው በዚሁ በማይጨው ግንባር ነው።

<u>**ማጣቀሻ ፅሑፎች**</u>

1. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 97-105።
2. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 116-117።



# ምዕራፍ አሥራ አራት
# ከማይጨው መልስ

እንደተገለፀው የኢትዮጵያ መሸነፍ፣ የኢጣልያ ማሸነፍ በማይጨው ጦር ሜዳ መጋቢት 22 ቀን 1928 ዓ.ም ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ ከተዋጉበት ቦታ ወደ ኋላ ተመለሱ። ሐሳባቸው ደግሞ ለመዋጋት እንጂ፣ በዚሁ እንዲያበቃ አልነበረም። ነገር ግን እንደአሰቡት አልሆነም። ጦርነቱ አልተደገመም፤ የመጨረሻው ሆነ። ዝርዝሩን ቀጥሎ እንመለከታለን።

ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት 23 ቀን እና 24 ቀን በዚያው በመሐን ውሎ አደረጉ። ነገር ግን ተመልሰው ከጦር ሜዳው አልገቡም። ሠራዊቱም እንዳይጠጋቸው ተከለከለ።[1] የኢትዮጵያ ጦር ሁለት ቀን ሙሉ ከተዋጋ በኋላ ወደ ኋላው መመለስ ጀመረ። ከጦር መሪዎች አንዱም ወደ ጦርነቱ ሜዳ ስለአልተመለሱ መሪ አልነበረውም። ስለዚህም ሁሉም በየፊናው መንገዱን ወደ ባዕታዩ ቀጠለ። መሸሽ ጀምሮ የነበረው የጠላት ጦር ለቅቆአቸው የነበረውን ምሽጎች መልሶ ያዘ። ያም ሆኖ ግን "ወደኋላችን እንመለስ" ካሉት "ለጠላታችን ግንባራችንን እንጂ ጀርባችንን አናሳይም" ያሉ ቆራጥ የኢትዮጵያ ጀግኖች ፍልሚያውን ቀጠሉ። እስከ መጋቢት 25 ቀን ዓርብ ድረስ ተኩስ ይሰማ ነበር።

በንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር ምክር ተደረገ። መኳንንቱና የጦር አለቆች ሐሳባቸውን ተጠየቁ። ከቀረቡት ሐሳቦች አንደኛው ወደ ባዕታዩ ተመልሰን ጦሩን እንደገና አዘጋጅተን እንዋጋ የሚል በመሆኑ ንጉሠ ነገሥቱ ስጋት አደረባቸው። ሥጋታቸውም ከማይጨው እግር ከነቀልን ዳግመኛ ጦርነት ለመግጠም የማይቻል ይሆናል የሚል ስለነበር "...ያለነው ተዋግተን ብንሞት ይሻላል" አሉ። የንጉሠ ነገሥቱን ሐሳብ መኳንንቱ ስለአልተቀበሉ ከብዙ ንግግር በኋላ፤ መጀመሪያ ራስ ከበደ ወደ ነበሩበት ዋሻ ከዚያም ወደ ባዕታዩ መልስ ሆነ። ንጉሠ ነገሥቱ መጋቢት 24 ቀን ከሌሊቱ በ6 ሰዓት ባዕታዩ ደረሱ።

በባዕታዩ አዲስ የጦር ዕቅድ ተሠራ። ለማጥቃት መሞከር ቀርቶ መከላከል እንደሚሻል ታመነበት። መኳንንቱ ሥራቸውን እየያዙ የሚሰፍሩባቸው አምስት ቦታዎች ተመደቡ። እነሱም፣

1. የባዕታዩ መሐል ሠፈር ለንጉሠ ነገሥቱ ተመደበ።
2. ከቦክራ እና ከመሐል ተራራ መካከል ያለው በር ለደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ተሰጠ።
3. ከክሣድ ሃያ እስከ አደባማዙ ያሉት 3 በሮች ለራስ ጌታቸው ተሰጡ።

4. ከኮማድ ሃያ ጀርባ እስከ መሐን ድረስ ያለው ለራስ ከበደ ተመደበ።
5. የሃያ ሚካኤል በር ለግቢ ሚኒስቴር ጭፍራ ተሰጠ።

ለወስላታ መጠባበቂያው በአዲ ወይፌር በር፣ በማህሌ ቤት በር፣ በሃያ ማርያም በር፣ በገረብ ሃያ በር፣ በመንክሬ በርና እና በቀኛዝማች ኃይለ ሥላሴ ቤት በር፤ በድምሩ በ6 በሮች ጠባቂ ተመደበ። እንደዚሁም በዋግ በኩል ለ5 በሮች፣ በጨርጨር በኩል ለ2 በሮች ወታደር ታዘዘ።

የኢጣልያ ጦር በበኩሉ ንጉሠ ነገሥቱ የነበሩበትን መሐን የተባለውን ቦታ መጋቢት 25 ቀን ያዘ። በዚህ ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ ጦራቸው መታኮሻ ቦታ እንዲይዝ አዘዙ። ራሳቸው እየተዘዋወሩ ቦታ ማከፋፈል ጀመሩ። የጦር ትዕዛዝ ቢሰጡም ያዳመጣቸው የለም። የጦርነቱ መከራ አሰቅቆት ነበርና ወታደሩ ጉዞውን ወደ ኮረም ቀጠለ። መኳንንቱ ይህንን ባዩ ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሰን አሸንጌ ላይ እንከላከል የሚል ሐሳብ አቀረቡ። ይህ ሁኔታ ንጉሠ ነገሥቱን እጅግ አበሳጨ። "... የፈቀደ ከእኔ ጋር ይመት። እኔ ግን ወደ ኋላዬ አልመለሰም" አሉ። በዚህ ጊዜ የንጉሠ ነገሥቱ ሕይወት አሳሳቢ እየሆነ መጣ።

ከቀኑ በ3 ሰዓት ስብሰባ ተደረገ። ወደ ኋላ ተመልሰን ጦራችንን እያስተባበርን፣ በደፈጣ አደጋ እየጣልን፣ ሲቻልም ፊት ለፊት በመግጠም ብንከላከል ይሻላል የሚል ሐሳብ ቀረበ። ነገር ግን ለንጉሠ ነገሥቱ አልጣማቸውም። ጦሩ ያለው በሁለት ሞት መካከል እንደሆነ አስረዱ። ቆሞ ቢዋጋም፣ ቢሸሽም ሞት እንደማይቀርለት ገልፀው "...የተቻለውን ያህል ሠርተን የኢትዮጵያ ነፃነት በእኛ ደም ይፋቅ" አሉ። 43 ሰዎች በየተራ እየተነሱ ሐሳባቸውን ሰጡ። ከእነሱም 33ቱ ወደ ኋላ ማፈግፈግን መረጡ። በዚሁ እንዲፈፀም ተወሰነ።[2]

የንጉሠ ነገሥቱ ስንበት ጉዳይ ደረሰ። "ከዚህ እግራችንን ከነቀልን ጦርነቱ መደገሙ መቅረቱ ነው" ያሉት በትክክል ተፈፀመ። ከባዕታዩ በኋላ ስለጦርነት ምንም አልተደረገም፤ ሐሳቡ ሁሉ ስለሽሽት ብቻ ሆነ። ጦሩ ተስፋ ቆርጦ የማንንም አመራር ሳይጠብቅ ጉዞውን ወደ መሐል ሀገር ቀጠለ። መጋቢት 27 ቀን 1928 ዓ.ም አሸንጌ ደረሰ። ጣልያንም ከንጉሣችሁ እንጂ ከእናንተ ጠብ የለንም። እንነካችሁም በሰላም መጓዝ ትችላላችሁ የሚል የስብከት ወረቀት ጥሎ ስለነበር፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሌሊት ለመሸሽ የነበረውን ሐሳብ ትቶ ከአውላላ ሜዳ ላይ ቀን ለቀን መጓዝ ጀመረ። ጠላት ግን ይህንን የሀሰት የስብከት ወረቀት የጣለው ለዘዴው ነበር። ታቹን በአዘቦ በረሃ በእግሩ ዞሮ የሚቆርጥ ጦር አቅርቦ ነበር። እንደልማዱ 150 አይሮፕላን አስነስቶ ድብደባውን ቀጠለ። በመትረየስ ፈጀው። በጠቅላላው 73 ቶን የሚመዝን ቦምብና መርዝ አወረደበት።



የኢትዮጵያ ሠራዊት ድካም ቢሰማውም፣ ድብደባ ቢበዛበትም፣ መከላከሉን አልተወም። በሚቻለው ሁሉ ተዋጋ። በአዘቦ በረሃ በኩል የመጣበትን እግረኛ ጦር አስታገሰ። ከአይሮፕላኖቹም 28 ጣለ። እነግራዝማች እንደሻው ቁንጮ የጀግንነት ሥራ ሠሩ።[3] ይህ ሥራቸው በታሪክ ውስጥ ሊጠቀስላቸው ይገባል። እነሱ በጀግንነት ባይከላከሉ ኖሮ የአሼንጌ እልቂት ጠላት እንደ አቀደው ሁሉ ፍፁም ይሆንና ምንም ሰው አይተርፍም ነበር።

ከእልቂት የተረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት መጋቢት 27 ቀን ወደ ኮረም ጉዞውን ቀጠለ። ነገር ግን እሱ ከመድረሱ አስቀድሞ በአዘቦ በረሃ የመጣው የጣልያን ጦር በዚሁ ቀን ኮረምን አስቀድሞ መያዙ ተሰማ። ስለዚህ ጦሩ መንገዱን ለውጦ ወደ ላስታ አቀና።

ንጉሠ ነገሥቱ ባላት ጊዮርጊስ፣ በጓሮ ማርያም፣ በመረዋ ሐዶ አድርገው ግራሮች ደረሱ። የአይሮፕላን ድብደባ ስለከበደ እስከዚህ ድረስ ጉዞው በሌሊት ነበር። ከዚህ በኋላ ግን በቀን ሆነ። ከግራሮች ተነስተው በአንጀፋት ማርያም በኩል ውሃ አቦ ገቡ። ከዚያም ጥላስፈሬ ሚያዝያ 3 ቀን ደረሱ። ንጉሠ ነገሥቱ የትንሣኤን በዓል ከጥላስፈሬ ሥላሴ አከበሩ። ሚያዝያ 5 ቀን ከጥላስፈሬ ተነስተው ወደ ላሊበላ በመሄድ የቅዱስ ላሊበላን አብያተ ክርስቲያናት ጉበኙ። ከላሊበላ ተመልሰው ጥላስፈሬ እንደገቡ በሚያዝያ 5 ቀን ተጽፎ የነበረውን አዋጅ አስነገሩ። በአዋጁም የጠላትን አመጣጥ፣ በማይጨው የተሠራውን ሥራ ዘርዝረው "...ታላቁን ጦርነት ለማድረግ ወደ ሸዋ ተጉዘናል። ...ባገርህ ላይ እየተዘዋወርክ...በያለህበት ተዋጋ..." የሚል ነበር።

ከጥላስፈሬ ሚያዝያ 8 ቀን ተነስተው ደላንታ ውስጥ አንጉጥ ከሚባል ሥፍራ ደረሱ። ከዚያም ሚያዝያ 10 ቀን ወገል ጤና ገቡ። የደሴ ሁኔታ ስለአልታወቀ ወደ ወረኢሉ ተጓዙ።[4] ይህ ግምት ትክክል ነበር። ምክንያቱም ደሴን አልጋወራሹ አንድም ጥይት ሳይተኰስ ለቀውለት በመሄዳቸው፤ የኢጣልያ ጦር ሚያዝያ 6 ቀን ገብቶበት ነበርና።[5]

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከጣልያኖች ቀድሞ ለመግባት ገሰገሱ። ሚያዝያ 11 ቀን ሰንበሊጥ በር አፋፍን ወርደው አደሩ። ስለጉዞው ባለ5 አንቀጽ መመሪያ አወጡ። ሰውም በየአለቃው እንዲሠፍር፣ ጉዞውንም ከዋናው መንገድና ከገላጣ ቦታ እየወጣ እንዲጓዝ አዘዙ። ሚያዝያ 12 ቀን መቅደላ ሥር አደሩ። በዚሁ ቀን በነዋሪውና በወታደር መካከል ተኩስ ተከፍቶ ብዙ ሰው ሞተ። በማግስቱም አገሩ ዙሪያውን ከብቦ ለጦር ተሰልፎ መጥቶ ነበር። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ መኖራቸውን ከተረዳ በኋላ ተመለሰ። እሳቸውም "ከዘመቻ ያለፈቃድ የተመለሰውን እጁን ለእኔ፣ ከብቱን ለአንተ" የሚል አዋጅ አስነገሩ። ይህም ሆኖ መተናኮሉን አልተወም። የመተናኮሉ

ምክንያት የውስልትና ብቻ ሳይሆን፣ በልጅ ኢያሱ አምዋምዋት የተነሳ ሕዝባዊ ስሜትም ነበረበት።



የንጉስ ነገሥቱ ጉዞ ከማይጨው ወደ አዲስ አበባ።

ጉዞ ተቀጥሎ ሚያዝያ 13 ቀን ተንታ ገቡ። በማግስቱ ደግሞ አበደ ቤት መሮ ከሚባል ቦታ፣ ከዚያም ሚያዝያ 15 ቀን ሰጋምቦ ደረሱ። በዚሁ ቀን የጣልያን ጦር ወረኢሉ መግባቱ ተሰማ። ከዚህ በኋላ ደግመን እንዋጋለን የሚለው ሐሳብ አከተመ። በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ጉዞ እንዲደረግ ተወሰነ። የአዲስ አበባው ጉዞ ቀጥሎ በለገሂዳ፣ ጀማ፣ በደብረ ግል አድርገው ዜማ ወንዝን ተሻግረው ሚያዝያ 22 ቀን ፍቼ ከተማ ገቡ። ከፍቼ ከተማ በዚሁ ሌሊት በ7 ሰዓት ተነስተው በአውቶሞቢል በመንዝ ሚያዝያ 21 ቀን ከጥዋቱ በ3 ሰዓት አዲስ አበባ ገቡ።[6]

### ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 119።
2. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው* ፣ገጽ 108-118።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *የአባላሸኝ ዘመን*፣ ገጽ 18።
4. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ ገጽ 119-125።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 122።
6. ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ገጽ 126-131።



# ምዕራፍ አሥራ አምስት
## የንጉሠ ነገሥቱ ስደትና የሠራዊቱ መፍረስ

ከዚህ በኋላ ንጉሠ ነገሥቱ ሁኔታውን የያዙት በትዕግሥትና በዕርጋታ ነበር። ሚያዝያ 23 ቀን ሌሊት አራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዓልን አከበሩ። ከቀትር በኋላ ደግሞ በጣርማ በር በኩል ለመጣው የጠላት ጦር ራስ ጌታቸው፣ በጅሩ በኩል ለመጣው ደግሞ ደጃዝማች ፍቅረማርያምን አበጋዝ አድርገው ሾሙ። ሽማግሌና ሴት ከከተማ እንዲወጣ፣ በዉጊያ ዕድሜ ላይ ያለ ሁሉ ከላይ ወጥቶ እንዲሠፍር አዘዙ።[1]

ከዚህ በኋላ ምክር ተደረገ። መኳንንቱና ሊቃውንቱ በንጉሠ ነገሥቱ ሰብሳቢነት በታላቁ ቤተ መንግሥት ተሰብስቦ መከረ። የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ ለብቻው ተሰባሰበ። መኳንንቱና ሊቃውንቱ ጉዳዩን የተመለከተው በአገር ባህልና ሥርዓት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደግሞ ከፖለቲካ አንፃር ሳይሆን አልቀረም።

የመኳንንቱና የሊቃውንቱ ስብሰባ መጋቢት 24 ቀን ከቀትር በኋላ በ12 ሰዓት ተጀመረ። ልዩ ልዩ ሃሳቦች ቀረቡ። አንደኛው ሐሳብ በማህል ሀገር ስለሚደረግ ውጊያ፣ ሁለተኛው ደግሞ የመንግሥት መቀመጫ ወደ ጐሬ ተዛውሮ ስለመከላከል ነበር። በመሐል ሀገር ለመዋጋት የከጀለው ቡድን ጦር ከሁለት ተከፍሎ አንዱ ቡድን በጣርማ በር ከዚያም እልፍ ቢመጣ በበረሃ እንዲመደብ ሲያሳስብ፣ ሁለተኛው ቡድን በአህያ ፈጅ፣ በጅሁር አፋፍ እንዲዋጋ ነበር። ለዚህ ዕቅድ ማሻሻያ የቀረበው ሐሳብ ደግሞ ጦሩ ከሁለት መከፈሉ ቀርቶ ጥቂት በጥቂት እየተመደበ በሁለቱም በር በሽፍትነት መልክ እንዲከላከል የሚል ነበር። ሌላው ዋና ሐሳብ ደግሞ እንደተጠቀሰው ቤተ መንግሥቱ ወደ ጎሬ ተዛውሮ ጦርነቱ እንዲቀጥል ነበር። ነገር ግን በአንዱም ሳይቆረጥ አደረ።

በማግስቱ ሚያዝያ 25 በዚያው ሰዓት ስብሰባው ሲቀጥል አዲስ ሐሳብ ቀረበ። እሱም ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ዓለም ማህበር ሄደው ያመልክቱ፣ እስከዚያው ድረስ ጦሩ በየሀገሩ ተሰማርቶ በሽፍትነት እየተከላከለ ፍርድ ይጠብቅ የሚል ነበር።[2] ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ውጭ አገር ይሂዱ የሚለው ሐሳብ ተደገፈ። ይህ ሐሳብ በድንገት ሳያልፍ ቀርቶ ውሎ ቢያድር ኖሮ፣ ተቀባይነት የማግኘቱ ጉዳይ ሳያጠራጥር አይቀሬም ነበር። ለዚህ ሳይሆን አልቀረም በቶሎ እንዲወሰን የተደረገው። ነገር ግን ቀደም ብሎ መደላድል ተሠርቶለት ስለነበር ሥምረት አገኘ። ቀደም ብሎ የተሠራው መደላደል ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

የእንግሊዝ መንግሥት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 14 ቀን 1928 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ፣ የንጉሠ ነገሥቱ ቤተሰብ ኢየሩሣሌም እንዲገባ ተስማምቶ ፈቃድ ሰጠ። የኢትዮጵያ መንግሥት የሚኒስሮች ምክር ቤትም በበኩሉ፣ ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ጀኔቫ ሄደው ለዓለም መንግሥታት ማህበር



የንጉሰ ነገሥቱ ጉዞ ከማይጨው ወደ አዲስ አበባ።

ያመልክቱ የሚለውን ሐሳብ 21 ለ3 በሆነ ድምፅ ተቀበለ፡፡ ከዚህም በስተቀር ንጉሠ ነገሥቱ ታላላቆቹን መኳንንት ይዘው ለመሄድ ማሰባቸው ለባለሥልጣኖች የነፍስ ማዳኛ መንገድ ሆኖ ተሠማቸው፡፡ በዚህ ሁሉ አቴጌይቱ አዲስ አበባ ከነበሩ የታላላቅ መንግሥታት ኤምባሲዎች ጋር ተነጋግረውበት በተሰጣቸው ምክር መሠረት ባላቸውን ይዘው ለመሄድ ጉትጉታውን አጠነከሩ፡፡ የእንግሊዝ መርከብ ጅቡቲ ወደብ ገብቶ ተጠባበቀ፡፡ የኢጣልያ ጦር ደብረ ብርሃን ገባ፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት ሐሳቡ ድጋፍ አገኘ፡፡

ንጉሠ ነገሥቱ የመጨረሻዎቹን ትዕዛዞች ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ.ም ጠዋት ሰጡ፡፡ ትዕዛዞቹም፣

1. መንግሥቱ በአዛዥ ወልደፃድቅ አበጋዝነት ወደ ጎሬ እንዲዛወር፡፡
2. አቶ /ብላታ/ ታከለ ወልደሃዋርያት አዲስ አበባን እንዲጠብቁ፡፡
3. ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ቂርሎስ አዲስ አበባ ቆይተው ሕዝቡን እንዲያረጋጉ የሚሉ ነበሩ፡፡[3]

የንጉሠ ነገሥቱ የአውሮፓ ጉዞ ብዙ ኢትዮጵያውያንን አስቆጣ፡፡ ደጃዝማች ፍቅረማርያም የኢትዮጵያን ክብር የሚያዋርድ ነው በማለት እስከ ግድያ አሰቧቸው፡፡ ብላታ ታከለም በበኩላቸው የአርበኝነት ሥራ ለማስጀመር የሚያስችል ሥልጠና ለማካሄድ ሞከሩ፡፡ ፊታውራሪ ተክለሃዋርያትም ቅሬታቸውን ገለፁ፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም ጉዞውን ማገድ አልቻሉም፡፡[4] ግራዚያኒ ይህንን የንጉሠ ነገሥቱን ጉዞ ባወቀ ጊዜ የሚሄዱበትን ባቡር በቦምብ ለመደብደብ አሰበ፡፡ ነገር ግን ሙሶሊኒ ራሱ ስለከለከለው ሐሳቡን መፈፀም ሳይቻለው ቀረ፡፡

እሳቸው ገብረሕይወትን፣ ራስ ኃይሉንና ሌሎችንም የሚጠራጠሩአቸውን መኳንንት ድሬዳዋ ትተው፤ ቤተሰቦቻቸውንና ባለሚሎቻቸውን ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ፡፡ ከዚያም ጅቡቲ በሰላም ደርሰው ኢንተርፕራይዝ በሚባል የእንግሊዝ ጦር መርከብ ተሳፍረው ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ፡፡ ግንቦት 26 ቀን 1928 ዓ.ም እንግሊዝ ሀገር ገቡ፡፡[5]

የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ መሄድ እስከ ዛሬም ድረስ እንደ አከራከረ ነው፡፡ ወዳጆቻቸው ይደግፉታል፣ ሌሎች ደግሞ ይቃወሙታል፡፡ ደጋፊዎቻቸው የንጉሠ ነገሥቱ ወደ አውሮፓ መሄድ የኢትዮጵያን ጥቃት ለዓለም ኅብረተሰብ ለማሳወቅ እንደረዳ፤ ከዚህም የተነሣ የዓለም ኅብረተሰብ ድጋፍ ተገኝቶ የኢትዮጵያ ነፃነት ሊመለስ እንደቻለ አድርገው ያቀርባሉ፡፡ በዚህ ነጥብ የማይስማሙት ግን ሌላ አመለካከት አላቸው፡፡ የኢትዮጵያ ነፃነት የተመለሰው በእንግሊዝ እንደሆነ፤ እንግሊዝ ኢጣልያን የወጋቸው፣ ኢጣልያ ከጀርመን ጐን በመቆምዋ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ለዓለም ማህበር የተነገረው ቃል አንዳች ፍንጭ እንዳላስገኘ በማስረጃ የተደገፈ ክርክራቸውን



ያቀርባሉ፡፡ የንጉሠ ነገሥቱ መሰደድ ለኢትዮጵያ ውርደት እንደሆነ አድርገው ይገምታሉ፡፡ ነገር ግን ስደቱ ለእሳቸው ለራሳቸው እንደጠቀመ ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

***የኢትዮጵያ ሠራዊት መፍረስ*** - የኢትዮጵያ ሠራዊት ከነበረበት የመሣሪያ እጥረት፣ የስንቅ እጦት፣ የአመራር ዝብርቅርቅነትና ከጠላት ስብከት እየተጋደለ በየጉራው ተዋጋ፡፡ በሰሜን ጦር ግንባር በአድዋ፣ በመቀሌ፣ በሽሬ ተጋደለ፡፡ በተንቤን ጦር ግንባር በአምባራዶም፣ በአሸንጌ ተጋደለ፡፡ በምሥራቅ ከወልወል ጀምሮ በቆራሄ፣ በጀረን ወንዝ፣ በጀመጉታ፣ በሰገግ፣ በደገሐቡር ተከላከለ፡፡ በደቡብ ግንባር ደግሞ በዶሎ፣ በመልካ ዳዲ፣ በአሚኖ፣ በቁልማዩ፣ በዋደራ፣ በደገንና በመልካካ በርትቶ ተዋጋ፡፡

ሙሶሊኒ አዳዲስ መሣሪያ የታጠቀና ብዛት ያለው ጦር በታንክ እየተረዳ እንዲዘምትበት አደረገ፡፡ በተቀነባበረና በዘመናዊ እቅድ በሚመራ አወጋግ ወጋው፡፡ ብዛት ያላቸው አይሮፕላኖችን ከጉርአ እና ከሞቃድሾ አይሮፕላን ማረፊያዎች እያስነሳ በብዙ መቶ ሺህ የሚመዘን ቦምብ ጣለበት፤ መርዝና ጋዝ አዘነበበት፡፡ የኤፕሪት ጭስ ረጨበት፡፡ ወንዝና ጉድጓዱን እየያዘ፣ ሊይዘው ያልቻለውን መርዝ እየረጨ፣ የሚጠጣው ውሃ አሳጣው፡፡ ባላገሩንና ገበሬውን በስብከት እያታለለ፣ መሣሪያ እያስታጠቀ፣ እርስ በርሱ አፋጀው፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ ከጦር ሜዳ ላይ ጥለውት እርዳታ ልፈልግ በሚል ምክንያት ተሰደዱ፡፡ መኳንንቱና መሣፍንቱ አውላላ ሜዳ ላይ እየጣሉት በባቡር፣ በአውቶሞቢል፣ በካሚዮን እየተሳፈሩ ጥለውት ሄዱ፡፡ የቻሉ ከሀገር ወጡ፤ ያልቻሉት ተሸቀዳድመው ከጠላታቸው ጐን ቆሙ፡፡

ሠፊው የኢትዮጵያ የሕዝብ ሠራዊት በየጉጡ ተበተነ፡፡ የቻለው ከቤቱ፣ ከወገኑ ገባ፡፡ ሌላው ደግሞ በሲዳሞ፣ በጉሬ እያደረገ የማያውቅበትንና ያለመደውን የስደት መንገድ በመከተል ኬንያ ገባ፡፡ ወደ በርበራ ሄደ፡፡ በምዕራብ የነበረውም ሱዳን ደረሰ፡፡ የትም ቢሄድ ግን፣ የዓለሙ ገዥ እነሱ ነበሩና ከእንግሊዝ በስተቀር ሌላ አላገኘም፡፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ዳግመኛ ይሰበሰባል ተብሎ በማይጠረጠር ዓይነት ተበተነ፡፡ በሀገር ላይ ከፍተኛ ውድቀት፣ በሕዝብ ዘንድ ደግሞ መሪር ሐዘን ወደቀ፡፡ ምን ማድረግ እንደሚሻል የሚያውቅ ሰው ጠፋ፡፡

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. **ገብረወልድ እንግዳወርቅ፣ *ማይጨው*፣ ገጽ 132፡፡**
2. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 164፡፡
3. Angelo Del Boca, *The Ethiopian War: 1935-41*, P.201.
4. Richard Greenfield, *Ethiopia: A New Political History,* pp.220-223.

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት
# የኢጣልያ አዲስ አበባ መግባት

ከሰሜኑም ከምሥራቁም በኩል፣ ጣልያኖች ማይጨው ላይ ድል ከአደረጉ በኋላ አዲስ አበባ ለመግባት በሙሉ ኃይላቸው ተንቀሳቀሱ። የሰሜኑ ጦር እስከ ኮረም ተሰርቶለት የነበረውን የመኪና መንገድ እየተጠቀመ ጉዞውን አፋጠነው። በአዘቦ በረሃ አቋርጦ የአሸንጌን እልቂት ከአካሄደ በኋላ፤ አንዳች ችግር ሳያጋጥመው እርምጃውን ቀጠለ። የመዋጊያ ቦታ እንዲሆኑ ከታሰቡት ቦታዎች አንድዋ ደሴ ነበረች። ነገር ግን እንደታሰበው አልሆነም። አልጋ ወራሹ ልዑል አስፋወሰን ኃይለሥላሴ ለቀውለት ወደ አዲስ አበባ በመምጣታቸው፤ ደሴን አንድ ጥይት እንኳ ሳይተኮስበት ያዘ።[1]

በአድዋ ጦርነት ጊዜ ጣልያኖች በአሰብ በኩል ለመግባት ሙከራ ማድረጋቸው ይታወሳል።[2] ከዚህ ቀደም ብሎ 1880 ዓ.ም አካባቢ አንድ ኢጣልያዊ ወደ አፍደራ ለጥናትና ምርምር በሚል መጥቶ ደንከሎች ገድለውት ነበር። ታሪክ እየተደጋገመ ይደርሳልና፣ አባቱ በሞተበት በዚህ በአሰብ በር ልጁ ባሮን ፍራንኬት ለመግባት አሰበ። በአይሮፕላን ከሮም ተነስቶ ካይሮ አረፈ። ከዚያ ተነስቶ ወደ አሥመራ ሲበር አይሮፕላን ስለተሰናከለበት፤ በግንቦት ወር 1927 ዓ.ም በግብፅ በረሃ ተቃጥሎ ሞተ። ከእሱም ጋር የኢጣልያ መንግሥት የሥራ ሚኒስትርና ሌሎችም ሰባት ጣልያኖች አብረው ሞቱ።[3] እንዲህም ሆኖ ጣልያኖች በአሰብ በር ለመግባት የነበራቸውን ዕቅድ አልተዉም ነበርና፣ አንድ ቡድን ጦር ላኩ። ከአሰብ የተንቀሳቀሰው ይህ ጦር በሰርዶ በኩል አድርጐ ወደ ደሴ መጣ። አልጋ ወራሹ ይህንን እንደተገነዘቡ ሁኔታውን ለንጉሠ ነገሥቱ አስታወቁ። የደረሳቸው መልስ "ያሳዝናል" የሚል ሆኑ። በዚህ ጊዜ ነበር ከተማውን ለቅቀው ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው የመጡት። የጣልያን ጦርም ወደዚያው ገስግሶ ወረኢሉን ያዘ።

ሮቤ ሲደርስ በመጀመሪያዎቹ የሆለታ የጦር ትምህርት ቤት ምሩቆች የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ተከላከለ። የደብረ ሲናን ተራራ አወጣጥና የጣርማ በርን አስተላለፍ ለጠላት አስቸጋሪ አደረጉበት።[4] ለነገሩ የዚህ ጦርነት የውጊያ ስልት ሲታይ፣ ያን ያህል ጠንካራ ገጽታ አይታይበትም። ነገር ግን ጠላት ከንጉሠ ነገሥቱ አስቀድሞ አዲስ አበባ በመግባት ድሉን ለማፋጠን የነበረውን ዕቅድ በማዘግየት ረገድ፤ ንጉሠ ነገሥቱ ቀድመው እንዲገቡና አንዳንድ ውሣኔዎችን ለማድረግ እንዲችሉ ስለአገዘ ሊጠቀስ ይገባል።



ጠላት አዲስ አበባ የሚገባበትን ሥልት ለማቃናት ልዩ ዝግጅት አድርጐ ነበር። ለመኰንኖቹ መቀመጫ 193 ፈረሶች መጥተውለት ነበር። በብዙ መኪናዎችና ሞተር ሳይክሎች ታጅቦ፣ በ12,495 ኢጣልያውያን ወታደሮች እየተመራ፣ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ከቀትር በኋላ፣ በ11 ሰዓት አካባቢ አዲስ አበባ ዳርቻ ደረሰ። በአዲስ አበባ ላይ ታላቅ ዝናም ይዘንብ ስለነበር መንገዱን ድጥና አስቸጋሪ አደረገበት። ባዶሊዮ ቀበና ወንዝ ሲደርስ ወደ ሰሜን ታጥፎ ከኢጣልያ ኤምባሲ ገባ። አይሮፕላኖችም በአዲስ አበባ ከተማ በመገለባበጥ እያንዣበቡ ደስታቸውን ገለፁ።[5] ማርሻል ባዶሊዮም ለሙሶሊኒ አዲስ አበባ መግባቱንና ኢትዮጵያን መያዙን የሚገልጽ ቴሌግራም አስተላለፈለት።

አዲስ አበባ ከታላቅ ጭንቅ ውስጥ ወደቀች። የሰዉ ሁኔታ ታወከ። ንጉሠ ነገሥቱ ከሄዱበት ከሚያዝያ 24 ቀን ጀምሮ ባዶሊዮ እስከገባበት እስከ ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም ድረስ፣ ከተማይቱ መሪም ሆነ አስተዳዳሪ አልነበራትም። ቤተመንግሥቱና አንዳንድ ድርጅቶች፣ በተለይም መሣሪያና ገንዘብ የነበረባቸው ተዘርፈዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ጥለውት የሄዱትን ከተማ ክብር ለመጠበቅ ሲባል፤ የሀገሪቱ ምልክት የነበሩት አንበሶች በሀገር ወዳዶች እጅ ተገደሉ። በጠላት ላይ ጥቃት ለማድረስ በተደረጉ አንዳንድ ሙከራዎችና በርስ በርስ ብጥብጥ ጭምርም ከ1,500 የማያንሱ ኢትዮጵያውያን ሞቱ። ብዙዎቹም እግሮቻቸውን እየታሠሩ በኢጣልያ ወታደሮች እየተጐተቱ፣ በየመንገዱ ዳር እየተጣሉ ባዶሊዮ እንዲያያቸው ተደረጉ። እሱም እያያቸው፣ ምንም ሳይናገር አለፈ፤ ይኼም አበጃችሁ ለማለት መሆኑ ነው።

የአዲስ አበባ መያዝ ሮም ሲሰማ፣ የሮማ ከተማ ሕዝብ ተነቅንቆ ወጣ። በየዕለቱ ሙሶሊኒ ረጃጅም ንግግር ይናገርበትና ታላላቅ ፉከራ ይፎክርበት በነበረው ፒያሳ ቬኒሲያ በተባለው አደባባይ ተሰበሰበ። ሙሶሊኒ ኢጣልያ ብዙ ታሪክ የሠራች ሀገር እንደሆነች ገልፆ፣ ነገር ግን ኢትዮጵያን መያዝዋ ከሁሉም የበለጠ ሥራ እንደሆነ የሚያስረዳ ዲስኩር አደረገ። በዚህ ብቻ አላበቃም። ስለኢትዮጵያ ሕዝብም ተናገረ። "...ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ሆነለት። በሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ይገዙ የነበሩት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች፣ በኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማ ሥር በሀጥታ ሥራቸውን እየሠሩ ሕይወታቸውን ለመምራት ግልፅ ምልክት አሳይተዋል..." አለ። በዚህ ንግግሩ፣ ሊወጣው ከማይችል ማጥ ውስጥ መዘፈቁን አላማወቁን መረዳት ይቻላል።

ከሰሜን የተንቀሳቀሰው የኢጣልያ ጦር ከፍ ሲል የተጠቀሰውን ሲሠራ፤ ከምሥራቅ በሐረርጌ በኩል የመጣው የጠላት ጦር የሐረርን፣

ከዚያም የድሬዳዋን ከተማዎች ሚያዝያ 30 ቀን እና ግንቦት 6 ቀን ያለምንም ችግር ያዙ። ይህም የሆነበት ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱን ጥሎ መሄድ ሲሰሙ፣ በዚያ የነበሩት የኢትዮጵያ የጦር አለቆች ሠራዊታቸውን በትነው ጌታቸውን ተከትለው ስለሄዱ ነበር።[6] ግራዝያኒም ወደ አዲስ አበባ በባቡር ዘለቀ።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. Richard Greenfield, *Ethiopia: A New Political History*, PP. 218.
2. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ ገጽ 345-9።
3. ታደስ ዘወልዴ፣ *የአባላሸኝ ዘመን*፣ ገጽ 25-6
4. ከኩሎኔል ገብራይ ገብረ እግዚአብሔር ለጸሐፊው የተነገረ።
5. ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 146-7።
6. Greenfield, PP.224-9



# ምዕራፍ አሥራ ሰባት
# ኢትዮጵያ ለምን እንደምን ተሸነፈች

ጦርነቱ ኢጣልያ በአጥቂነትና በወራሪነት፣ ኢትዮጵያ በተከላካይነት የቆሙበት ነበር። የማይጨው ጦርነት የተደመደመው በኢጣልያ አሸናፊነት ነበር። እነዚህ ሁኔታዎች አያከራክሩም። የሚያነጋግረው ጉዳይ፡- ኢትዮጵያ ለምን፣ እንደምን በወቅቱ፣ በማይጨው ጦርነት ተሸነፈች? የሚለው ነው።

ይህንን ጠያቂ በጥልቅ መመርመር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ ማይጨው ላይ ድል ሆነች፣ ኢጣልያ ድል አደረገች። ባዶሊዮም ጦርነቱን እንደጨረሰ ቆጥሮ ፎከረ። ብዙ ሀገሮችም ጦርነቱ ያለቀ መስሎአቸው ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ያላትን ይዞታ አወቁ። ነገር ግን ጦርነቱ ቀጠለ። ጣልያንንም አበሳዋን አሳያት። ኢትዮጵያውያን ጦርነቱን በአርበኝነት መቀጠል ከቻሉ፣ ቀድሞውን ለምን ተሸነፉ? ከተሸነፉስ እንደምን ጦርነቱን መቀጠል ቻሉ? ኢትዮጵያ ለምን፣ እንደምን ተሸነፈች? የሚለውን ጥያቄ እንድንመረምር የምንገደደው በእነዚህ ምክንያቶች ነው።

1ኛ. **የጦር ግንባር ብዛት፡-** በአፄ ምኒልኩ የአድዋ ጦርነት ጊዜ የጦርነቱ ግንባር አንድ ብቻ ነበር። በአሰብ በኩል የነበረው ከቁጥር አይገባም። ስለዚህ ኢትዮጵያ ያለ፣ የሌለ ኃይልዋን አሰባስባ ለመከላከልና ጠላትዋን ድል መትቶ ለመመለስ ቻለች።

በማይጨው ጊዜ ግን እንዲህ አልነበረም። ኢጣልያ በሰሜንና በደቡብ ሶስት የጦር አውዶች ከፈተች። አንዱ ከአሥመራ የሚንቀሳቀሰው የሰሜኑ ጦር ሲሆን፣ እሱም ሁለት አፎት ነበረው። አንደኛው ከአክሱም ተነስቶ በሽሬ፣ በጎንደር፣ በጎጃም አድርጎ ወደ ደቡብ የሚዘልቅ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ከመቀሌ ተነስቶ በአምባላጌ፣ በማይጨው፣ በደሴ አድርጎ አዲስ አበባ የሚገባው ነበር።

ኢጣልያ የከፈተችው ሁለተኛ የጦር ግንባር ከሞቃዲሾ የሚንቀሳቀስ ሆነ። የዚህኛው አንደኛው አፎት በሞያሌ፣ በሸላምቦ፣ በቀብሪደሐር፣ በጅጅጋ፣ በሐረር፣ በድሬዳዋ በኩል አድርጎ አዲስ አበባ የሚገባ ነበር። ሌላኛው የዚህ ጦር አፎት በዶሎ፣ በቦረና ነገሌ፣ በይርጋ ዓለም አድርጎ አዲስ አበባ የሚገባ ነበር። ሶስተኛው ግንባር ደግሞ በአሰብ ገብቶ፣ በሰሜኑ የጦር ግንባር የተሰለፈውን ጦር ሸንጥ ደሴ ላይ እንዲቆርጥ የተሰማራ ነበር። እነዚህ የጦር ግንባሮች እያንዳንዳቸው ከአዲስ አበባ ሲለካ እስከ ሺህ ኪሎ ሜትር ድረስ ከፍተኛ ውጥረት ፈጠሩ። በጦርነቱ ላይ ወሳኝነት ካላቸው ሁኔታዎች አንዱ ይህ ነበር።

2ኛ. **የመሣሪያ እጥረት፡-** በአንድ ጦርነት ላይ ወሳኝነት ካላቸው ጉዳዮች ዋናው መሣሪያ ነው። ኢጣልያ ለጦርነቱ አስፈላጊ መስለው የታዩአትን መሣሪያዎች ሁሉ በመልክ በመልካቸው ለቁጥር በታከተ ብዛት አዘጋጅታለች። ለእግረኛው ጦር ብዙ ጉራሻ ጠመንጃ ከበቂ ጥይት ጋር

ሰርታ አስይዛለች፤ የእጅ ቦምብ አስጨብጣለች። የሚንቀሳቀስበት ታንክና መኪና፣ እንደዚሁም በቂ ስንቅ አቅርባለች። በሰማይ ደግሞ ቦምብ ጣይ አይሮፕላን፣ እንዲሁም የተከለከለ ልዩ መርዝ በገፍ አዘጋጅታ አገልግሎት ላይ እንዲውል አድርጋለች።

በወቅቱ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ ጦርነቱ እስከ ተቀሰቀሰበት ጊዜ አንዳች ዝግጅት አላደረገም። እንዲያውም ኢትዮጵያ እንኳን አዲስ መሣሪያ ልትጨምር፣ የነበራትንም በወግ አልያዘችም። ወደፊት እንደምንመለከተው፣ ለምሣሌም የኮረማሽን መሣሪያ ክምችት በአግባቡ አገልግሎት ላይ እንዲውል አላደረገችም።

3ኛ. ***የሠራዊት ሥልጠና፡-*** ኢጣልያ ጥሩ ሠራዊት አሠልጥናለች። የፋሽስት ካድሬዎችን በአመራር ረገድ አሰልፋለች። ከራስዋ ተወላጆችም በስተቀር የተቻላትን ያህል አስካሪ ወታደሮችን ከሊብያና ከሶማሊያ መልምላለች። በተለይ የኤርትራን ተወላጆች በደንብ አሰልጥና አሰልፋለች።

በኢትዮጵያ በኩል ሁኔታው ከዚህ የተለየ ነበር። ከውጭ የሚጠበቅ አንዳች ድጋፍ አልነበረም። ከራስዋም ሠራዊት የምኒልክ ነፍጠኛ ባዶውን የቀረ፣ የተበሳጨ፣ በአሠፋፈሩ የተበታተነ፣ በስሜቱም ያዘነና የተከዘ ነበር። በአዳዲሶቹ ሹማምንት የተቋቋመው ሠራዊት ደግሞ የሙያ ብቃት አላገኘም ነበር።

በወቅቱ ለኢትዮጵያም ሠራዊት ሥልጠና ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም፣ መጀመሪያ ነገር ለጥቂቶች ብቻ እንጂ ለሁሉ አልተዳረሰም፤ ለእነሱም ቢሆን በበቂ ሁኔታ አልተሰጠም፤ ለብለብ ሆነ። ከሥልጠናውም የሚበዛው በሠልፍ ሆኖ ማለፍ እና ግራ ቀኝ እኩል እየረገጡ መራመድ ነበር። የመከላከል እና የማጥቃትን፣ የመሣሪያ መለማመድን፣ እንደ ታንክ የመሣሰሉ መሣሪያዎች መጠቀምን አልጨመረም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ሠራዊት ታንክ በማረከ ጊዜ የነበረው ዕድል፤ ጠላት መልሶ እንዳይጠቀምበት ማቃጠል እንጂ እሱ ራሱ መጠቀም አልነበረም። አሰልጣኞቹ ፈረንጆች መሆናቸውም ሌላው ችግር የፈጠረ ጉዳይ ነበር።

4ኛ. **ሕዝባዊ *ሥነ* ልቡና፡-** እንደ መሣሪያ፣ በጦርነት ወቅት ወሣኝነት ከአላቸው ሁኔታዎች አንዱ የሕዝብ ሥነ ልቡና ነው። የኢጣልያ ሕዝብ አንድነቱን አጠናክሮ በአፍላ የለውጥ ሂደት ላይ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ አዲስ የተከሰተው የፋሽስት ፓርቲ የሚበዛውን ወገን ያረካ አመራር አስገኝቶለት ነበር።

በኢትዮጵያ በኩል ግን የነበረው ሁኔታ ከዚህ የራቀ ነበር። አስቀድሞ በልጅ ኢያሱና በንግሥት ዘውዲቱ መካከል በተካሄደው የሥልጣን ሽኩቻ፤ ኋላ ደግሞ ራስ ተፈሪ ከንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ሥልጣን በወሰዱበት መንገድ ልቡናው የተነካው ይበዛ ነበር። የንግሥት ነገሥታት ዘውዲቱን አሟሟት ሳይረሳ፣ የልጅ ኢያሱ ተጨምሮበት የተከዘው በርክቶ ነበር። በዚህ



ላይ አፄ ምኒልክ ጀምረውት የነበረው የማህበራዊ ውህደት ስለአልቀጠለ በደቡቡና በሰሜኑ ሕዝብ መካከል የልብ አንድነት አልነበረም።

5ኛ. **የጦር *አመራር*፡-** በጦር አመራር ረገድም በሁለቱ አገሮች፤ ማለትም፡- በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል፤ ልዩነት ነበር። የኢጣልያን ጦር እንደእነ ደቦኖ፣ ግራዚያኒ የመሳሰሉ አስበው የሚሠሩና (ጨካኝ ቢሆኑም) ቆራጥ የጦር መሪዎች ነበሩት። በፖለቲካውም ረገድ ደግሞ የፋሽስት ፓርቲ አፍላ ሥልጣን ላይ ነበር። በዚያ ሁሉ ላይ ሙሶሊኒ ራሱ በሙሉ ልቡ ጦርነቱን የመራ ሲሆን ንጉሡም፣ ጳጳሱም ተባበሩት።

በኢትዮጵያ በኩል እንደዚህ አልነበረም። በንጉሠ ነገሥቱ ቅሬታ የነበረው ብዙ ነበር። በጦር አመራራቸው ያላመነውም ቀላል አልነበረም። ምክር ቤቱም፣ ሠራዊቱም፣ መኳንንቱም ምክር የመስጠትና የመደመጥ ዕድል አላገኙም። ንጉሠ ነገሥቱ የፈረንጅ እንጂ የወገኖቻቸውን ምክር የማድመጥ ፍላጐት አልነበራቸውም። ከአዲስ አበባ እስከ ሀዩ ድረስ አንዳች ምክር አልተደረገም። ሁሉም ያቀበቀበው ሸሽቶ ነፍሱን ለማዳን ሲሆን፣ አብዛኛው ደግሞ ልቡ ወደጠላት አዘንብሎ ነበር።

6ኛ. **የጦርነት *ሥልት*፡-** የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ የሆነ የጦርነት ሥልት አለው። በኢጣልያ ወረራ ጊዜ በዚያ የመጠቀም ዕድል አላገኘም። እንዲዋጋ የተፈለገው በዘመናዊ ሥልት ነው። በእሱ ደግሞ ሥልጠናም፣ መሣሪያም አላገኘም።

በጣልያኖች በኩል ግን በእቅድ የመንቀሳቀስ ሥልት ነበር። የጦር ግንባሮች ሁሉ በአንድ ማዕከላዊ ዘዴ የተቀነባበሩ ነበሩ። እግረኛውና ታንከኛው፣ አየር ኃይሉና ባሕር ኃይሉ በኅብረት ሠሩ።

7ኛ. ***መረጃ፡-*** ኢጣልያ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዋ ጠንካራ ነበር። ሚሲዮናዊ፣ ዲፕሎማት፣ ነጋዴ፣ ጥናትና ምርምር አድራጊ እያስመሰለች በላከቻቸው እና በከፈለቻቸው ሰዎች አማካኝነት የኢትዮጵያን ሁኔታ አጠናች። ይህም አዲስ ነገር አልነበረም። በአድዋም ጊዜ ተጠቅማበታለች።[1] በዚህ ላይ ደግሞ የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች በሬዲዮ ቴሌፎን የሚያስተላልፉትን ምስጢር በመጥለፍ ተጠቀመች።

በኢትዮጵያ በኩል ግን የጣልያንን የውስጥ ሁኔታ ለማወቅ የተደረገ ሙከራ አልነበረም። የራስዋን ምስጢር የመጠበቅ ችሎታም እንኳን አልተገኘም። ከዚህ የተነሣ ነው የማይጨው ጦርነት የሚከፈትበት ቀን ምስጢር አስቀድሞ ለጠላት የደረሰው።

8ኛ. ***መገናኛ፡-*** የኢትዮጵያ ጦር መንገዱን የሚቀይስበት ባሕላዊ ዘዴ አለው። በዘመቻ ጊዜ መንገድ ለሠራዊቱ እንደሚያመች ሆኖ፣ ጠላት በማያውቀው፣ በማይጠረጥርበት መሥመር ይከፈታል። አንዱ ሠራዊት በአንድ መንገድ፤ ሌላው ሠራዊት በሌላ መንገድ ይጓዛል። ለየብቻው በተራ፣ በተራ ይዋጋል። በማይጨው ጊዜ እንዲህ አልተደረገም። ከንጉሠ ነገሥቱ

አውቶሞቢሎች በስተቀር ሌሎች አንድ መቶ መኪናዎች በሌሉበት በዛን ጊዜ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ኮረም የመኪና መንገድ ተሠራ። በየወንዙ ላይ ድልድይ ተጣለ። ነገር ግን ለጠላት መግቢያ እንጂ፤ ለኢትዮጵያ መከላከያ አልጠቀመም። የሕዝብ ጉልበትና ገንዘብ ለራሱ መጠቂያ ሆነ።

በኢጣልያ በኩል ሁኔታው ያለቀ ነበር። እግረኛው ሠራዊት በእግሩ ይጓዛል። በተያዘው አገር የመኪና መንገድ ይሠራል። ወደፊት በተከታታይ ለሚደረገው ጦርነት አዲስ በተዘጋጀው መንገድ በመኪና ይጓዛል።

9ኛ. **ክህደትና ከሀዲዎች፡-** እርስበርሱ በጥቅምና በሥልጣን ቢናቆርም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ጠላት ሲመጣበት አንድነቱን አጠንክሮ ይመክታል። ይህ ኢትዮጵያውያን የታወቁበትና ሌላው የተደነቀበት ባሕሪያቸው ነው። ነገር ግን በኢጣልያ ወረራ በጦርነቱ ጊዜ የተከሰተው ለየት ባለ ሁኔታ ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ባለሟሎች አብዛኞች ለጠላት አደሩ። እነቀኛዝማች ተክለ ማርቆስን፣ እነአምባሳደር ወልደማርያምን /ፓሪስ/ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። ሁሉን መዘርዘር ግን ጊዜ ማጥፋት ነው። በአንጻሩ ደግሞ ምንም ጥቅም ያላገኙ፣ ከዚያም አልፎ ቅጣት የደረሰባቸው ለኢትዮጵያ ቆሙ። በዚህ ረገድ ደግሞ አርባ የተገረፉትን ደጃዝማች በየነን፣ በእሥር ላይ የነበሩትን ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉን መጥቀስ ይገባል። የዚህ ዓይነቶቹም ሰዎች ቁጥር ብዙ ነው። ከሀዲዎች ምን ምን ሥራ እንደሠሩ፣ ምን ምን ጉዳት እንደአደረሱ ይህንኑ በሚመለከተው ምዕራፍ የተዘረዘረ ስለሆነ ከዚያው መመልከት ነው።

10ኛ. **የጦርነት ጊዜ፡-** ጦርነቱ የተደረገበት ጊዜ ወሣኝነት ነበረው። ዘመቻው ፈጣን፣ ውጊያው አጭር ነበር። በጥቅምት 1923 ዓ.ም ሙሉ ሥልጣን የያዙት ንጉሠ ነገሥቱ ገና አስተዳደራቸው አልጠነከረም ነበርና፣ ለኢትዮጵያ ምቹ ጊዜ አልነበረም። የጦርነቱ ጊዜ የተወሰነው በኢጣልያ ብቻ ነበር። እስዋም የተንቀሳቀሰችው አንድነትዋን ገንብታ፣ የጦር ኃይልዋን አዘጋጅታ፣ የዓለምን ሁኔታ አስተካክላና ገምታ በአመቻች ጊዜ ነበር።

ስለዚህ ኢትዮጵያ የተሸነፈችው በእነዚህና በሌሎችም ብዙ ምክንያቶች ነበር። ሁሉን መዘርዘር አይመችም። ማተኮር የሚገባው ኢትዮጵያ በእነዚህ ሁኔታዎች ከተሸነፈች በኋላ እንደምን ጦርነቱን መቀጠል ቻለች? ከሚለው ጥያቄ ላይ ነው። እሱንም ወደፊት እንመለከታለን።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ተክለፃድቅ መኩሪያ፣ *አፄ ምኒልክ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ ገጽ 161-70።



# ምዕራፍ አስራ ስምንት
## የገጠሩ ሕዝብ ሁኔታና የአርበኝነት አጀማመር

በኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ ወሳኙ ሕዝብ የገጠሩ ነው። የከተማው አይደለም። ለዚህም እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው በገጠር የሚኖረው ሕዝብ ከከተማው መብዛቱና በሀገር ጉዳይ የገጠሩ ሕዝብ ልቡና በአመዛኙ የማያወላውል መሆኑ ነው። በዘመቻው ጊዜ ገጠሩ ባዶ ሆነ። ጀግናው ወንዱ ዘመተ። ሴትና ልጅ፣ ሽማግሌ ብቻ ቀረ። የሚታዩት ነገሮች ሁሉ አስፈሪ ሆኑ። ጦርነቱ የገጠሩን ሕዝብ አስገነገነው። ዘማች ከማይጨው በኋላ ሲመለስ የታየው ሁኔታ ደግሞ ይበልጡኑ አስደነገጠው። የንጉሡ አገር ጥሎ ወደ ፈረንጅ አገር መሄድ አስገረመው። ፈረንጅ እዚህ አገር ሲገባ እሳቸው ወደ ፈረንጅ ሀገር የሄዱበት ጥበቡ አልታይህ አለው። የመሣፍንቱ፣ የመኳንንቱ ክህደት አስደነቀው።

ከዘመቻ የተመለሰው ሰው ጥቂት ነው። የሚበዛው በጦርነቱ ላይ ሞቶአል። መርዶው፣ ውሎ የሚደረገው በእያንዳንዱ አካባቢ፣ በየተራ ሆነ። ሁኔታዎች ተዘበራረቁ። ትርምስምሱ ወጣ። እኔ ራሴ በአካባቢዬ ያየሁትን ከመግለፅ በስተቀር ሌላ ማስረጃ መስጠት አልችልም። ስለዚህ በቡልጋ የደረሰውን በአጭር፣ በአጭሩ እመለከታለሁ።

ከማይጨው ጦርነት በኋላ በህይወት የተረፈው የኢትዮጵያ ሠራዊት አመላለስ አሳዛኝ ነበር። አብዛኛው አለ መሣሪያው እና ራቁቱን ነበር። ሌላው የተበጫጨቀ ትንሽ ልብስ ቢኖረው እያፈረ ሌሊት ተደብቆ ከቤቱ የገባም አለ። እኔ ከማውቃቸው ሰዎች መሣሪያቸውን እንደያዙ፣ የጦር ልብስ እንደለበሱ ከትውልድ ሀገራቸው የገቡ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴና ሶስት አሽከሮቻቸው ብቻ መሆናቸው እስከ ዛሬም ትዝ ይለኛል።

ከዘመቻው መልስ ሕዝቡ እየተሰባሰበ መምከር ያዘ። የመጀመሪያው ጉዳይ መሪ መምረጥ ነበር። እኔን ምረጡኝ የሚል አልነበረም። ሁሉም ፈርቶ እኔ አልችልም፣ አልፈልግም ባይ ሆነ። ከብዙ ምክር በኋላ በየአካባቢው የጉበዝ አለቃዎች ተመረጡ። የጉበዝ አለቆች ደግሞ እየተሰባሰቡ ይማከሩ ጀመር። የአንዱ አገር የጉበዝ አለቃ አንድ፣ የሌላው ሌላ ይላል፤ አይስማሙም፣ ይከፋፈላሉ። ሕዝቡም እነሱን እየተከተለ ይከፋፈላል። ግለሰቦች ሲሰለቻቸው የግላቸውን እርምጃ ይወስዳሉ። ለዛሬው አንባቢ ይህ አገላለፅ ልብወለድ ይመስለዋል። ግን እውነት ነው። አንዳንድ ማስረጃ ለመስጠት እፈልጋለሁ።

ሙገሬ ዛላ፣ ሜጢ በሚባለው ቦታ "ለኢጣልያ እንመን፤ የለም እንሸፍት" በሚል ሐሳብ ሕዝብ እርስ በርሱ ተከፋፍሎ ታላቅ ክርክር ተካሄደ። "እንሸፍት!" በሚለው ሐሳብ ተስማማ። አቶ ህብተ ኢየሱስ የሚባል ሰው እንቢ ስላለ ሀገር አደመበት። "ከቤቱ ሰው ቢሞት ላያቃብረው፣ እሳት

ላያስጭረው፣ ከንጉሥ መንገድ ውጭ ውሃ ላያስቀዳው ተማማለበት። ከብቱ አንድ ቀን ጫውሶ ዋለበት። ሚስቱ ጥላው ሄደች። ሲጨንቀው ማሩኝ ብሎ ገባ። በዚያች የገጠር አካባቢ የሽፍትነት ሥራ እንዲህ ተጠነሰሰ።

በበረከት ወረዳ ዋጨ ከሚባል ቦታ አቶ በየነ ወልደ ገብርኤል የተባለ ሰው ነበር። ሀገሩ አልስማማለት ስላለ እሱ ብቻውን ሸፈተ። ጠላትም ወሬውን ሰምቶ ከበበው። በተከበበ ጊዜ አንድ ለበን ጠመንጃ ከአሥር ጥይት ጋር ብቻ ነበረው። ከሁለት ቀን የተኩስ ልውውጥ በኋላ በየነ ሞተ። አሟሟቱም ራሱን በመግደል ነበር። የሞተውም ከአሥሩ ጥይት በስምንቱ ስምንት ሰው ገድሎ፣ ዘጠነኛዋን እሱ ራሱ ጠጥቶ ነበር። አሥረኛዋ መጠባበቂያ ነበረች።

የጠላት ኃይል እያየለ ሲሄድ ጦርነቶች ተቀሰቀሱ። ጦርነቱ ከባድ፣ አስደንጋጭና አስፈሪ ሆነ። ቀስ በቀስ ጀግናው ተንቀሳቀሰ። እርስበርሱ እየተማማለ ሽፍትነቱን ያዘ። ጠላት ሊያውቅና ሊገነዘበው የማይችል አዲስ ሁኔታ ተፈጠረ። በዋናው ጦርነት ጊዜ የታዩት ነገሮች ሁሉ ፍርስ ሆኑ። የጦሩ ግንባር በየተራራው፣ በየሸንተረሩ፣ በየጎጡ ሆነ። አሸነፍኩ ብሎ በድንፋታ የገባው የጠላት ጦር ግራ ገባው። ታንክ የማይደርስበት፣ መድፍ ሊንቀሳቀስ የማይቻልበት፣ በአይሮፕላን በመደብደብ ውጤት የማይገኝበት አዲስ የጦር ሥልት ተከፈተ። ምንም አይነት ሥልጠና ሳያስፈልገው ሽፍታው በዱላ፣ በጦር፣ በጐራዴ የጠላቱን መሣሪያ እየነጠቀ መሣሪያ ጨበጠ። የመሣሪያውንም አጠቃቀም እርስበርሱ ተማማረ። ለየግል ጥቅማቸው ከሚከፋፈሉት ሹማምንት ሲላቀቅ፣ ሥነ ልቡናው አንድ ሆነ። በቀድሞዎቹ መሪዎች ፈንታ አዳዲስና ቆራጥ መሪዎች አገኘ። አዳዲሶቹ መሪዎች ለሹመት፣ ለሽልማት ሳይሆን ለሀገር ነፃነት፣ ለወገን ደህንነት የቆሙ መሆናቸውን አረጋገጡ። ሕዝቡም ተከተላቸው። የጦርነቱ ሥልት ከፈረንጅኛ ዘዴ ተላቅቆ ፍፁም ኢትዮጵያዊ ሆነ። ምሥጢራዊ መረጃ ከሀበሻ ወደ ፈረንጅ መንቆርቆሩ ቀርቶ ከፈረንጅ ወደ ሀበሻ ይፈስስ ጀመር። ጣልያን የሚያስበው ሁሉ ለሽፍቶቹ ከየቦታው በሰው ይደርሳቸው ጀመር። የመገናኛ ችግር የሚያጋጥመው ጠላት ራሱ ሆነ። የሽፍቶቹ ሥራ በየቀዬአቸው መዋጋት ስለሆነ፣ የመጓጓዣ ችግር አልነበረባቸውም። ከሀዲዎች የክህደት ማቃቸውን ለብሰው ከጣልያን ጉያ ተሸጐጡ። ከሕዝብ ስለተነጠሉ አንዳች ማድረግ ተሳናቸው። ጣልያን የጦርነቱን ጊዜ በማፋጠን ያገኘውን ጥቅም፤ ሽፍቶች የጦርነቱን ቦታ በማብዛትና ጊዜውን በማራዘም አጠፉበት። ግራ አጋቡት። ሥራቸውም በሕብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ እያገኘ ሲሄድ፣ ከሽፍትነት ወደ አርበኝነት ተሸጋገረ።

አርበኞች የፈፀሙትን ሥራ ለመገንዘብ የጦርነት፣ የአርበኝነት፣ የታጋይነት፣ የሽፍትነት ልዩነት ምን ላይ እንደሆነ ለይቶ ማወቅ ይገባል። ሁለት መንግሥታት የሚያካሂዱት ውጊያ ጦርነት ይባላል። አርበኝነት ደግሞ



አንድ ሕዝብ በሌላ አገር ሕዝብ ተወርሮ ነፃነቱን በተገፈፈ ጊዜ መንግሥት በሌለበት ሁኔታ የሚያካሂደው ትግል ነው። ታጋይነት አንድ ግለሰብ ብቻውን ወይም ከጥቂቶች ጋር ስለሀገር የሚያካሂደው ተጋድሎ ነው። ሽፍትነት ግን በግል ጉዳይ በመንግሥት ላይ አመፅ ማካሄድ ነው።

የኢጣልያ ወረራና የኢትዮጵያን የተጋድሎ ስልት ስንመለከት ከእነዚህ ሦስት የውጊያ ስልቶች በሁለቱ፣ ማለትም በጦርነትና በአርበኝነት የተካሄደ ሆኖ እናገኘዋለን። ዝርዝር ሁኔታውንም ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

1ኛ. የወልወል ግጭት ከተከሰተበት ከህዳር 27 ቀን 1927 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 24 ቀን 1928 ዓ. ም ድረስ የተካሄደው ውጊያ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ቤኒቶ ሞሶሎኒ በርዕሣነ ብሔርነት የቆሙበት የሁለት መንግሥታት ጦርነት ነበር።

2ኛ. ንጉሠ ነገሥቱ ሀገር ጥለው ከሄዱበት ከሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም አንስቶ ተመልሰው በኦሜድላ በኩል የኢትዮጵያን መሬት እስከረገጡበት እስከ ጥር 16 ቀን 1933 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያውያን ያካሄዱት ጦርነት ለሀገር የመከላከል የአርበኝነት ተጋድሎ ነው።

3ኛ. ጥር 12 ቀን 1933 ዓ.ም የጐንደር ጦርነት ተፈጽሞ ጀነራል ናዚ እስከተማረከበት እስከ ህዳር 1934 ዓ. ም ድረስ ያለው ደግሞ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥታት መካከል የተካሄደ ጦርነት ነው። የእንግሊዝ ድጋፍ ከኢትዮጵያ ወገን መሆኑ ሁኔታውን አይለውጠውም።

4ኛ. በዚህ ፅሑፍ ውስጥ በአንዳንድ ቦታ ሽፍትነት እንደነበረ ተገልፆአል። ይህ አገላለፅ ሰዎች በግላቸው የተጫወቱትን ሚና በዚያን ጊዜ በነበረው አስተሳሰብ ለማሳየት እንጂ፣ ለግል ጥቅማቸው ያካሄዱት ትግል አለመሆኑን አንባቢ እንዲረዳው ያስፈልጋል።

የአዛኸር ሙሉ ሰውነ የዕለት ማስታወሻ መነሻ ብናደርግ የአርበኛው ሐሳብ ከጠላት ጋር ተያይዞ ለመሞት፣ ባይሞትም ስቃይ ለማሳየትና ለማየት፤ ለሀገርና ለወገን ለኢትዮጵያ መንግሥት ሠንደቅ ዓላማ ለመሰዋት ነበር። እንደ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ አባባል ደግሞ ለሃይማኖትና ለሀገር ለመሞት ነበር። የአብዛኛው አርበኛ ሐሳብ ከዚህ እምብዛም የተለየ አልነበረም። እንደ ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ ያሉት ደግሞ ለንጉሠ ነገሥታቸው የቆሙ ነበሩ።

ከዚህ ላይ ሊጠቀስ የሚገባው ነጥብ በዚያን ጊዜ የአርበኝነት ሥራ በዓለም ውስጥ የተለመደ እንዳልነበረ ነው። በዋናው ጦርነት ድል ከሆኑ፣ መሪአቸው ጥሎአቸው ከሄደ ወይም ከሞተ በኋላ በራሳቸው ኃይል እየተንቀሳቀሱ ከጠላታቸው የታገሉ ሀገሮች እስከዚያን ጊዜ ድረስ አልታዩም። ብዙ ሀገሮች በቀላሉ ለቅኝ ግዛት የተጋለጡት፣ ባደሊዮም ጦርነቱን ጨረስኩ፣ ሰላም ሆነ ያለው በዚህ ዓይነት የአርበኝነት ተጋድሎ መኖሩን ስለአላወቀ

ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ የአርበኝነት ተጋድሎ መሠረት መሆንዋን መገንዘብ ይገባል።

በዚያን ጊዜ በተካሄደው የአርበኝነት ተጋድሎ የመጀመሪያው ትንቅንቅ ከጣልያን ከራሱ ጋር አልነበረም፤ ከባንዳ ጋር እንጂ። የባንዳው ኃይል ቀላል አልነበረም። ለጥቅም በተገዙ ከሀዲ መኳንንት እየተመራ ለመደበኛው የጠላት ጦር ግንባር ቀደም እየሆን በብዛት የሚግተለተል የገበሬ የባንዳ ሠራዊት ነበር። በአብዛኛው ከአካባቢው የተመለመለ በመሆኑ መውጫ መግቢያውን ስለሚያውቅ የማጥቃት ኃይል ነበረው። በመሆኑም የመከላከሉ ሥራ ከበደ። በዚሁ ከቀጠለ የአርበኝነት ሥራ ለማካሄድ አይቻልም። በምክርና በተግሣፅ ማስታገስ የተቻለው ጥቂቱን ብቻ ሆነ። ስለዚህ የጠላት መሣሪያ እየሆኑ ምስጢር በሚያቀብሉና ነገር በሚየመላልሱ፣ መሣሪያ ታጥቀው ከጠላት ጐን በቆሙ ባንዶች ላይ የኃይል እርምጃ መውሰድ ግድ ሆነ።

በባንዳ ላይ የኃይል እርምጃ የመውሰድ ጉዳይ አስፈላጊ የመሆኑን ያህል በጥንቃቄ እንዲፈፀም አስፈለገ። እየተገደደ ያለፍላጐቱ አንዳንድ ሥራ የሚሠራውን ሁሉ መግደል ብዙ ሰው መፍጀትና ሀገርን እንደሚጎዳና ወዳጅ፣ ዘመድ መቀየሙ ስለማይቀር ችግሩ ቀላል እንደማይሆን ታወቀ። የእያንዳንዱ ባንዳ ግብር እየተመረመረ በፍርድ ይቀጣ ጀመር።[1] አርበኛ በባንዳ ላይ እንደአሻው እርምጃ ወስዶ ቢሆን ኖሮ፣ የሕዝብ ድጋፍና ትብብር አያገኝም ነበር። ስለዚህ በጦር ሜዳ ካልሆነ በስተቀር ባንዳ ያለፍርድ እንዳይገደል ጥንቃቄ ተደረገ። ይህ አሠራር ጥሩ ውጤት ሰጠ።

በዚህ ዓይነት የኢትዮጵያ ሰው ከሦስት ተከፈለ። አንዱ ወገን ለሀገር ለነፃነት ብሎ አርበኝነትን ቀጠለ። ሁለተኛው ወገን ከጠላት ጐን በመቆም የሀገር ጠላትነቱን በግብር ማረጋገጡን ያዘ። ሦስተኛው ወገን ሰላማዊ ኑሮውን ተከተለ።

ከዚህ ለታሪክ አወንታ ሲባል መጠቀስ ያለበት ጉዳይ፡- ለጠላት መሣሪያ እየሆኑ በሀገርና በወገናቸው ላይ ከባድ በደል የፈፀሙ ወንጀለኞች ለፍርድ እንኳን ሳይቀርቡ መቅረታቸው ነው። እሱን ደግሞ በቦታው እንመለከታለን።[2]

**<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>**

1. *ሙሉሰው ምትኩ፣ ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ*፣ ገጽ 9 እና 16።
2. ከድል በኋላ ትግል የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።



# ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ
# የሲዳሞ ተጋድሎ

"እንዴት ሲዳሞን ወንድ የሌለበት አድርጐ ጠላት ይግባበት?" ተብሎ ከንጉሠ ነገሥቱ የተላለፈለትን አዋጅ የሲዳሞ ሠራዊት ተቀበለ። ያፈገፈገው ተመልሶ ከጦር ግንባር ገባ። በየአለበት እየተቆረጠ የቀረውም ተመልሶ በአለቆቹ ዙሪያ ቆመ። ነገር ግን ማዕከላዊ አመራር ሳያገኝ ቀረ። ድጋፍም የማያገኝ መሆኑን አወቀው።

ድኑን በተባለው ቦታ ዝግጅቱን ቀጠለ፣ አጠናቀቀም። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጦራቸውን ይዘው ግንቦት 25 ቀን 1928 ዓ.ም ከዋደራ ድኑን ገቡ። በደረቅ ሰማይ ዝናም ዘንሞ ውሃ እየጠጡ ተጓዙ። ነገር ግን የጦር እቅዳቸውን በሥራ ላይ ከማዋላቸው በፊት ከሃዲው ፊታውራሪ አደመ ነፍሶ ከእሳቸው ተነጥሎ ከጣልያኖች ጋር ተቀላቀለ። የጦር ሚስጢራቸውንም ለጠላት ሰጠባቸው።

ጠላት የኢትዮጵያን ጦር ምሥጢር ከአደመ ከተረዳ በኋላ ግንቦት 9 ቀን 1928 ዓ.ም ድኑን የተባለውን አካባቢ በአይሮፕላን መደብደብ ጀመረ። በዚህ ጊዜ በአርበኞች ዘንድ ምክር ተደርጐ በፍጥነት የነገሌን ምሽግ ለማጥቃት ተወሰነ። ጠላት በ25 ካሚዮን እግረኛ ጦር አቀረበ፤ እንዲሁም ለካሚዮኖችና ለታንኮቹ ደጀን አደረገላቸው። ጠላት ፈጥኖ ተንቀሳቀሰ። ግንቦት 11 ቀን ጦርነቱ ተከፈተ። እነ ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ እያነጣጠሩ በመድፍ የጠላትን ወታደር ረፈረፉት። የኢትዮጵያ ጦር ከፊት ለፊት በብርታት ተዋጋ። ጠላት ወደኋላው ለመመለስና ከምሽጉ ለመሸጐጥ ሞከረ። ነገር ግን አስቀድሞ ከኋላ ዞሮ መንገዱን ቆርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ይጠዘጥዘው ጀመር። ወዲያው የጨበጣ ውጊያ ተያዘ። ጥይት ከመተኮስ ይልቅ በጐራዴ መጨፍጨፍ ተሻለ። አይሮፕላኖች በሚያካሂዱት ድብደባ የሚደርሰው ጉዳት የጋራ ሆነ።

ለእርዳታ ከነገሌ በታንክና በካሚዮን የመጣው የጠላት ጦር አንዳች ማድረግ አቅቶት ወደ ምሽጉ ተመለሰ። እፁብ ድንቅ የተባለ ውጊያ ተካሄደ። ከጥዋቱ በ4 ሰዓት የተጀመረው ጦርነት ከቀትር በኋላ በ8 ሰዓት በኢትዮጵያውያን አሸናፊነት ተፈፀመ። አንድ መቶ ሃያ ድግን መትረየስ፣ አሥራ ሁለት ባለውሃ መትረየስ፣ አንድ ሺህ አርባ ሰባት አልቤን ጠመንጃ፣ ብዙ ሺህ ጥይት፣ አንድ መቶ ሃምሣ አራት ምንሽር፣ ሦስት ሳንፊል የመገናኛ ሬዲዮ፣ ሦስት መቶ የመድፍ ጥይት፣ ሦስት መቶ ሃምሣ በቅሎ ተማረከ። ሃምሣ ስምንት ኢጣልያኖች፣ ሰባት መቶ ሱማሌዎች ሞቱ። እነ ፊታውራሪ ወልደ ሚካኤል ኃይሉ ነገሌ ከምሽጉ የጣልያኑን መኰንን ማርከው አመጡ። በኪሱም "ልጃችን አደራህን ...ወደፊት አትሂድ፣ እንዳትሞት፤

ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ናቸውና" የሚል ወረቀት ተገኘ፡፡ ከወላጆቹ የተፃፈለት ነበር፡፡

ጣልያን በዋደራ በኩል ሰብሮ ለመግባት የነበረው ሃሳቡን በአደመ ነፍሶ ምክር ለውጦ፣ በሜጋ በኩል ዞሮ ሲዳሞ ለመግባት አሰበ፡፡ ይህንን የሰማው የኢትዮጵያ ጦር ክንዱን ወደ ዋደራ መልሶ ነዋሪ ለመምሰል ቦታ እየተከፋፈለ ቤት መሥራት ያዘ፡፡ ቤተክርስቲያንም ሠራ፡፡ በአንፃሩ ደግሞ መልካ ጉባ ላይ የነበረውን ድልድይ ሰብሮ የጠላቱን ዕቅድ ለማሰናከል ወሰነ፡፡

ለዚሁ ለድልድዩ ሠበራና ለመንገድ ቆረጣ የተመረጡ ወታደሮች ተላኩ፡፡ ነገር ግን ከታሰበው ቦታ ሳይደርሱ ቆርቆሮ ከተባለው ቦታ የጠላት ጦር ገጠማቸው፡፡ ታላቅ ጦርነት ተደረገ፡፡ ውጊያውም ስምንት ቀን ፈጀ፡፡ ብዙዎች ሞቱ፤ ብዙዎቹም ቆሰሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የተላከው የኢትዮጵያ ጦር ዓላማውን መፈፀም አቅቶት ወደ ዋደራ ተመለሰ፡፡

ጣልያን ከነገሌ ወደ ሜጋ ጉዞ ጀመረ፡፡ የኢትዮጵያ ልጆች በሩን ይዘው ጠበቁት፡፡ ሰኔ 19 ቀን ገጠሙት፡፡ ከጥዋት ጀምረው ሲዋጉ ውለው እግረኛውን ጦር መለሱት፡፡ ነገር ግን በአይሮፕላንና በታንክ እየታገዘ መጥቶ አስለቀቃቸው፡፡ ብዙ ቆራጥ ጀግኖች ወደቁ፡፡ ራስ ደስታ የዚህን ጉራ መከፈት እንደሰሙ የደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶን አሽከሮች ጨምረው ጦር ላኩ፡፡ ወታደሩም ገላግሌ የተባለ መድፍና ሁለት አይሮፕላን ማውረጃ አርሊከን፣ ሰባት ድግን መትረየስ በመያዝ ደርሶ ጀባ ሜራ የተባለውን ቦታ ያዘ፡፡

ሰኔ 27 ቀን ጠላት በሩን ለመስበር መጣ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር እንደልማዱ መክቶ በጀግንነት ተዋጋ፡፡ ጠላቱንም ድል አድርጐ አባረረው፡፡ አሥራ ሰባት ኢጣልያውያንና ብዙ የሶማሌ ወታደር ተገደለ፡፡ ሰባት ድግን መትረየስ፣ ሦስት መቶ ጠመንጃ፣ ሁለት ታንክ ተማረከ፡፡ ነገር ግን በታንኮቹ ሊጠቀምባቸው አልቻለም፡፡

አልፎ አልፎ ጦርነት ቢያደርግም የኢትዮጵያ ጦር ጀባ ሜራን ሳይለቅ ምሽጉን አጥብቆ እስከ መስከረም ወር 1929 ዓ.ም መጨረሻ ተቀመጠ፡፡ ጠላት በበርጉዲ በኩል አዲስ መንገድ እያስመነጠረ መምጣቱ ተሰማ፡፡ በኢትዮጵያ በኩል ዝግጅት ተደረገ፡፡ አንድ ቡድን ወደ አማሮ ተሻገረና በሀገረ ማርያም ጀርባ በፈንጭ ውሃ በኩል ቦታ ያዘ፡፡ የኢትዮጵያ ልጆች መፎካከርና ለሥልጣን መጓጓታቸውን ትተው በአንድ ልብ ቆሙ፡፡ በመተባበር አያሌ ጦርነት አካሂደው አያሌ ድል በማግኘት ከዘጠና ቀን ላላነሰ ጊዜ የጀባ ሜራን በር ተከላከሉ፡፡

ይህ ጉራ የማይበገርለት ስለሆነ የጠላት ጦር ከሀገረ ማርያም አንስቶ እስከ ጀባ ሜራ ጋራ ጥግ ሥር ያለውን ቦታ ያዘ፡፡ ጉሎልቻ ከተባለው ሥፍራ ላይ ሠፍሮ የጋራውን ጥግ መከታ አድርጐ ተቀመጠ፡፡ የኢትዮጵያ ጦርም በሊላ ዳኒሣ በኩል ዞሮ አደጋ በመጣል ኢጣልያኖች ገድሎና ማርኮ ተመለሰ፡፡ በዚህ ዓይነት በየጊዜውና በየቦታው አደጋ እየጣሉ አደከሙት፡፡ የመድፍ



ድብደባውም ሦስት ወር ሙሉ ጦርነቱን ሳያስታግስለት ቀረ፡፡ ስለዚህ በትልቅ በርሜል መርዝ አምጥቶ ጣለ፡፡

ይህ በኢትዮጵያ ወታደሮች ሠፈር ላይ የተጣለው አንድ በርሜል መርዝ ስለአልፈነዳ ለጊዜው ጉዳቱ እምብዛም ሆነ፡፡ ነገር ግን በርሜሉ ተሰንጥቆ ስለነበር ነፋስ ወደሚነፍስበት ወገን እየተነፈሰ በመዋል፣ በማደር አካባቢውን አቃጠለው፡፡ ሰውም፣ እንስሳትም ገደለ፡፡ መሬቱ ቀይ ቀለም እንደተነከረ ጨርቅ ወረዛ፡፡ የከብት ማሰማሪያ የነበረው የግጦሽ ሣር ተቃጠለ፡፡ መሬቱም ለብዙ ዘመን አመድ ሆነ፡፡

የኢጣልያ ጦር ጥቅምት 1 ቀን 1929 ዓ.ም በሠላሣ አይሮፕላን እየደበደበ ብዙ ታንክ አስቀድሞ በእግር መጣ፡፡ የኢትዮጵያም ጦር ተከላከለ፡፡ በእጅ ቦምብ ጭምር ከፍ ያለ ጦርነት ተካሄደ፡፡ በጀግና ላይ ጀግና ተረባርቦ ወደቀ፡፡ ኢላ ዳኒሣ በተባለው በር የተሠለፉ የኢትዮጵያ ልጆችም እንደዚሁ አደረጉ፡፡ የጃባ ሜራ ሜዳ በደም ታጠበ፤ በጠላትም፣ በወገንም ሬሣ ተሸፈነ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ተሸንፎ በሩ ተከፈተ፡፡ ጠላትም እንደተመኘው ጥቅምት 5 ቀን ገባ፡፡ መግባቱንም በዚያ ለነበረው ሕዝብ ጥቅምት 6 ቀን ነገረ፡፡ በዚህ ጦር ሜዳ ለወደቁ ለእነ ደጃዝማች ደባይ ወልደአማኑኤል በታሪክ ፊት ክብርና ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በወቅቱ በደጃዝማች ገብረማርያም የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ወደጃባ ሜራ ተጉዞ ነበር፡፡ ነገር ግን እሱ ሳይደርስ ጦርነቱ ስለአለቀ ሃሳቡን መፈፀም ሳይችል ቀረ፡፡ ስለዚህ በደመርሶ አካባቢ የሚገኙትን ድልድዮች አስፈርሶ፣ ስልኩንም በጣጥሶ፣ አንጥፎ ይጠባበቅ ጀመር፡፡ ጠላትም እያጓራ መጣ፡፡ ጥቅምት 9 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ አካባቢው ለስለላ በአራት ካሚዮን መጥተው የነበሩ የጣልያን ወታደሮች ጥይት ሲሰሙ አምልጠው ወደ ኋላቸው ተመለሱ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ፍስሐ ገነት ላይ ለመዋጋት ተዘጋጀ፡፡

የፍስሐ ገነት ጦርነት ጥቅምት 11 ቀን 1929 ዓ.ም ጥዋት ለ12 ሰዓት ሩብ ጉዳይ ተከፈተ፡፡ ጣልያን በአራት ካሚዮን ሞልቶ ወታደር አመጣ፡፡ የኢትዮጵያ መድፈኛ ወደፊት ሦስቱን መኪናዎች አሳልፎ አራተኛውን ካሚዮን ቢመታው መንገዱ ተዘጋ፡፡ ከዚያም አከታትሎ ሌሎቹን ሦስት አጠፋቸው፡፡ እግረኛውንም የኢትዮጵያ ጦር ከመኪና ሳይወርዱ ተቀባበለው፡፡ በመኪናዎቹ ውስጥ የነበሩ የኢጣሊያም፣ የሶማሊያም ወታደሮች አለቁ፡፡ መሣሪያውን ኢትዮጵያውያን ማረኩት፡፡ ጠላትም ተዘጋጅቶ ነበርና ወዲያው ሌሎች አራት ታንክና አራት አውቶሞቢሎች ቢያቀርብ የኢትዮጵያ መድፈኛ አራቱንም ታንኮች በፍጥነት አቃጠላቸው፡፡ ወዲያው የነጭ እግረኛ ጦር ደረሰ፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ከየጫካው እየወጣ እንደሠርገኛ ተቀላቀለው፡፡ ጣልያን በ9 ሰዓት በተጨማሪ አምስት ታንክና አምስት ካሚዮን ወታደር አመጣ፡፡ የኢትዮጵያ መድፈኛ ሦስቱን ታንኮች ወዲያው አወደማቸው፡፡ የኢትዮጵያ ጦር የአይሮፕላኑን ድብደባ ከምንም ሳይቆጥር ውጊያውን ቀጠለ፡፡ ሌላ ደጀን

የጠላት ጦር ከሀገረ ማርያም አመጣ። ከሌሊቱ 5 ሰዓት ሆነ። የጠላት ጦር ተተኪ ሲደርስለት፣ የኢትዮጵያ ጦር ምንም ረዳት አላገኘም። ጠላትም ጦርነቱን የሚያጣድፈው ይህንን አይቶ ነበር። በዚህ ዓይነት ጠላት የባንዲን ጎራ ሰብሮ፣ የፍስሐ ገነትን ከተማ እጁ አደረገ። በዚህ ጦርነት ላይ የነበሩ ሁሉ፣ በተለይም መድፈኛው ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ ምስጋና ይገባቸዋል።

ከዚህ ጦርነት በኋላ በኢትዮጵያ በኩል እንደገና ምክር ተደረገ። ዋና ዋናዎች ሁኔታዎች፡- የደጃዝማች ገብረማርያም መቁሰል፣ ብዙ የጦር አለቆችና ወታደሮች መውደቅ፣ የተረፈውም መበተኑ ነበር። ጦሩም መክሮ በርትተን ከሌሎች አርበኞች ጋር በመቀላቀል ትግላችንን እንቀጥል በማለት ወሰነ። በዋናው መንገድ ለመጓዝ ስለአልተቻለ፣ በጫካ ውስጥ አዲስ መንገድ እየተመነጠረ ጉዞ ተደረገ። በዚያም ጠላት ተከትሎ መጣ። ተከላክለው በመመለስ ጉዞው ቀጠለ። የተረፉት ሰዎች ሠላሣ ስድስት ብቻ ስለነበሩ አንድ ባለጋሻ መድፍ ይዞ መንቀሳቀስ አስቸገረ። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ግን "የምመካና የምኮራበትን መድፌን ትቼ አልሄድም" አሉ። ከመድፋቸው ጋር መሞትን መረጡ። ወታደሮቹ መድፉን እየጐተቱ ከጥቅምት 11 እስከ 13 ቀን ድረስ እህል ሳይቀምሱ ወደ ሀገረ ሰላም ተጓዙ። ከዚያም ጥቅምት 16 ቀን ቡሌ ከሚባለው ቦታ ደርሰው ከሰው ተቀላቀሉ። ከዚያ ደግሞ ጥቅምት 1 ቀን ሀገረ ሰላም ከተማ ገቡ።

ዋደራ በተባለው ቦታ መቀመጥ የማያዋጣ ሆኖ ስለተገኘ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው ከ9 ወር ቆይታ በኋላ የጦር ሠፈራቸውን ነቅለው ወደ አለታ ወንዶ ህዳር 2 ቀን ተነስተው ህዳር 5 ቀን በመድረስ ተፈሪ ኬላ የተባለውን ቦታ ያዙ። ደጃዝማች ገብረ ማርያም ጥቅምት 28 ቀን ከዚሁ ቦታ ደርሰው ስለነበር የሁለቱ ጦር ለመቀላቀል ቻለ።

ጥቅምት 29 ቀን 1929 ዓ.ም አካባቢውን ይደበድቡ ከነበሩ አይሮፕላኖች አንዱ ልኩ ከተባለው ቦታ ተሰናክሎ ወደቀ። በአካባቢው የነበሩ አርበኞች በውስጡ የነበሩትን ሁለት ኢጣልያውያን ቆራርጠው ጣሉአቸው። ሌሎች ጣልያኖች ደግሞ ገሚሱ ይርጋ ዓለም ሚካኤል፣ ሌሎች መናፈሻ ተክለ ሃይማኖት በየዛፉ ላይ ተቆራርጠው ተሰቅለው ተገኙ። በአይሮፕላን ውስጥ ወረቀት ተገኘ። ይህ መኰንን ወደ ሮም ለመሄድ እንዲያስፈቅድለት ለአንድ ወዳጁ ደብዳቤ ፅፎ ያገኘው መልስ ኖሮአል። ደብዳቤው "...ዛሬ የእኛ አገር የሚመኝዋት አይደለችም። እኛም ወደ እናንተ ለመምጣት እናስባለን። በኢትዮጵያ የተነሣ በዚህች በጥቅምት ወር በድፍን አውሮፓ የተለኮሰው እሳት ምንጊዜም መብረጃ የለውም..." ይል ነበር።

ወደ ዋናው ጉዳያችን ስንመለስ፣ በአርበኞች በኩል ለአዲስ ፍልሚያ ዝግጅት ተደረገ። ከአሥራ ስምንት ዓመት በላይ የሆነ ወንድ ልጅ ሁሉ እንዲከት አዋጅ ታወጀ። ሠራዊቱም አዋጁን አክብሮ፣ ያለውን መሣሪያ ይዞ



ተሰባሰበ። ለሌላው ደግሞ ከጦሩ ግምጃ ቤት ተሰጠው። ይርጋ ዓለም በዕረፍት ላይ የቆዩት 500 ኤርትራውያን መጥተው ተቀላቀሉ። ህዳር 7 ቀን አንድ ቡድን ከጠላት በስተጀርባ ዞሮ ስለላ ከአካሄደ በኋላ የጦርነቱ ዕቅድ በተገኘው መረጃ መሠረት ተሠራ። ወታደሩ የመድፍና የቦምብ አደጋ በማያገኘው ዓይነት ተደለደለ። ከተፈሪ ኬላ ቀኝ ያለው ተራራ ለመድፈኞች፣ በስተግራ ያለው ለአይሮፕላን ተከላካዮች፣ ማለትም፡- ለባለ ኦርሊኮኖች ተሰጠ። የጦር መሪዎች ሠራዊታቸውን ይዘው ከረባዳው ሥፍራ አደፈጡ። ጠላት ሊያውቀው በማይችል ሁኔታ ተዘጋጁ።

ጠላት ጉዞውን ቀጥሎ ተፈሪ ኬላ ደረሰ። የኢትዮጵያ ሠራዊት መከተ። አንድ ጊዜም ሳያቋርጥ ለ16 ቀን የተካሄደው የጦር ዝግጅት ህዳር 3 ቀን 1929 ዓ.ም ተከፈተ። አይሮፕላኖች ድብደባቸውን ቀጠሉ። ከአዲስ አበባ እየተነሱ ከሚመጡት 17 ጋር ቁጥራቸው ወደ 44 ከፍ ያለ አይሮፕላኖች ድብደባ ቢፈፅሙም የኢትዮጵያ ጦር አልተበገረም። ጠላትም ይህንን ባየ ጊዜ ተጨማሪ ጦር አቀረበ። ኢትዮጵያውያን በስተቀኝ የመጣባቸውን ጦር አበረሩ፤ ነገር ግን በስተግራ የመጣው ጠላት የሚዋጉበትን ቦታ አስለቀቃቸው። ጦርነቱም ስለጠነከረ ጣልያን ምሽግ መሥራት ጀመረ። አይሮፕላኖቹም በአካባቢው የነበሩትን ከተሞች ሙልጭ አድርገው አቃጠሉ።

ኢትዮጵያውያን የጦር ሥልታቸውን ለወጡ። ሲመጣ መከላከል ብቻ ሳይሆን እስከ አለበት ድረስ እየሄዱ አደጋ ይጥሉበት ጀመር። ህዳር 7 ቀን መድፍና ኦርሊከን ይዘው 300 ሆነው ከበስተጀርባው ዞረው ከምሽቱ በ11 ሰዓት አደጋ ጣሉበት። ሠፈሩን አቃጠሉበት። የድንኳኑ ቃጠሎ ሌሊቱን ቀን እስኪያስመስለው ድረስ እሳቱ ተንቀለቀለ። አንድ ጄነራል አንገቱን ተቆርጦ ከብዙ ወታደር ጋር ሞተ። የጦር መጋዘኑ ተቃጠለበት። የኢትዮጵያ አርበኞች አንዳችም ጉዳት አላገኛቸውም።

ህዳር 9 ቀን የኢትዮጵያ አርበኞች ሌላ ጥቃት ለማካሄድ ተንቀሳቀሱ። ሁለት መቶ ወታደሮች፣ ሁለት መድፍ ይዘው ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው ሲነጋጋ ከጠላት ጀርባ ዞረው ቦታ ያዙ። ነገር ግን ተኩስ አልከፈቱም፤ አልተንቀሳቀሱም። አድፍጠው ውለው አይሮፕላኖች ድብደባቸውን ፈፅመው ወደ ሠፈራቸው ሲመለሱ አርበኞች ከቀኑ በአሥር ስዓት ሥራቸውን ቀጠሉ። ቀላል የመድፍና የጥይት ድብደባ አካሄዱበት። የነበሩትን ታንኮችና ካሚዮኖች አቃጠሉበት።

ህዳር 12 ቀን ደግሞ ሌሊቱን ሲጓዙ አድረው ከንጋቱ በ12 ሰዓት ከፊት ለፊት አደጋ ጣሉበት። ይህ ደግሞ ሌላ ፈሊጥ ሆነበት። አደናግረው ብዙ ጉዳት አደረሱበት። ነገር ግን አይሮፕላኖች በ1 ሰዓት ደርሰው ድብደባ ጀመሩ። እየተፈራረቁ እስከ 12 ሰዓት ዋሉባቸው። ሆኖም የኢትዮጵያ ወታደሮች ምቹ ሥፍራ ይዘው ስለነበር ጉዳት አልደረሰባቸውም። ማታውኑ በደህና ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ።

የኢትዮጵያ ጦር አቅሙ እያነሰ፣ ብርካቴውም እየቀነሰ ሄደ:: በእግር፣ በአይሮፕላን ቅጥቀጣው በዛበት:: ከፍ ያሉ ጀግኖች ተራ በተራ ወደቁ:: ብዙ የጦር መሪዎች ቆስለው ከአዛዥነት ወደ ሽክምነት ተዛወሩ:: ወታደሩ ችግር በዛበት:: ጊዜውም ረዘመበት:: ደግሞ ጠላት ከተሞችን በአይሮፕላን ሲያቃጥል፣ አርበኛው ስለ ሚስቱና ስለ ልጆቹ ሁኔታ ማወቅ ግድ ሆነበት:: ስለዚህም ቀስ በቀስ ተበተነ:: ተዋጊው ኃይል ቢቆጠር አንድ መቶ ሃያ አምስት ብቻ ሆኖ ተገኘ:: ከኤርትራዉያኑም የቀሩት ሦስት መቶ ሰባ አምስት ሆኑ:: በጠላት በኩል ግን ሁኔታው ከባድ ነበር:: ከአዲስ አበባ ሠላሳ ሦስት ካሚዮን ወታደርና አርባ ታንክ ገባ::

እነዚህን ሁኔታዎች በመገምገም የኢትዮጵያ ጦር ምክር አደረገ:: አካባቢውን ለቅቆ መሄድና ከሌሎች አርበኞች ጋር ተቀላቅሎ መዋጋት እንደሚሻል ስለታመነበት፣ ጦሩ ተፈሪ ኬላን ህዳር 19 ቀን 1929 ዓ.ም ለቅቆ ወደ ሀገረ ሰላም ተጓዘ:: ጠላትም ይርጋ ዓለም ገባ:: ክፍለ ሀገሩም ከኢትዮጵያ አስተዳደር ወደ ጣልያን ቅኝ ግዛት በዚህች ቀን ገባ::

በዛ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር ከተፈሪ ኬላ ወደ አርባጉና ዞረ:: ከዚያም ጠላቱን እየተከላከለ እስከ ጥር 12 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ ቆየ:: በኢጣልያ ወገን ጄነራል ግራዚያኒ የማርሻልነት ማዕረግ ተሰጥቶት አዲስ አበባ ሲገባ፣ የጦር አዛገፍ ጄነራል ጀሉዞ ሆነ:: እሱም ለራስ ደስታ ዳምጠውና ለደጃዝማች ገብረ ማርያም አንድ ዓይነት ቃል የያዙ ሁለት ደብዳቤዎች ጽፎ ሙሴ ቀስተኛ በተባለ የስዊስ ተወላጅ ነኝ ባይ እጅ ላከ:: በደብዳቤዎቹ ሰላምታ ከአቀረበ በኋላ በትግሬም፣ በሐረርጌም የመጣው ጦር አዲስ አበባ መግባቱን ይገልፅና "...እኔ ብቻ እንዳልገባ ብትከለክሉኝ ምን ጥቅም ታገኛላችሁ?" ካለ በኋላ፣ ምህረት እንደተደረገላቸው አረጋግጦ እጃቸቸውን እንዲሰጡ ይጠይቃል:: ሙሴ ቀስተኛም መልዕክቱን ታህሣስ 7 ቀን አርቤጉና ላይ አስረከበ:: በቃሉም የተላከበትን ጉዳይ አስረዳ:: ግራዚያኒ የፃፈላቸውንም ዛቻ የተመላበት ደብዳቤ አብሮ አስረከበ::

ሁለቱም መሪዎች የሠራዊታቸውን ቁርጠኛ ሐሳብ በማንፀባረቅ ታህሣስ 7 ቀን አንድ ዓይነት ደብዳቤዎች፣ መልስ ሰጡት:: የፃፈላቸው ደብዳቤ እንደደረሳቸው ገልፀው፣ ስለነፃነታቸው እስከ ሕይወታቸው ፍፃሜ መከራከር እንደሚገባቸው ገለፁለት:: ከዚህም አያይዘው ለእሱ ለራሱ ምክር ሰጡት:: "...ኢትዮጵያን ይዤአለሁ ካልክ ይልቅ ሰላማዊው ሕዝብ፣ ድኃው በከንቱ እንዳያልቅ... እንዲጠበቁ ለሹማምንቶችህ ትዕዛዝ ማስተላለፍ ነው..." የሚል ነበር:: እሱ ግን ይህንን ምክር ከቁጥር አላገባውም:: የኢትዮጵያን ሕዝብ መጨረሱን ቀጠለ:: የደብዳቤአቸው ቃል በዚህ ብቻ አላበቃም:: የአርበኛውን ቁርጠኛ ሐሳብ የሚገልፅ ነበር:: "እኛ ግን" በማለት ይቀጥላል፤ "...እኛ ግን ላንተ ማስረከብ የሚገባን የደማችንን ጠብታ ብቻ እንጂ፤ እንኳንስ



እጃችንን አንዲት ሰባራ ጠመንጃም አንሰጥህም" በማለት ይደመድማል:: ጄነራል ጀሉዞም ቁርጡን አውቆ ድብደባውን በአይሮፕላንና በእግር ቀጠለ::

በዚህ ጊዜ በአርበኛው መሃከል ምክር ተደረገ:: መጀመሪያ ከጣልያን የተፃፉት ደብዳቤዎችና ከአርበኞቹ መሪዎች የተሰጠው መልስ ተነበበ:: በምክሩም ላይ ልዩ ልዩ ሐሳቦች ቀረቡ:: አንዱ ሐሳብ ሲዳሞን ሳንለቅ በዚሁ ክፍለ ሀገር እንዋጋ የሚል ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ በአንገት፤ ማለትም:- ጓዝ ቀርቶ፤ በአማሮ በኩል አድርጉ ወደ ኬንያ ጠረፍ መድረስ የሚል ነበር:: ሦስተኛው ሐሳብ በአርሲ በኩል አቋርጦ ጉራጌ አገር ከተደረሰ በኋላ ጓዙን አሩሲ ትቶ የጊቤን ወንዝ ይዞ በጕፋ ድንበር ጠረፍን ተጠግቶ ለመከላከል ነበር:: ነገር ግን የሲዳሞው ጦር በዚህ የማይስማማ ሆነ:: እዚያው ሲዳሞ መዋጋትን መረጠ:: በዚሁ መሠረት በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የአርበኝነቱን ሥራ ለመቀጠል ተወስኖ ሠራዊቱ ቃለ መሐላ ፈፀመ:: ደጃዝማች ገብረ ማርያምም ቀደም ብሎ የተንቀሳቀሰውን ጦራቸውን ወደ አርባ ጉና መለሱ:: ከፊሉ እምቢ ብሎ ወደ እገምጃ ጉዞውን ቀጠለ::

ከታህሣሥ 7 እስከ 29 ቀን 1929 ዓ.ም ድረስ ዝግጅት ከተደረገ በኋላ፣ ከጠላት ወገን ከታህሣሥ 30 ጀምሮ አዲስ እንቅስቃሴ ተጀመረ:: መጀመሪያ የንጉሠ ነገሥቱን ፎቶግራፍና የስብከት ቃል የያዘ ወረቀት በአይሮፕላን ተበተነ:: ቃሉም በአማርኛ የተፃፈ ሆኖ ንጉሡ ጥለው እንደሄዱ፣ ትንሽ እንኳ ሳያስቡ በሰላም ቦታ ተቀምጠው በሕይወትና በተድላ ጠግበው እንደሚኖሩ ከገለፀ በኋላ፤ "...የሚገርመው በውሸት አምናችሁ ልታልቁና ልትገደሉ ያለልክ ሞኞች መሆናችሁ ነው" የሚል ነበር:: ነገር ግን አርበኛው ይህንን ስብከት ከጆሮው አላንጠላጠለውም:: ትግሉን ቀጠለ::

ጥር 1 ቀን ሸንቆበር በተባለው ቦታ ጦርነት ተጀመረ:: ጦርነቱም በየቦታው፣ በየቀኑ ቀጠለ:: እረፍት አልሰጠም:: ከጥር 3 ቀን ጀምሮ አይሮፕላኖች በብዛት እየመጡ አካባቢውን በሙሉ ደበደቡት:: እንደ እሳተ ገሞራ አቃጠሉት:: ከራስ ደስታ ዳምጠው ሳንለይ እንዋጋለን ብለው ምለው የነበሩ፣ አርበኛው ወደሌላ ቦታ ለመዛወር አስቦት የነበረውን ዕቅድ አጨናግፈው ያስቀሩት የሲዳሞ ጦር አባላት፣ ተከበብን በሚል ምክንያት ከደው እጃቸውን ለጠላት ሰጡ:: አንድ ቁምነገር ብቻ ሠሩ:: እሱም እኛ እጃችንን ሰጥተናልና እጃችሁን ስጡ የሚል ወረቀት ጽፈው ላኩ:: የሚገርመው እጄን አልሰጥም በማለት ከበባውን ሰብረው በወጡት በግራዝማች እቁቢት እጅ መላኩ ነበር:: ጠላትም የተማረኩትን ሹማምንት ቀቤና ከተባለው ቦታ ወስዶ በመትረየስ ፈጃቸው:: የፈሩትን ሞት በውርደት ተቀበሉት::

አርበኛው ይዞት የነበረውን ቦታ ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ መዛወርን መረጠ:: ምክንያቱም ተማራኪዎቹ የሚያውቁትን ምስጢር ለጠላት መንገራቸው ሳይታለም የተፈታ ነበር:: ስለዚህም አርበኞች ከአርቤጉና፣ ቀቤና ወደሚባለው ቦታ ሄዱ:: ከዚያም ጉዞ ቀጥለው ለገታ ከተባለው ቦታ ደረሱ::

ከዚህ ቦታ ጠላት በጠቋሚ ደረሰና አስደናቂ ውጊያ ተደረገ። ከጦር ሜዳው በስተምሥራቅ የነበረውን የጠላት ጦር አርበኛው አመድ አድርጐት ከበባውን ጥሶ አለፈ። ገላግሌ የተባለውን መድፍ ነቅሎ አፈሙዙን ብቻ ይዞ ተጓዘ። መከራከሩን ለጌታ ከተባለው ወንዝ አጠገብ ከነበረው ዋሻ ውስጥ ከብዙ ጥይትና ገንዘብ ጋር ደብቆት ሄደ። ነገር ግን ጠላት ከአንድ ከተማረከ ወታደር ምስጢሩን አግኝቶ ወሰደው።

አርበኛው በአርሲ በኩል አልፎ ከሌሎች አርበኞች ጋር ለመቀላቀል በነበረው ሐሳብ መሠረት ጉዞውን ለማፋጠን ሌሊት በመብራት ጭምር ተጓዘ። የሲዳሞን አርበኛ፦ ካሕን መሃይምን፣ ሴት ወንድ ሳይል፣ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ታቦቱን ይዞ ነዋሪው ተከተለ። ጥር 11 ቀን ከሌሊቱ በ11 ሰዓት ጠላት ደረሰበት። ጥምቀት ስለነበረ ሠራዊቱ በዚያ ሰዓት ከፀሎትና ከቅዳሴ ላይ እንደሚሆን አምኖ ነበር። አርበኛው ግን ከበባውን ሰብሮ በመውጣት የሁለተኛውን መድፍ መንኮራኩር ከዋሻ ውስጥ ደብቆ አመለጠ። ለጥር 12 ቀን አጥቢያ ሌሊት ጥሬ ከሚባለው ሲዳሞ፣ ባሌ እና አርሲ ከሚዋሰኑበት ቦታ ደረሰ። ከዚያም ከፍተኛ ውጊያ አደረገ። ጠላት እያየለ፣ አርበኛው አቅሙ እያነሰ፣ ብዛቱም እየቀነሰ ሄደ። ከዶሎ ጀምሮ የደረሰበት ጥቃት አንገፈገፈው። መሪዎቹ አለቁ። እየቆሰሉ ተማረኩ። ስለዚህ የሲዳሞን ክፍለ ሀገር መልቀቅ ግድ ሆነበት። በዚህ ዓይነት ከዘጠኝ ወር የአርበኝነት ትግል በኋላ ጥር 15 ቀን 1929 ዓ.ም ሲዳሞን ለቀቀ። የጣልያን ሥልጣን በክፍለ ሀገሩ ሰፈነ።

ታላቁ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሲዳሞን ከለቀቀም በኋላ የክፍለ ሀገሩ ተጋድሎ አላበቃም። በልጅ /ደጃዝማች/ ተስፋዬ ወልዴ የሚመራው አርበኛ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ በቡርጂ፣ በአማሮ፣ በገለና፣ በሀገረ ማርያም፣ በባርጉዳ፣ በቦረና፣ በተልተሌ፣ በያቤሎ፣ በሰብራ፣ በቡርቃ፣ በገለባና በጭራ የጦር ሜዳዎች በእጅጉ ሲፋለም ቆይቷል።[1]

## ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. "የጀግኖች አደራ"፣ የጀግኖች ማህበር መጽሔት፣ መጋቢት 1983 ገጽ 37-39።



# ምዕራፍ ሃያ

## በሐረር፣ በባሌና በአርሲ የተካሄደ ትግል

ከኦጋዴን የተመለሰው ጦር በየቦታው የተቻለውን ያህል ከተከላከለ በኋላ፣ በምሥራቅ ወገን የነበረው ወደ በርበራ ሲሄድ፣ በምዕራብ ወገን የነበረው ወደ ባሌና አርሲ ገባ። በተለይ በጋራ ሙለታ የነበረው ጦር ከሐምሌ 1 ቀን 1928 እስከ ጥቅምት 30 ቀን 1930 ዓ.ም ያደረገው ተጋድሎ የሚጠቀስ ሲሆን፣ ቀደም ብለው በታተሙ መፃሕፍት ተጠቅሷል።

ወደ ባሌ የዘመተው ጦር የሄደው በአርሲ በኩል ነበር። አዝማቹም ደጃዝማች በየነ መርዕድ ነበሩ። ከእቴጌ መነን የማይወለዱት ልዕልት ሮማን ወርቅ ኃይለሥላሴ፤ ከባላቸው ከደጃዝማች በየነ ጋር አብረው ዘምተው ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱ ቤተሰብ በጦር ግንባር ቆመው የተማረኩና ታሥረው የሞቱ እሳቸው ብቻ መሆናቸው ነው። በባሌ የዘመተው የኢትዮጵያ ጦር በኦጋዴንና በቦረና ግንባር በኩል የመጣውን የጠላት ጦር ከሁለት ፈልቅቆ በመሀሉ በመቆም የሚቻለውን ያህል ተከላከለ። በተሸነፈም ጊዜ በኦጋዴን ምዕራባዊ ግዛት የተመለሰውን የኢትዮጵያ ጦር ጨምሮ በአርሲ በኩል ወደ መሀል ሀገር ገባ።

ከሲዳሞ ጦር ውስጥ ሶርፌታ /ዶዶላ እረና/ ከሚባለው አካባቢ የመጣው የሕዝብ ሠራዊት ጥር 5 ቀን 1929 ዓ.ም አርሲ ሲገባ ከባሌ ጦር ጋር ተቀላቅሎ ዳበረ። የዚህ ጦር ሐሳብ አዲስ አበባ ገብቶ የልቡን ሠርቶ ሕይወቱን ማሳለፍ እንዲሆን በምክር ተመርጦም ነበር። ነገር ግን እንደታሰበው አልተፈፀመም። ጠላት ከአዲስ አበባ በስተደቡብ ያለውን ጉራ አጠናከረ። ከዚያም አልፎ በናዝሬት በኩል አልፎ አርሲ ገባ። ቤቱን እያቃጠለና ከብቱን እየዘረፈ በደራ፣ በጡሩታ በኩል ስለመጣ፣ በዚያ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር እየተከላከለ ወደ ሶዶና እገምጃ አመራ። ጥቂቱ ደግሞ ወደ ሸንኮራና ቡልጋ ተሻገረ። አዲስ አበባ ለመግባት የነበረው ሐሳብ በዚሁ ተቋርጦ ቀረ። በዚሁ ላይ ደግሞ ከአርበኞች ጋር በነበሩ የኤርትራ ልጆች መካከል የሐሳብ ልዩነት ተፈጠረ። እነሱን የኢትዮጵያ ጦር መገላገል አቃተው። በራሳቸው ውሣኔ መሠረት ተለዩ።

ጦሩ ከዶዶላ ወደ ሂበኖ ቀጠለ። ከዚህ ቦታ ላይ ሲደርስ የኢጣልያን አይሮፕላኖች ስለአገኙት ጥር 19 ቀን 1929 ዓ.ም ከጥዋት እስከ ማታ ታላቅ ድብደባ አካሄዱበት። ከዚያም በማግስቱ የጠላት ጦር የእግረኛ ሠራዊት አቀረበ። ከሲዳሞ በአርሲ ጉና፣ ከአርሲ ደግሞ በኮፈሌ በኩል ከበበ። ኢጣልያ የዐረብና የጥቁር እንደዚሁም ከሀገር ውስጥ የተመለመለ የባንዳ ሠራዊት በብዛት አሰለፈ። የኢትዮጵያም ጦር ገድሎ ለመሞት ተዘጋጅቶ ነበርና በብርታት ተዋጋ። የጨበጣ ውጊያ ስለሆነ የጠላት አይሮፕላኖች ወገኖቻቸውን ሊረዱ አልቻሉም። ጦርነቱ ከጥዋቱ ረፋድ ጀምሮ ሙሉ ቀን ዋለ።

ውጥንቅጡ ወጣ። ጨለማ ገላገለው። ፊታውራሪ ሽመልስ ሃብቴና ብዙ ጀግኖች ወደቁ።



ከደቡቡ ግንባር የአሩሲና የባሌው ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበት ነበር።

ከበባውን ሰብሮ ማለፍ ግዴታ ስለነበር፣ አርበኞች ሌሊቱን ተጉዘው ጥር 21 ቀን ለቂደንበል ደረሱ። በንጋት ለመጓዝ እንዲቻል፣ ሆኖም ግን መድፉ በጠላት እንዳይማረክ በሰዋራ ሥፍራ እስቀምጠውት ሄዱ። ጉዞው በአዳሚቱሉ በኩል ቀጠለ። ጠላትም በአይሮፕላን እየተከታተለ በየቀኑ ድብደባ አካሄደ። የአርሲን ኅብረተሰብ በጀሌነት እያሰለፈ አዋጋው። ጉዞው በዚህ ዓይነት ቀጥሎ የካቲት 9 ቀን 1929 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። የሞተው ሙቶ፣ የተረፈው አርበኛ ጉዞውን ቀጥሎ፣ የካቲት 10 ቀን ከሞጆ ወደ ሻሸመኔ ከሚወስደው መንገድ ላይ ደረሰ። በዛም አድፍጦ ይጠብቅ የነበረውን የጠላት ጦር ደፍጥጦ መንገዱን ለማለፍ ቻለ። የካቲት 11 ቀን መቂ ከተባለው ቦታ እንደደረሱ ጠላት ተከታትሎ ደረሰና ውጊያ ተካሄደ። ሰማንያ ያህል ጣልያኖች ሞቱ። የኢትዮጵያም ጦር በዱግዳ በኩል አድርጐ የካቲት 13 ቀን 1929 ዓ.ም ማረቆ ለመግባት ወደ ጉራጌ አገር ተሻገረ። በዚህ ግንባር የነበረው ትግል በእንዲህ ተፈፀመ።

## ማጣቀሻ ፅሑፎች


1. ሰይፉ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገፅ 125-171።




# ምዕራፍ ሃያ አንድ
# በጉራጌ አገር የተካሄደ አርበኝነት

ከኦጋዴንና ከቦረና የጦር ግንባር የተመለሰው ሠራዊት በሐረርጌ፣ በባሌ፣ በሲዳሞና በአርሲ እንደምንም ሲከላከል እንደቆየና ከዚያም ወደ ጉራጌ አገር እንደተሻገረ ተመልክተናል። አሁን ደግሞ በጉራጌ አገር የተካሄደውን ተጋድሎ እናያለን።

ጦሩ ሌሊቱን ተጉዞ ከመቂ ማርቆስ፣ ጉጉቲ ጥዋት ሲነጋ ደረሰ። ከዚያ ደግሞ በከህዲያን ምክር እየተመራ አዲስ የጠላት ጦር ጠበቀው። የኢትዮጵያ ጦር አዛዦች አስቸኳይ የሐሳብ ልውውጥ አደረጉ። አብዛኞቹ የጦር መሪዎቹ ለሞት ቁርጠኞች ስለነበሩ ከውሣኔ ለመድረስ አልተቸገሩም። በተለይ ደጃዝማች ገብረ ማርያም ለውድ ሀገራቸው ለኢትዮጵያ በዚያች ቀን የሞት ጽዋ ለመቀበል ቁርጠኛ መሆናቸውን በሠራዊታቸው ፊት ገለፁ። ከዚህ ፅዋ ለመሳተፍ ያልተዘጋጁ እንዲሄዱ አሰናበቱ። የጠላትን ጦር ብዛትና የእርሳቸውን ሠራዊት መመናመን ተመልክተው "... በቂ ሰው አላገኘንም። ስለሰው አምላኬን ጨምሬአለሁ..." በሚል ቃል የነበሩአቸውን ጥቂት ሰዎች ቦታ አስያዙ። ወጣቱ የጦር መኰንን ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ በዚህ ሐሳብ አልተስማሙም። "...ጠላታችንን የምናጠቃው በመሥራት እንጂ፣ በመሞት ብቻ አይደለምና ለሞት ሳንቸኩል መንገዳችንን ብንቀጥል መልካም ነው..." አሉ። ተቀባይ አላገኙም። ደጃዝማች ለማምለጥ ሲቻላቸው ተዋግቶ መሞትን መረጡ።

የመጣው የጠላት ጦር ከወገን ጦር እጅግ ብዙ ብልጫ ነበረው። ራስ ደስታ ዳምጠው፣ ደጃዝማች ገብረ ማርያም፣ ደጃዝማች መርዕድ በየነና ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ ጥቂት ወታደሮቻቸውን ይዘው የካቲት 13 ቀን ጉጉቲ ከተባለው ቦታ ግንባር ለግንባር ገጠሙት። እያንዳንዳቸው መትረየስ ይዘው ተዋጉ፤ የጠላት ወታደርንም ረፈረፉት። ግን ከብዛቱ የተነሣ መክተው ለመመለስ አልቻሉም። ጦርነቱ ረፋዱ ላይ ተጀምሮ ሙሉ ቀን ቀጠለ።

ውጊያው ከመጠን በላይ ብርቱ ከመሆኑ የተነሣ በትንቅንቁ ሂደት አርበኞቹ ርስ በርሳቸው ተለያዩ። ሁሉም በየፊናው ሄደ። ከደጃዝማች ገብረ ማርያም ጋር በውሣኔአቸው እንደፀኑ የቆሙት በዚህ ታላቅ የጦር ሜዳ ከብዙ ኢትዮጵያውያን ጋር የጀግንነት ሞት ሞቱ። ደጃዝማች በየነ



ከደቡቡ ግንባር የአሩሲና የባሌው ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለበት ነበር።

መርዕድ መቂ ላይ በተደረገው ጦርነት በኃይል ቢቆስሉም፣ በዚህ ቀን በዋለው ጦርነት ከሜዳ ገብተው የጠላትን ወታደር ሲጠርጉት ዋሉ። ነገር ግን ከቁስላቸው ፅናት የተነሣ ማምለጥ ስለአልቻሉ ከጠላት እጅ ወደቁ። እሱም ቀሎ ከሚባል ቦታ ላይ በመትረየስ ደብድቦ ገደላቸው።

ከራስ ደስታ ዳምጠው ጋር በመሆን ከዚህ ጦርነት የተረፉት ከአሥር ያልበለጡ ወታደሮች ብቻ ነበሩ። ከዚያም ልዕልት ሮማን ወርቅ ኃይለ ሥላሴን ለፊታውራሪ ታደሰ ገነሜ በአደራ ሰጥተው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ልዕልት ሮማን ወርቅ ለፊታውራሪ ታደሰ የተሰጡት ሊያድኑአቸው እንደሚችሉ ተገምቶ ነበር። ነገር ግን ፊታውራሪ ታደሰ ራሳቸው በገበሬ እጅ ስለተገደሉ፣ ልዕልት ተማረኩ። ከዚያም አዳሜ ቱሉ የተባለው ወረዳ ኃላፊ የነበረው ሰውዬ ከገበሬው ተቀብሎ ለአለቆቹ አስተላለፋቸው። ከዚያም ወደ ጣልያን ሀገር ተወስደው በአሥር ላይ እንዳሉ ሞቱ። እዚህ ላይ ከጦርነቱ ጥቂት ቀደም ብሎም ልዕልት ዘነበ ወርቅ ኃይለሥላሴ፣ ደጃዝማች ኃይለሥላሴ ጉግሣን አግብተው መቀሌ ሲኖሩ ሞተው እንደነበር ይታወቃል። ምንም እንኳን የእኚህኛዋ አሟሟት በሕመም ቢሆንም፤ እነዚህ ሁለት ልዕልቶች በአገር ውስጥ ቆይተው እንደ ማንኛውም ነዋሪ ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ እንደሰጡ ሊታወቅላቸው ይገባል።

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስ፣ ራስ ደስታ ዳምጠው የካቲት 15 ቀን በጉዞና በጦርነት ላይ ውለው ለየካቲት 16 ቀን አጥቢያ ሙሽር ከተባለው ቦታ ደረሱ። ከሀገሩ ሰዎች ጋር በተደረገው ንግግር ወደ ግቤ በረሃ መግባት የተሻለ ሆኖ ተገኘ። መንገዱን የሚያውቁ ሁለት ሰዎች ተሰጥተዋቸው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። መንገድ ለመሩአቸው ሰባ፣ ሰባ ብር የተከፈላቸው ቢሆንም፣ የተቀጠሩት ባላገሮች ራሳቸው መሐላቸውን አፍርሰው ጠቋሚ በመሆን ለጠላት ነገሩባቸው።


የጠላት ጦርም አገሬውን ጨምሮ በብዛት ሆኖ ቢመጣባቸውም በድፍረት ገጠሙት። ጠላት ሌሊቱን ከአደረገባቸው ከበባ ሰብሮ ለመውጣት ባደረጉት ሙከራ ከተረፉት አሥር ያህል ሰዎች አራቱ ሞቱ፤ ሁለቱ ቆሰሉ። በዚህ ሁኔታ ራስ ደስታ ዳምጠው ብቻቸውን ቀሩ። ከሞቱትና ከቆሰሉት ወታደሮቻቸው መካከል ሆነው፣ የጦር ልብሳቸውን ለብሰው፣ በቤልጅግ መትረየስ የጠላትን ወታደር እንደረፈረፉት ነጋ። በመሀሉም ጥይት ስለአለቀባቸው ተናደው መትረየሳቸውን ወረወሩት። ከዚያም በአገኙት መሣሪያ ሁሉ ተዋጉ። ያገኙአቸው መሣሪያዎችና የሸጉጣቸው ጥይት አንድ እንኳን ሳይቀር ስለአለቀባቸው እጃቸውን



እኪሳቸው ውስጥ ከትተው በወታደሮቻቸው ሬሣ መካከል ይንጐራደዱ ጀመር። ከጥዋቱ በ12 ሰዓት በጣልያኖች እጅ ተያዙ።

እንደተያዙም የሞቱት ወታደሮቻቸው እንዲቀበሩ፣ የቆሰሉትም ተነስተው ሕክምና እንዲደረግላቸው ጠየቁ። በዚሁ ዓይነት ተፈፀመላቸው። ጠላት በበቅሎ አስቀምጦ ከሙሽር እስከ ቡታጅራ ከተማ አመጣቸው። ከዚያም የኢጣልያ መኮንኖች የክብር ሰላምታ ሰጥተው ከድንኳን ውስጥ አስቀመጡአቸው።

ራስ ደስታ መያዛቸውን የሚገልፅ ቴሌግራም ወደ አዲስ አበባ ተላለፈ። በዚያን ሰዓት ለጉዳዩ ውሣኔ የመሥጠቱ ሥልጣን የዋና ጠላታቸው የግራዚያኒ ነበር። እሱም በቶሎ እንዲገደሉ ትዕዛዝ ሰጠ። ውሣኔውን መፈፀም የነበረበት ሻለቃ ቱቺ የተባለው ኢጣልያዊ ለራስ ደስታ መናፈሻ ሊያሳያቸው ማሰቡን ገለፀላቸው። እሳቸው ግን ሞታቸውን አውቀው ነበርና በጣም ደስ እንደሚላቸው ገለፁለት። ሲፈልጉት የነበረው የድል አክሊልን መቀዳጀት እንደነበረ፣ ስለሀገራቸው ክብር የሚገባቸውን እንደፈፀሙ፣ በጦር አዛዥነታቸው ሙሉ በሙሉ እንደሠሩበት፣ በእሳቸው እዝ የተንቀሳቀሰው የኢትዮጵያ ጦር በእያንዳንዱ ጉራ የፈፀመው ድል እንደ አስደነቃቸው ገለፁ። ንግግራቸውንም "...ያንዲት ደሜ የመጨረሻ ጠብታ...ነፃነትን እንደሚያፈራ አልጠራጠርም" በማለት ደመደሙ። ጠላትም የካቲት 17 ቀን 1929 ዓ.ም ከቀኑ በ7 ሰዓት በዘጠኝ ጥይት ደብድቦ ገደላቸው።



ራስ ደስታ ዳምጠው እጃቸውን በሰጡበት ወቅት።



ራስ ደስታ ዳምጠው እጃቸውን በሰጡበት ወቅት።

በአካባቢው የነበሩ የሦስት ደብር ካህናት በመስቃን መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ፀሎተ ፍትሐት ከአደረሱላቸው በኂላ፤ አስከሬናቸው ወደ ምድረ ከብድ ተጉዞ በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም የካቲት 18 ቀን 1929 ዓ.ም በክብር ተቀበረ።[1]

እዚህ ላይ በቦረና ጦር ግንባር የተሰለፈውን የኢትዮጵያ ጦር የመሩ፣ በዚያ ግንባር የተሰለፉ ወታደሮች ሁሉ ምስጋና እንደ ሚገባቸው የዚህ መፅሐፍ አዘጋጅ ዕምነት ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ጥቂት ከህድያንና ትንሽ ወላዋዮች ቢኖሩባቸውም፣ አብዛኞቹ የጀግንነትን ሥራ ሠርተዋል። ሸሽተው ማምለጥ ሲችሉ በየነበሩበት ቆመው ጠላትን ግንባር ለግንባር በመጋፈጥ ለሀገራቸው የመጨረሻ ጠብታ ደማቸውን አፍስሰዋል። ጀግናው የኢትዮጵያ ባሕርይ ይህ መሆኑን በግብር አረጋግጠዋል።

ግራዚያኒና ሌሎችም የኢጣልያ ሹማምንት፣ እንዲሁም የጦር መኰንኖች፣ የደቡብ ትግል በእነዚህ የጦር አለቆች የሚፈታ መስሏቸው ነበር። ነገር ግን እንደ አሰቡት አልሆነም። ምክንያቱም ሰው እንጂ የሀገርና የነፃነት ፍቅር አይሞትም። አንዱ ሲሞት ሌላው ይተካልና። የጉራጌ አገር ትግል ከእነራስ ደስታ፣ ደጃዝማች ገብረ ማርያምና ደጃዝማች በየነ አስከሬን ጋር አልተቀበረም። ሌሎች ጀግኖች ተነሱ። በግልፅ እንደታየው ትግሉ ይበልጡኑ ተቀጣጠለ።

ለአርበኞች፣ ከየካቲት 19 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ያለው ጊዜ አስቀድሞ የነፍስ ማዳኛ፣ ከዚያም የመልሶ ማጥቂያ ሆነ። በአካባቢው ያለው የጉራጌና የአማራ ኅብረተሰብ ጠላቱን ለመቋቋም ተደራጀ። ይህንን የውስጥ እንቅስቃሴ ጠላት ተረዳ። አፍራሽ እርምጃ ለመወሰድ የሚረዳውን የልምምጥና የማስፈራራት ሥራውን በጣምራ ቀጠለ። ለዚህ ጉዳይ መሣሪያ ያደረገው ሙሴ ቀስተኛን ነበር።

እዚህ ላይ ስለ ሙሴ ቀስተኛ ማንነት አንዳንድ ነጥቦችን እንመልከት። ሙሴ ቀስተኛ ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ በመግባት የአማርኛን ቋንቋ ያጠናና በየመኳንንቱ ቤት እየዞረ ወሬ የሚለቅም፤ የስዊስ ተወላጅ ነኝ ይበል እንጂ በ1888 ዓ.ም በአድዋ ጦርነት ጊዜ የኢጣልያ ወታደር ሆኖ መጥቶ ከተማረከ በኂላ ሳይመለስ እዚሁ የኖረ ሰው ነበር። ከንጉሠ ነገሥቱም መጠነኛ ቅርበት ነበረው። የኢጣልያ ወረራ ሲንቀሳቀስ፣ የእነሱ ሰላይ ሆነ። አዲስ አበባ ሲገቡ ደግሞ፣ በአስታራቂነት ስም የአርበኝነት እንቅስቃሴ በሚታይባቸው ቦታዎች እየዞረ ነገር ማካሄድ አመጣ። ዋና ዋና ሥራዎቹ ሦስት ነበሩ። ከእነዚህም



አንደኛው የአርበኛውን ልብ በስብከት መከፋፈል፣ ሁለተኛው ደግሞ አንዳንዱን ልበ ፍንቅል ወደ ጠላት እንዲገባና ለእነሱ መሣሪያ እንዲሆን ማድረግ ሲሆን፣ ሦስተኛው ደግሞ የአርበኞችን ሁኔታ እያጠና እነሱን ማጥፋት የሚቻልበትን መንገድ ለጣልያን ምክር መስጠት ነበር። ይህ ሰው ወደ ቡልጋም ሄዶ ነበር። በዚያ ያደረገውን ከቦታው እገልፃለሁ። ቀደም ብሎ ከእነ ራስ ደስታ ጋር አድርጎት የነበረውን በመቀጠል፣ ወደ ጉራጌ አገር ሄደ። በዛ ግን ባላምባራስ /ደጃዝማች/ ገረሱ ዱኪ የሚመሩት የመራና የአመያ አርበኞች በስቅላት ስለቀጡት ጥበቡ ከሸፈ።

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስ፣ አርበኛው ጠላቱን በየቦታው ግንባር ለግንባር እየገጠመ ያርበደብደው ቀጠለ። በየካቲት ወር 1930 ዓ.ም ጠላት አዲስ ጦር ላከ። በሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ የሚመራው አርበኛ በሶዶ እና በሜጫ ወሰን ላይ ገጥሞ ጥሩ ሥራ ሠራ። ብዙ ጀግኖች ቢሞቱና ሻለቃ በቀለም ጭምር ቢቆስሉም፣ በጦርነቱ በተገኘው ድል የአርበኛው ወኔ በረታ። ጠላት አከታትሎ ሌላ ጦር ላከ። በአይሮፕላን አካባቢውን ደበደበ። ነገር ግን አርበኞቹ እገምጃ ከተባለው ስፍራ ቦታ ይዘው ጠበቁት። በቀረበም ጊዜ ጥሩ አድርገው ወጉት። አይሮፕላኖቹ አርበኛውን መጉዳት አልቻሉም። ጦርነቱ እስከ ተከፈተበት ጊዜ ድረስ ጠላት የነበሩበትን አላወቀም ነበር። ጦርነቱ ሲከፈት ደግሞ አርበኛው ፈጥኖ ከጠላት ጋር በመቀላቀል የጨበጣ ውጊያ ስለያዘ፣ ለይቶ መምታት አልቻለም። ከጥዋቱ 12 ሰዓት የተከፈተው ጦርነት እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ቀጥሎ፣ ጠላት በፍፁም ድል ሆነ። አርበኛው እየተከታተለ ጠላቱን ረፈረፈው። ብዙ የጠላት መኰንኖች በጦር ሜዳው ወድቀው ተገኙ። ብዙ መትረየስ፣ ጠመንጃና ጥይት፣ የመድፍ መጫኛ በቅሎዎች ጭምር ተማረኩ። ታላቅ ደስታ ሆነ። በመሆኑም ብዙ ጀግኖች መሐላቸውን አፀኑ።

በሙሴ ቀስተኛ ላይ የጠቀስኩት ቅጣት በመወሰዱ የተናደደው ጠላት፣ 44 ባታሊዮን ጦር ከጂማ፣ ከሲዳሞ፣ ከሐረርጌ፣ ከአርሲና ከሸዋ በማቅረብ ከበባ አደረገ። አርበኛውም ይህንን የቀረበለትን የጦርነት ማዕድ ለመቋደስ ተዘጋጀ። ወለኒ ዋቤ፣ አምቦ ጉዳ ከሚባለው ተራራ ላይ ግንባር ለግንባር ገጠመው። ጦርነቱ ያለዕረፍት ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ቀጠለ። አርበኞች በሚያስደንቅ ብርታትና ቆራጥነት ተዋጉ። የጠላትን ወታደር ጨፈጨፉት፤ ብዙ የጠላት ሹማምንት በጦር ሜዳው ላይ ወደቁ። ነገር ግን የጠላት ጦር ከብዛቱ የተነሳ የማይበገር ሆነ። በርካታ የአርበኛው መሪዎች ከሠራዊታቸው ጋር ወደቁ። ጦርነቱ እየከበደ ስለሄደ፣ በአንድ ወገን ያለው ከባቢ የጠላት ጦር ላይ በድንገት አደጋ በመጣል የጨበጣ ውጊያ በማካሔድ ጥሰውት ወጡ።

ጠላት በጦር ሜዳ ሲሸነፍ "...በሰላም ብረታችሁን አስረክቡ..." የሚል ደብዳቤ ፃፈ። አርበኛውም ብረት አግቡ በማለት የፃፈው ቃል ድፍረት መሆኑን በመግለፅ መልስ ሰጠው። ትግሉ ቀጠለ። መጋቢት 19 ቀን 1930 ዓ.ም ሌላ አዲስ የጠላት ጦር መጣ። ብዛቱም አያሌ ነበር። አርበኛውም በጠራ ሜዳ ላይ ገጥሞ በቆራጥነት ተዋጋ። ነገር ግን ጠላት ስለአየለ ጦርነቱን መቀጠል ወገንን ማስጨረስ ሆነ። ስለዚህ አርበኛው አካባቢውን ለቅቆ ወደ አዳሜ ቱሉ ሄደ። ከዚያም ወደ ቡልጋ ዞረ።

ወደ ቡልጋ ሄደው በዚያ ከነበሩ አርበኞች ጋር ከተመካከሩና የልምድ ልውውጠ ከአደረጉ በኂላ፣ የጉራጌ አገር አርበኞች ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ተመልሰው ሥራቸውን ቀጠሉ። ቶሌ በረሌ ላይ ያጋጠማቸውን ጦርነት ከመቅጽበት ድል አድርገው አባረሩት። ብዙ የጠላት ወታደሮችና መኰንኖች በጦር ሜዳው ላይ ወደቁ። ጠላት ኃይሉን እንደገና አጠናክሮ ማጥቃት ቀጠለ። አርበኞችም እጨበር ቆሽት ላይ ቦታ ይዘው በመጠበቅ ገጠሙት። ከባድ ጉዳትም አደረሱበት። ለስምንት ሰዓት በተካሄደው ጦርነት ከጠላት ወገን ብዙ መቶ አለቆችና ሻምበሎች በጦር ሜዳው ወድቀው ተገኙ። ምርኮው ቁጥር አልነበረውም። እርግጥ ከአርበኞችም ወገን ብዙዎች ወድቀዋል።

የ1930 ዓ.ምቱ ትግል በዚህ ዓይነት ተጠናቅቆ የ1931 ዓ.ምቱ ቀጠለ። መስከረም 10 ቀን ባንቱ በተባለው ቦታ በተደረገው ጦርነት ጥሩ ሥራ ተሠራ። ጠላት ከምሽጉ ወጥቶ በጠራ ሜዳ ላይ ስለተጋጠመ፣ በዛ ለነበሩት አርበኞች ተመቻቸው። ለሰባት ሰዓት በተካሄደው ውጊያ ጠላት ተጠርንፎ ወደ ምሽጉ ገባ። አርበኞች ብዙ ግዳይና ምርኮ አገኙ።

የ1931 ዓ.ም ዘመን ለጠላት የሚዛን መጠበቂያ ሲወጣው፣ የአርበኞቹ ኃይል ደግሞ የማይበርድ መሆኑ ታወቀ። በዚህ ላይ የአይሮፕላን ድብደባው የተጠበቀውን ውጤት ማስገኘቱ እየቀነሰ ሄደ። ይህም ሆኖ ጠላት ገና ተስፋ አልቆረጠም ነበርና ማጥቃቱን አልተወም። አርበኞችም ጫካ ደፋሩ በተባለው ቦታ ገጠሙት። ጥሩ ውጊያ ተካሂዶ አርበኞች ድል አገኙ።

ጠላት በዚህ የማጥቃት ሙከራውን አላበቃም። ሚያዝያ 19 ቀን አዋሽ ላይ 5 ሰዓት ሙሉ የፈጀ ጦርነት አካሄደ። ወዲያው ደግሞ ሚያዝያ 23 ቀን ዝቋላ ላይ ሌላ ውጊያ ተካሄደ። እንደዚሁም ሰኔ 13 ረጺ በተባለው ሥፍራ ተደገመ። በተከታታይ ጅሮ በሚባለው ቦታ ውጊያ ተካሄደ። ቀጥሎም ሐምሌ 15 ቀን ጌቶ እሾ ከተባለው ሥፍራ በሁሉም ቦታ ቀኙ ለአርበኞች ሆነ። በጠላት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እየበዛ፣ በአርበኞች ላይ የሚደርሰው እየተቀነሰ ሄደ። የጣልያን የጦር መኰንኖች



በየሜዳው ይረፈረፉ ጀመር። የሚማረከውም መሣሪያ ብዛት ከአርበኞቹ ሽክም በላይ ሆነ። ለምሣሌም ያህል በጌቶ እሾ ጦርነት ብቻ 800 ጠመንጃ ከብዙ ጥይት ጋር ተማረከ።

በዚህ መልኩ የድል ወጋገን እየቀደደ ሲመጣ የንጉሠ ነገሥቱ የጦር እንቅስቃሴ ደግሞ እየተሰማ መጣ። ይህም በጠላት ላይ ድንጋጤን፣ በአርበኞች በኩል ብርታትን ፈጠረ። በ1933 ዓ.ም መባቻ አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ። ጥቅምት 11 ቀን 1933 ዓ.ም ዝቋላ፣ ወንበራ በተባለው ቦታ ጦርነት ተደርጐ ጥሩ ተግባር ተሠራ። በዚሁ ቀን አቡ ከሚባለው ቀበሌም እንደዚሁ መልካም ተግባር ተሠራ። በሌላ አገላለፅ፣ በልጅ የጨዋታ ፈሊጥ ሥሉስ ዞረ እንደሚባለው ሆነ።

ጥቅምት 13 ቀን 1933 ዓ.ም ሌመን ከሴ በተባለው ቦታ በድንገት ተኩስ ተከፈተ። የበለጠው ምቹ ቦታ በአርበኞች እጅ ስለነበር ቀናቸው። የጣልያን ጦር ደግሞ እንኳን ቆሞ መዋጋት፣ ሸሽቶ ማምለጥ አቃተው። ዋናው የጦር አዛዥ የነበረው ኰሎኔል ከሳበሳ፣ ከብዙ የጣልያን መኰንኖች ጋር በጦርነቱ ላይ ወደቀ። አንድ ነጭ መኰንን ተማረከ። አሥራ ሦስት ካሚዮኖች በአርበኞች እጅ ተቃጠሉ። የከሳበሳ ሻንጣ ሲከፈት ታላቁ ባለአንበሳ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተገኘ። ሠራዊቱም በአንድነት ቆሞ፣ የኅሊና ፀሎት አድርሶ፣ ከፍ አድርጐ አውለበለበው። ብዙዎቹም ከደስታ ብዛት አለቀሱ።

ጠላት የሞት ሞቱን ማጥቃት ቀጠለ። ሙጤቻ በተባለ ቦታ በተደረገው ጦርነት ሦስት መትረየስ ከብዙ ጠመንጃና ጥይት ጋር በአርበኞች ተማረከ። ጣልያን ከጂማ፣ ከሲዳሞ፣ ከአርሲ፣ ከናዝሬት ከሞጆ፣ ከቢሾፍቱ፣ ከወሊሶ፣ ከአዲስ አበባ ጭምር አዲስ ጦር አመጣ። አርበኞችም በድፍረት ገጠሙት። ጥር 7 ቀን 1933 ዓ.ም ከንጋት እስከ ምሽት በተካሄደው ጦርነት ብዙ የጠላት ወታደሮች ወደቁ። ከአርበኞችም ጥቂት ሞቱ፣ ሌሎች ጥቂት ቆሰሉ። በተከታታይ መቂ እና በዲቂሮ ላይ በተደረጉ ጦርነቶችም አርበኞች ቀናቸው።[2]


## ማጣቀሻ ፅሑፎች

[1] ሰይፉ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ገጽ 171-191።

[2] ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 191-200።

## ምዕራፍ ሃያ ሁለት
## በጋሞ ጎፋ የተካሄደው ትግል

መጀመሪያ ላይ የጋሞ ጎፋ ጦር የዘመተው ወደ ኦጋዴን ነበር። የተጓዘውም በወላይታ፣ በአላባ ቁሊቶ፣ በሻሸመኔ አድርጐ ባሌ በመግባት ነበር። የባሌ ጦር ከምዕራብ ሐረርጌ፣ ከአርሲና ከሲዳሞ ጦር ጋር ተቀላቅሎ ምን እንደሠራ ቀደም አድርገን አይተናል። ከእልቂት የተረፈው ጦር በወላይታ አድርጐ ወደ ቡልቂ ተመለሰ። የጠላት ጦር የሲዳሞን ክፍለ ሀገር እጅ ከአደረገ በኋላ፣ ይህንን ሠራዊት ተከታተለው። የመጀመሪያው ጦርነት ቡልቂ ላይ ነበር። ምንም እንኳ የኢትዮጵያ ሠራዊት ከክክምትና ከድካም ገና ያላገገመ ቢሆንም፣ በርትቶ ተዋጋ። ነገር ግን ጠላት የአንዱ ጦር ሲደክምበት ሌላ አዲስ እያቀረበ ማጥቃቱን ስለቀጠለ፣ የኢትዮጵያ ሠራዊት ያንን አካባቢ ለቅቆ ወደ ደቡብ ተጓዘ።

ጠላት እንደልማዱ እግር በእግር ተከታተለው። ሌላው ጦርነት ደግሞ ባኮ ጋዘር ሆነ። ከዚያም ኢትዮጵያውያን የጀግንነት ተግባር ሠሩ። ጠላት አንዱን ቡድን ሲያባርር፣ ሌላ ቡድን ከኋላው እየደረሰ ብዙ አጠቁት። የኢትዮጵያ ሠራዊት በዚህ ዓይነት እየተከላከለ፣ የሞተው እየሞተ፣ የተረፈው ኬንያ ጠረፍ ደረሰ።

የሲዳሞ ጦር ወደ ባሌ ለመሻገር ቆሽ ከተባለው አካባቢ ሲቃረብ፣ ከጠላት ከድተው ከኢትዮጵያውያን ጐን ቆመው ከነበሩት ሐማሴኖች መካከል አንዱ ቡድን ከራስ ደስታ ጋር ሲቀጥል፣ ሌላው ቡድን ከኢትዮጵያ ጦር ተለይቶ ወደ ኋላው ተመልሶ እንደነበር ባለፈው ተመልክተናል።

ወደ ኋላው የተመለሰው ቡድን በጉዞ ላይ ሳለ አባላቱ እርስበርሳቸው ሳይስማሙ ቀሩና እንደገና ከሁለት ተከፈሉ። አንደኛው፣ በቀኛዝማች ሰለባ ይመራ የነበረው ቡድን፣ አንድ መቶ አባላት ነበሩበት። ቡድኑ ጐፋ ውስጥ ከገባ በኋላ የጠላት ጦር ስለአጋጠመው 15 ቀን የወሰደ ውጊያ አካሂዶ ግዳጁን ተወጣ። አባላቱ በሙሉ በጦር ሜዳ የክብር ሞት ሞቱ። ምክንያቱም ቢማረኩ የሚጠብቃቸው አበሳ ከባድ ነበር። በቀኛዝማች ገብሬይ የሚመራው ሌላኛው ቡድን ግን ምንም ያህል ችግር ሳያጋጥመው ኬንያ ለመግባት ቻለ።[1] በሌላ ወገን ከራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ጦር፣ ከጊቤ በክብር ተሰናብተው የመጡት ኤርትራውያን ከደጃዝማች ወልደ ማርያም ጦር ጋር ተቀላቀሉ። ከዚያም ከኢትዮጵያውያን ጋር ሆነው ጠላትን በመከላከል ኬንያ ገቡ።

እዚህ ላይ ከጠላት ከድተው ሱዳን የገቡ ሦስት የኢጣልያ ወታደሮች ለእንግሊዞች በሰጡት ቃል "...በበከና በኩልም ካሉ



ኢትዮጵያውያን ጋር ተዋጋን።... በባኮ እስከ ቆላ ዘጠኝ ጊዜ ተዋጋን። ሁልቀን ከእኛ አይሞትብንም፣ ከኢጣልያ በኩል ግን እንገድላለን። በከፋም ተዋግተን አንድ ነጭና ብዙ ወታደሮች ገድለናል..." ማለታቸውን መጥቀስ ተገቢ ይሆናል።[2]

ወደ ኬንያ የሄደው ሠራዊት ከኢትዮጵያ ከወጣ በኋላ የቀረው ጦር በጋርዱላ አውራጃ፣ ጉማይዴ ላይ ተዋግቶ ጥሩ ውጤት አገኘ። በዚያም ቡድን የሃያ አንድ ዓመቱን ወጣት ልጅ /ደጃዝማች/ ተስፋዬ ወልዴን መሪ አድርጐ መረጠ። በጋሞ ጐፋና በደቡብ ቦረና እየተዘዋወረ ጠላት በየሠፈረበት ቦታ አደጋ በመጣል ተደጋጋሚ ጉዳት አደረሰበት። በጋርዱላ አውራጃ በጉማይዴ፣ በኃይሎታ፣ በበነያ፣ በማሽሎ፣ በዛርጉላ የጦር ሜዳዎች ከጠላት ጋር ተፋለመ። ዋና ሥልቱ የጠላት ወታደር በውሃ ጥም በሚደክምበት ጊዜ ጠብቆ መምታት፣ እንዲሁም ሥንቅና ትጥቅ ማግኘት ነበር። በ1933 ዓ.ም ደግሞ ቡድኑ ከክፍለ ሀገሩ ዋና ከተማ ጨንቻ በመግባት አካባቢውን ከጠላት በማፅዳት የሀገሩን ሰላም አረጋገጠ።[3]

### ማጣቀሻ ፅሑፎች


1. ሰይፉ አባ ወሎ፣ *የታሪክ ቅርስ*፣ ገጽ 158።
2. ሕይወት አደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 71።
3. "የጀግኖች አደራ"፣ የጀግኖች ማህበር መጽሔት፣ መጋቢት 1983 ዓ.ም፣ ገጽ 37-39።